# ማ ው ጫ

ገፅ

**ከአንባቢያን**...................................2

**የዝግጅት ክፍሉ ማስታወሻ**........................4

**ዓለም አቀፍ**

- ኒዮ ሊበራሊዝም ሸሸ ወይስ አፈገፈገ ?
  የአዲሱ የቀኝ አክራሪ ህዝበኝነት ማቆጥቆጥ፣
  ኸርንጉርጉሩ ዓለማዊ ሁኔታና አገራዊ እንድምታው.....................6

# አዲስ ራዕይ

በየሶስት ወሩ፣ በአማርኛ ቋንቋ እየተዘጋጀች በኢኮኖሚያዊ፣ በፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ዓለም አቀፋዊና ድርጅታዊ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ማብራሪያና ትንታኔ ይዛ የምትቀርብ የኢህአዴግ የትንታኔ መፅሄት ነች፡፡

12ኛ ዓመት ቅፅ 5 ህዳር-ታህሳስ 2010

አዘጋጅ፡- የኢህአዴግ የህዝብና የውጭ ግንኙነት ዘርፍ

አሳታሚ፡- ኢህአዴግ

አድራሻ፡- ስልክ 011-123-43-03

የመ.ሳ.ቁጥር፡-80007

ፋክስ፡- 011-123-43-02/ 011-122-12-34

ኢ..ሜይል- addisreay.mag @ gmail.com

ድህረ ገፅ- WWW.eprdf.org.et/publication

## የምንከተለው ስርአት እውን የጎሳ ፌዴራሊዝም ነውን?

የተወደዳችሁ የአዲስ ራዕይ መጽሄት አዘጋጆች! ሰላምና ጤና ይስጥልኝ! ውድ አዘጋጆች! የመጀመሪያዬ ተሳትፎ የሆነውን ይህ ፅሁፍ ሚዛን የሚደፋ ሆኖ ካገኛችሁን በአዲስ ራዕይ መጽሄት ላይ እንዲወጣ ልኬላችኋለሁ እንደሚሆን አድርጉት፡፡ ወደ ዋናው ርእሰ ጉዳዬ ስገባ።

ተቆጥረውና ተሰፍረው የማያልቁ የጭቆናና የብዝበዛ አይነቶች ለኢትዮጵያ የፌደራል ሥርዓት መወለድ መነሻ ምክንያቶች ስለመሆናቸው አያከራክርም፡፡ይህ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ስርአት ሌሎች የአለም ፌዴራል ሃገራት የሚከተሏቸውን የጋራ ባህሪያት ያሚላ፣ ከራሱ ታሪካዊና ነባራዊ ሁኔታዎች የመነጩ ልዩ ባህሪያት ያሉት፣ በሁሉም የዲሞክራሲያዊ ይዘት መስፈርቶች ሲመዘን የላቀ ዲሞክራሲያዊነት ያለውን ህገ መንግስት በማጽደቅ እየተመራ የሚገኝ ስርአት ነው፡፡

ሆኖም በአሁኑ ጊዜ የዴሞክራሲያዊ ፌዴራላዊ ስርዓት ግንባታ ሂደትን የሚፈታተኑ ተግዳሮቶች ጎልተው እየታዩ ናቸው፡፡ ከዚህም አንዱ በስርዓቱ ደጋፊዎችም ሆነ ተቃዋሚዎቹ ላይ የሚታየው ስለ ስርዓቱ ያለ የግንዛቤ ማነስ ነው፡፡ ስርዓቱ በጎሳ ላይ የተመሰረተ ነው ከሚል ጀምሮ እስከ ለማንነቶች እኩል እውቅናና መብት አልሰጠም የሚል የተሳሳተ ወቀሳ ድረስ፣ ስርዓቱ ትብብርን ሳይሆን ፉክክርን ያበረታታል ከሚለው ጀምሮ እስከ በሀገሪቱ ውስጥ ግጭቶች እንዲስፋፉ ምክንያት ሆኗል የሚሉት ድረስ ክሶች ይቀርቡበታል፡፡

የፌዴራል ስርዓቱን ምንነት በመገንዘብ የግንባታ ሂደቱን ማሳካትና ተግዳሮቶቹን በመታገል የኢትዮጵያን የህዳሴ ጉዞ እውን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ በፌደራሊዝም ፅንሰ ሃሳብ ዙሪያ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራዎች በመሰራት ላይ ናቸው፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ በዚህ ፅሁፌ እውን የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ስርዓት በጎሳ ላይ የተመሰረተ ነውን የሚለውን ነጥብ ለማየት እሞክራለሁ።

እዚህ ላይ በቅድሚያ ጎሳ ማለት ምን ማለት ነው የሚለው ጥያቄ ምላሽ ማግኘት አለበት፡፡ ጎሳ ማለት በአንድ የማህበረሰብ የእድገት ደረጃ ውስጥ በተዋረድ ከግለሰብና ከቤተሰብ ቀጥሎ የሚፈጠር፣ የቤተሰብ ከፍተኛ

የእድገት ደረጃ የሆነ፣ የብዙ ቤተሰቦች ስብስብ የሆነ፣ በደምና በዝምድና ሀረግ ግንኙነት ላይ የተመሰረተ እንዲሁም የጥንታዊ ጋርዮሽ ሥርዓተ ማህበር አይነተኛ ባህሪ መገለጫ እና አሁንም በአንዳንድ በእድገት ወደኋላ በቀሩ ሀገሮችና አካባቢዎች የሚታይ የማህበረሰብ አካል ነው፡፡

በአንፃሩ የኢትዮጵያ የፌዴራል መንግስት በክልሎች የተደራጀ ሲሆን በህገ መንግስቱ አንቀፅ 46 ላይ እንደተመለከተው ደግሞ ክልሎቹ የተዋቀሩት በህዝብ አሰፋፈር፣ በቋንቋ፣ በማንነት እና በህዝብ ፈቃድ ላይ ተመስርቶ ነው፡፡ ህገ መንግስቱ ስለ ማንነቶች ሲያብራራም መገለጫዎቹ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ መሆናቸውን አመልክቷል።

እነዚህ አራት መስፈርቶች አንዳቸውም በትርጉም ደረጃ ጎሳን የሚወክሉ አይደሉም። ይህ ብቻ ሳይሆን የጎሳ ትርጉም ከአሁኑ የኢትዮጵያ ፌደራሊዝም ጋር በየትኛም አመክንዮና ትንተና አይገናኝም፤ አይዛመድም፡፡እናም የፌዴራል ስርዓታችን መሰረቱ ህብረ ብሄራዊነት እንጂ ጎሰኝነት አይደለም፡፡

ከላይ በፌዴራሊዝም የአስተዳደር አወቃቀር ላይ የተነሱት አራት መስፈርቶች በሀገራችን ብቻ ሳይሆን በስዊዘርላንድ፣ በቤልጂየም፣ በካናዳና በሌሎችም የፌዴራል ሥርዓትን በሚከተሉ የበለፀጉ ሀገራት ሥራ ላይ የዋሉ ናቸው። በእነዚህና ሌሎች መሰል አገራት የፊዴራሉን መንግስት በጥምረት የመሰረቱት አካሎች የሚጠሩት ክልሎች፣ ክፍለ ሀገሮች፣ ካንቶኖች፣ ላንደሮች፣ ማህበረሰቦች አልያም ደሴቶች በሚል እንጂ ጎሳ የሚል ወይም ከጎሳ ጋር የተያያዘ ስያሜ ተሰጥቷቸው አይታወቅም፡፡ በአጭሩ የፌዴራሊዝምን ሥርዓት ያራምዳሉ ተብለው ከሚታመኑ ከሁለት ደርዘን በላይ የሚሆኑ አገራት ውስጥ የጎሳ ፌደራሊዝም የሚል ስያሜ የተሰጠው አገር የለም፡፡

እነዚህን ጉዳዮች መሰረት አድርገን ስንነሳ የፌዴራል ስርዓታችን በጎሳ ላይ የተመሰረተ ፌዴራሊዝም ሳይሆን በዲሞክራሲያዊ ብሄርተኝነት ላይ የተመሰረተ ህብረ ብሔራዊ ፌዴራሊዝም (Multinational Federalism) መሆኑን ለመረዳት አይከብድም፡፡

**ሳዲቅ አደም**
**ከአዳማ**

# የዝግጅት ክፍሉ ማስታወሻ

ኢህአዴግ በየጊዜው የሚቀያየረውን አለማዊና አገራዊ ሁኔታ በጥልቀት በማጥናት ለመገንዘብ የሚሞክር ተራማጅና ተማሪ ድርጅት ነው፡፡ የሚያወጣቸው ፓሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እንዲሁም እቅዶች አለማዊና አገራዊ ነባራዊ ሁኔታውን ግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ ስለሆኑ የሚጨበጥና የሚዳሰስ ለውጥ ማምጣት የሚችሉ ሆነዋል፡፡ ባለፍንባቸው ታሪካዊ ሂደቶች ሁሉ የሚያጋጥሙንን ፈተናዎች ወደ መልካም እድልነት እየቀየርን በችግሮች መካከል እየጠነከርን መሄድ የቻልንበት ሚስጥሩም ይሄው የቆየ ድርጅታዊ ባህላችን ነው፡፡

በአንፃሩ በየጊዜው የሚያጋጥሙ አዳዲስ ሁኔታዎችን መገንዘብ ያልቻሉ ድርጅቶች ምንም እንኳን ታላቅ አላማ ሰንቀው ቢነሱም በየመንገዱ በመቅረታቸው በታሪክ ብቻ የሚወሱ ድርጅቶች ሆነዋል። እኛ ግን ዓለማዊም ሆነ አገራዊ ሁኔታው እጅግ በፍጥነት የሚቀያየር ነውና የመማር ፍጥነታችንንም ከዚሁ ሁኔታ ጋር በማጣጣም በአለም አቀፍ ውድድሩ አሸናፊዎች መሆን ካልቻልን የእስካሁኑ የአሸናፊነታችን ገድል የአንድ ወቅት ትረካ ብቻ ሆኖ እንደሚቀር አጥርተን እንገነዘባለን፡፡

ዛሬም ለስኬት ያበቃን የተራማጅነትና የተማሪነት እሴታችን ከኛ ጋር ይገኛል፤ ዛሬም እንደትላንቱ እየተለዋወጠ በሚገኘው ዓለማዊ እና አገራዊ ሁኔታና ፈተና እየጠነከርን የአገራችንና የድርጅታችን የድል አድራጊነት ገድል እናስቀጥላለን፡፡ አዲስ ራዕይም እንደ ድርጅታችን የንድፈ ሃሳብ መፅሄትነቷ በተከታታይ በአዳዲስ ዓለም አቀፋዊና አገራዊ ሁኔታ ላይ ያተኮሩ ትንታኔዎችን ማቅረቧን ትቀጥላለች፡፡

በዚህ እትም የመረጥነው ርእሰ ጉዳይ በህዝበኘነት እና ዓለም አቀፋዊ አንድምታው ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ህዝበኘነት ምንድነው? ታሪካዊ አመጣጡስ ምን ይመስላል? ክስተቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ምን ላይ ይገኛል? ወዘተ... የሚሉትን ጥያቄዎች አንስታ ሰፊ ትንታኔ ትሰጣለች፡፡ መላው የድርጅታችን አባላት ደግሞ ይህን ፅሑፍ እንደመነሻ በመውሰድ በክርክርና ውይይት እንደምታዳብሩት ይጠበቃል፡፡

**መልካም ንባብ !!**

## ዓለም አቀፍ

# ኒዮ ሊበራሊዝም ሸሸ ወይስ አፈገፈገ ?

### የአዲሱ የቀኝ አክራሪ ህዝበኝነት ማቆጥቆጥ፣ ዥንጉርጉሩ ዓለማዊ ሁኔታና አገራዊ እንድምታው

## መግቢያ

የአለም አቀፉ የፋይናንስ ቀውስ ከተከሰተ አንድ አስርት አመት ወዲህ አለም በነውጥ እና በፖለቲካ አለመረጋጋት ውስጥ በመዳከር ላይ ትገኛለች። ዛሬ ዛሬ በብዙ አንጋፋ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ሊቃውንት ህዝብንና አገርን ከማሳደግ ይልቅ ለድህነትና ለጥቂቶች መክበር ምክንያት የሆነው ገበያ አክራሪው የኒዮ ሊበራሊዝም አስተሳሰብ ለብሄረተኛና ወገንተኛ ወይም ህዝበኝነት አስተሳሰብ ለሚያራምዱ ፖለቲከኞች ማቆጥቆጥ ምክንያት እንደሆነ በተለያዩ ጥናታዊ ጽሁፎቻቸው ያመለክታሉ።

ከሁለት አስርት አመታት ወዲህ የቀኝ አክራሪ ህዝበኝነት አስተሳሰብ ያላቸው የፖለቲካ ምርጫ ተወዳዳሪዎች በተለይም በምዕራቡ አለም የመራጩን ከፍተኛ ድምጽ እያገኙ የመጡበት ሁኔታ የተስተዋለበት አመታት ናቸው። በተለይም ደግሞ በ2016 የዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ በንግግራቸው ጽንፈኛ አስተሳሰብ የሚያራምዱትና በፖለቲካ የካበተ ልምድ የሌላቸው እንደሆኑ የሚነገርላቸው የሪፐብሊካኑ እጩ ዶናልድ ትራምፕ ባልተጠበቀ ሁኔታ ማሸነፋቸው፤ ይህንን እውነታ የሚያጠናክር እንደሆነ የተለያዩ የፖለቲካ ተንታኞች ይስማሙበታል።

ወግ አጥባቂ ብሄረተኛ ህዝበኝነት አስተሳሰብ ከሚያራምዱ ፖለቲከኞች ማንሰራራት ጋር ተያይዞ፤ እንዲሁም በአንጻሩ አክራሪነት፣ ወግ አጥባቂነት፣ ብዝሀነትን ያለማስተናገድ፣ የሌላ አገር ዜጎችን እንደ ጠላት መመልከት፣ ስደተኞችን ያለመቀበል አስተሳሰቦችና ተጓዳኝ እርምጃዎች መከሰታቸው አልቀረም።

☞

ይህ የብሄረተኛ ህዝበኝነት አስተሳሰብ እንደ ኒዮሊበራሊዝም በአሜሪካና በምዕራብ አውሮፓ ሳይወሰን በእስያና በላቲን አሜሪካ አገራት እየተስፋፋ በመሄድ ወደ አፍሪካ ምድር የማይዘልቅበት ምክንያት አይኖርም።

ለመሆኑ ህዝበኝነት ምንድነው? የህዝበኝነት አስተሳሰብ መነሻዎችና መገለጫዎች ምን ምን ናቸው? የሚሉት ጥያቄዎች በጉዳዩ ላይ የተለያዩ ጥናቶችን ያደረጉ ባለሙያዎችን ጽሁፍ ዋቢ በማድረግ እንደሚከተለው ተብራርቷል።

## 1. ውጥንቅጡ በመውጣት ላይ ያለ ዓለም

ሪቻርድ ሃስ "ውጥንቅጡ የወጣ ዓለም "A world in Disarray" ብሎ የሚገልፀው ጉዳይ ዓለም በዋናነት ከሃገራዊ ፖለቲካዊ የተለወጠ እውነታ በመነሳት በዓለም አቀፍ ግንኙነትና ሥርዓት (Rules based international order) ላይ በስፋት እየተስተዋለ ካለው የተገማችነት መጥፋት ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ሪቻርድ በጽሁፉ በተለይም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ የናዚዝምን ሽንፈት እውን በማድረግ ከፍተኛውን ድርሻ በተወጡት በአሜሪካና በቀድሞው ሶቪየት ህብረት እንዲሁም በምዕራባውያን ወዳጆቻቸው የተጀመረውና በኋላ መልኩ የምዕራቡን ዓለምን የአስተሳሰብ የበላይነት ባስጠበቀ መልኩ እስከ አሁን ድረስ የዘለቀው ዓለማዊ ሥርዓት ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እየገጠሙት ያሉትን ዘርፈ ብዙ ቀውሶች በስፋት ይተነትናል፡፡ ይኸ ሥርዓት በብዙዎች እምነት ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በፊት የነበረውና በኃይል ሚዛን (Balance of power) ላይ የተመሠረተው በፉክክርና በግጭት የተሞላ ሥርዓት ፈርሶ ከሞላ ጎደል በግልጽ በሚታወቁ ህግጋትና መርሆዎች የሚገዛ (Rules Based) ሆኖ ከመጣ ወዲህ ከነበርካታ ውሱንነቶቹም ጭምር ለዓለም ሰላምም ሆነ በሃገራት መካከል ላሉ ግንኙነቶች እንደ ገዢ ማዕቀፍ ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል፡፡

ይህ ስርዓት ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቂያ ወዲህ ወዲያውኑ በተበሰረው የሊብራል ዲሞክራቲክ አስተሳሰብ የበላይነትና ብቸኛ አማራጭነት አስተሳሰብ ታግዞ የምዕራቡ ዓለም ተፅዕኖ ፈጣሪነት እጅጉን የዳበረበትና ዓለም አቀፍ ግንኙነቶች ከሞላ ጎደል በዚሁ ቅኝት ብቻ የሚገዙበት ለመሆን በቅቶ እንደነበርም ይታወቃል፡፡

☞

በዚህ ማለቂያ የሌለው በሚመስል ድል በመበረታታትም የምዕራቡ ዓለም እምነቱን፣ አስተሳሰቡንና ኃይማኖቱን ጭምር በሌሎች ዓለም ህዝቦች ላይ ያለ ይሉኝታ ለመጫን ያደፋፈረውን ጉልበት ለግሶትና በራስ መተማመን ፈጥሮለት እንደነበር ግልፅ ነው፡፡ እንደ ሪቻርድ ሃስም ሆነ እንደ ሌሎች ምዕራባዊያን ታዛቢዎች እምነት ይኸ የምዕራቡ ዓለም የአስተሳሰብ የበላይነት በሌሎች ተቀናቃኞች ተነሳሽነትም ይሁን በምዕራባውያኑ በራሳቸው የውስጥ ፈተና ምክንያት ከ25 ዓመት በፊት የነበረው በራስ መተማመን ተሸርሽሮ ወይም ደግሞ እንደ ሃስ አገላለፅ "የኢኮኖሚ እውነታው ወደ ውስጥ ጉዳይ መጀመሪያ ማየትን" የግድ የሚል ሆኖ ሳለ ውጭ ውጭ ማየት በመብዛቱ ምክንያት ጭምር የቀድሞ ተሰሚነቱ የቀነሰበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ውስጣዊ ሁኔታን ወደ ጎን በመተው ነገሮችን በውጫዊ ቅኝት ለመምራት መሞከር መዘዙ ትልቅ መሆኑን ለማየትም የሚጠቅም ሆኗል፡፡

ካሁን ቀደም በተደጋጋሚ በቀረቡ ፅሑፎች ለማሳየት እንደተሞከረው የምዕራቡ ዓለም ሊበራል ዴሞክራቲክ አስተሳሰብ እንደ ብቸኛ አማራጭ ሲገፋበት የነበረበት ዘመን ሄዶ ሄዶና ከእውነታ ጋር ተላትሞ ዘላቂነቱንና ዘላዓለማዊነቱን ሲሰብኩ የነበሩ የርዕዮተዓለም ቀሳውስቱን ሳይቀር ያሳፈረበት ሁኔታ እንደተፈጠረ ግልፅ ነው፡፡ ሊበራል ዴሞክራሲም ሆነ የሊበራል ደሞክራሲ ገበያ አክራሪ ፅንፍ የሆነው ኒዮ ሊበራሊዝም ብቸኛ አማራጮች እንዳልሆኑ ብቻ ሳይሆን በሂደትም ቢያንስ በተሰበኩበትና በተዘመረላቸው መልኩ በታዳጊ ሀገሮች ብቻ ሳይሆን በበለፀጉ ሀገሮችም ጭምር የራሳቸው ውስንነት ያላቸው አማራጮች መሆናቸውን ድርጅታችን ኢህአዴግ ከጅምሩ የተገነዘበውና በማያጠራጥር ሁኔታ አቋም የያዘበት ጉዳይ ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ላይ ረዥም ሃተታ ማቅረቡ አስፈላጊ አይሆንም፡፡ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ በዓለም እየታየ ባለው የፋይናንስና የኢኮኖሚ ቀውስ እንዲሁም በቅርቡ እየታየ ካለው የፖለቲካ ቀውስ በላይ ዋቢ የሚያስፈልገው አይደለምና ፡፡

ይሁን እንጂ ፈረንጆቹ እንደሚሉት "ህፃኑን ከነእጣቢው" መጣል ተገቢ ስላልሆነ ብቻ ሳይሆን ወደድነውም ጠላነውም ዓለም ለረዥም ጊዜ ስትመራበት የመጣችበት ሥርዓት የምዕራብ ዓለም ሊበራላዊ ቅኝት በመሆኑ እና ለረዥም ዓመታትም እየተንገዳገደ ሊቀጥል የሚችልበት እድልና አቅም ያለው በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት ይኸ አስተሳሰብ የገባበትን አጣብቂኝ በትክክል መረዳት መቻላችን ቢቻል የተሻለ የዓለም ሥርዓት

☞

ለመፍጠር፣ ካልተቻለ ደግሞ ውጥንቅጡ መውጣት በጀመረ ዓለም እውነታ ማዕቀፍ ውስጥ ሆነን ጥቅሞቻችንን አስጠብቀን መጓዝ የምንችልበትን ሁኔታ ከመፍጠር አንፃር የጎላ ጠቀሜታ ስለሚኖረው ጉዳዩን ዘርዘር አድርጎ ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አሁን በምንኖርበት ግሎባላይዝድ ዓለም ውስጥ የሃገራት እጣ ፈንታ የተሳሰረ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሁላችንም ብንሆን እንደየሁኔታው የምንጋራቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እሴቶች መኖራቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት በበለፀጉት ሃገራት ውስጥ የሚከሰቱ ክስተቶች በእኛ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እሴቶች ላይ ሊያመጡት ከሚችሉት ተፅዕኖ አንፃር ጉዳዩን በጥልቀት ለመገንዘብ መሞከርም ተገቢና አትራፊ ይሆናል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በዴሞክራሲ ግንባታ፣ በፖሊሲ ባለቤትነትና በልማት፣ በአካባቢያዊ ሰላምና መረጋጋት ዙሪያ የምንሰራቸው ሥራዎች ይነስም ይብዛም በነዚህ አገራት ከሚኖሩ ፖለቲካዊ አዝማሚያዎች የሚያተርፉትም ሆነ የሚያጡት ነገር ስለሚኖር ጉዳዩን በተሻለ ለመረዳት መሞከርን አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡ ከሃገራት ጋር ያሉን የሁለትዮሽ ግንኙነቶች ምንም ይሁን ምን በየደረጃው በጋራ የምንጋፈጣቸውና ለመፍታት የሁላችንም የጋራ ጥረት የሚጠይቁ በርካታ ፈተናዎች በየሃገራቱ በሚከሰቱ ክስተቶች ላይ ተመስርተው የሚባባስበትም ሆነ የሚሻሻሉበት ሁኔታ ስለሚኖር ጉዳዩን በተመለከተ የተሻለ ግንዛቤ መያዝም ግድ ይላል፡፡በተለይም ከአክራሪነት፣ ከአሸባሪነትና እንዲሁም ከህገ ወጥ የሰዎች፣ የገንዘብና የጦር መሣሪያዎች ዝውውርና ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ የሚያዙ አቋሞችና የሚራመዱ እምነቶች በዚህ ረገድ የምንሰራውን ስራ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ተፅዕኖ ሊያሳርፉበት እንደሚችሉ ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ነው ውጥንቅጡ እየወጣ ያለውን ዓለም ዋና ዋና ባህሪያት ከመተንተናችን በፊት ለዚህ ውጥንቅጥ መፈጠር የአንበሳውን ድርሻ የያዘውን የምዕራቡ ዓለም ሊበራሊዝምም ሆነ ኒዮ-ሊብራሊዝም ይዞት የመጣው ከኃይማኖት የተጠጋ እርግጠኝነት ያስከተለውን ፈተና በአጠቃላይ፣ በተለይም ደግሞ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በዋና ዋናዎቹ የምዕራቡ ዓለም ሃገራትም ሆነ ሌሎች ተፅዕኖ ፈጣሪ ሃገራት አካባቢ የሚታዩትን ቀውሶች ማየት አስፈላጊ የሚሆነው፡፡

☞

## 2. የምዕራቡ ዓለምና የፅንፈኛ ፖለቲካ ተቀባይነት እየጨመረ መምጣቱ

### 2.1. የሊበራል ሥርዓቱ የገባበት አጣብቂኝ

ላለፉት ሦስት መቶና ከዛ በላይ ዓመታት የምዕራቡ ዓለም የነፃ ገበያ መር ኢኮኖሚን ማቀንቀን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ካፒታሊዝም በየወቅቱ የሚፈራረቁ ፈተናዎችን እየተሻገረ በመላው ዓለም ሊባል በሚችል ደረጃ ገዢ አስተሳሰብና ተፅዕኖ ፈጣሪ ርዕዮተ ዓለም ለመሆን የበቃባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡ ካፒታሊዝም የሚመራበት የነፃ ገበያ ሥርዓት በየወቅቱ ያሳያቸው ዕድገቶችና ከጊዜ ወደ ጊዜ ያሳያቸው ተለዋዋጭ ባህሪያት እንደነበሩት ይታወቃል፡፡ ይሁንና በዋነኛ አቀንቃኞቹ ዘንድ እንደ ስኬት ምንጭ ከመቆጠር አልፈው እንደ ኃይማኖት የሚሰበኩለት ከሞላ ጎደል ቋሚ ሊባሉ የሚችሉ ባህሪያት ያሉት ሥርዓት ሆኖ እስከአሁን ድረስ ሊዘልቅ ችሏል፡፡ የነፃ ገበያ ስርዓት የግለሰቦችን ኃብት የመፍጠር ሚናን ከአምልኮ ባልተናነሰ የሚቀበል ስርዓት ነው፡፡ በዚህ አስተሳሰብ መሠረት የህብረተሰብ ዕድገትን የሚወስኑትና ህብረተሰብን ወደፊት እንዲጓዝ የሚያስችሉት ኃሳቦችም ሆኑ ድርጊቶች በዋናነት የፈጠራ ችሎታቸውን የረጋውን የህብረተሰብ አኗኗር (status quo) ለመረበሽ (disruption) እና እንቅፋት የሆነን አመለካከትም ሆነ አሠራር አስወግዶ ለትርፋማነት አመቺ ሁኔታ መፍጠርን (creative destruction) ዓላማ ለማዋል በተዘጋጁ ግለሰቦች እንቅስቃሴ ላይ የሚመሰረት ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ ከጅምሩ ያራመደው የፖለቲካ አስተሳሰብ ለለውጥ ጉዞ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ የመንግስትም ሆነ የማህበረሰብ ተቋማትን ቢቻል በማለዘብ ካልሆነም ደግሞ በአብዮት ጭምር ማስወገድን እንደ ተመራጭ አማራጭ የሚወስድና በሂደት ሊበራሊዝም እየተባለ የሚጠራው አካሄድ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ሊበራሊዝም የባለኃብቱን የመንቀሳቀስና እንደፈለገ ትርፍን የማጋበስ መብት ለማስጠበቅ ታስቦ የተጀመረና በባህሪው ምንም ዓይነት ዴሞክራቲክ ይዘት (element) ያልነበረው ቢሆንም ከጊዜ ብዛት የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን ባካተተ መልኩ በሂደት እየተስተካከለ ሊበራል ዴሞክራቲክ በሚል አገላለጽ ለመታወቅ በቅቷል፡፡

☞

በ19ኛው ምዕተ ዓመት የተከሰተው የኢንዱስትሪያል ካፒታሊዝም አብዮት እጅግ በርካታ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶች አጅበውት የተከናወነ ሆኖ በመጨረሻም ለአውዳሚ የዓለም ጦርነቶችና ለአምባገነናዊና ፋሽስታዊ መንግስታት መፈጠርም ምክንያት እስከመሆን ደርሶ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ቀድሞውኑም ቢሆን ካፒታሊዝም ለህብረተሰቡ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ የሚያመጣቸው መልካም ትሩፋቶች በማህበረሰቡ ዘንድ በሚፈጥረው አጠቃላይ ረብሻ (disruption) አማካኝነት በሚያስከትለው አጠቃላይ ማህበራዊ ቀውስ ምክንያቶች በዜሮ የሚጣፉበት ሁኔታ እንደነበር ብዙ ተንታኞች ይስማማሉ፡፡ ታሪክ በተጨባጭ የሚያሳየንም ካፒታሊዝም በየጊዜው በሚወስዳቸው ጥገናዊም (cosmetic) ሆነ የምር የሆኑ ለውጦች አማካኝነት በትሩፋቶቹና በሚያስከትላቸው ቀውሶች መካከል ያለውን ሚዛን በመጠበቅ በኩል ከሞላ ጎደል የተሳካ ሊባል የሚችል ስራ እየሰራ ቢመጣም አሁን ባለንበት ደረጃ በተለይም ካፒታሊዝምን ቀድመው በተቀበሉትና የዳበረ በሚባል ደረጃ ላይ በደረሱት ሃገራት ዘንድ የተባባሰ የቀውስ ምንጭ ሆኖ ለማህበራዊ ትርምስ ማጋለጥ የጀመረበት ደረጃ ላይ መድረስ ችሏል፡፡

ፖንካጅ ሚሻራ የተባለ ፀሐፊ "ኤጅ ኦፍ አንገር፣ ሂስትሪ ኦፍ ዘ ኘረዘንት" በሚለው መፅሐፉ በትክክል እንዳስቀመጠው ካፒታሊዝም በ19ኛው ክ/ዘመን መገባደጃና በ20ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ ያጋጠመውን ዓይነት ቀውስ የፈጠሩበት ክስተቶች አሁንም በብዙ ሃገራት ዘንድ በስፋትና በጥልቀት መከሰት መጀመራቸውን ዋቢ በመጥቀስ ያስረዳል፡፡ ፖንካጅ እንደሚለው፣

"በምዕራቡ ዓለም ካፒታሊዝም ያመጣው የቴክኖሎጂ ፈጠራና ኢኮኖሚ እድገት በተደራጀ ሥርዓታዊ ብዝበዛ፣ እጅግ እያደገ በመጡ ኢፍትሐዊ የሃብት ክፍፍል፣ በማህበራዊ ግንኙነት መበጣጠስ፣ እንዲሁም በማህበረሰቦች መካከል በሚፈጠር የሃብት ልዩነት አማካኝነት በዜሮ የሚባዙበት ሁኔታ በብዛት ይፈጠራል፡፡ ይኸ የማህበራዊ ሕይወትን የመረበሽ ሂደት (disruption) አሁን በብዛት እየታየ ያለበትና በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ህዝቦች የህይወት ትርጉምን የሚያዩበትን ሁኔታ ማዛባት የቻሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡"

☞

ይህ እውነታ ያልተሳኩም ሆነ የተሳኩ የካፒታሊዝም ግንባታ ሙከራዎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተደረገባቸው በርካታ ሃገራትም ጭምር የሚታይ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት እንደ አሜሪካና ፈረንሳይ፣ እንዲሁም ጀርመን፣ፖላንድ፣ ኔዘርላንድስና ኦስትሪያ ባሉ የዳበረ የሊበራል ዲሞክራሲ ልምድ ባላቸው ሃገራት ጭምር በስፋት መስተዋል ከመጀመሩም በላይ በየሃገራቱ ያለውን ፖለቲካ ወደ ተካረረ ፍጥጫ እንዲያመራ የራሱን አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ካፒታሊዝም አሁን ለደረሰበት ቀውስ መባባስ ትልቁን ሚና የተጫወተው ደግሞ በተለይም ከ1970ዎቹ ወዲህ በሥራ ላይ ውሎ የኢኮኖሚውን ዋና ትኩረት ከማኑፋክቸሪንግና ከሌሎች መሰል ዘርፎች ይልቅ የለየለት ቁማር ወደሚመስል ፋይናንሻላይዜሽን በማድረግ ግልጽ የገበያ አክራሪነትን የሚሰብከው የኒዮ ሊበራል አስተሳሰብ የፖለቲካውን ገበያ (political market place) ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ መቆጣጠር መቻሉ ነው፡፡ ኒዮ ሊበራሊዝም በርካታ አውዳሚ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሙከራዎችን ያካሄደ ቢሆንም በበለፀጉት ሃገሮች ዘንድ የነበሩትን የዳበሩ አምራች ዘርፎችን በሂደት ከጥቅም ውጭ በማውጣት ሁሉም ነገር ወደ ቁማር ጨዋታ እንዲወርድ ያደረገበት አካሄድ ሚሊዮኖችን ለቤት አልባነት፣ ለፍፁም ድህነትና ለከፋ ተስፋ ቢስነት የዳረገበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ይህ ሁኔታ በድኅማም ሆነ በተራማጅ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፖሊሲዎች አማካኝነት የሥርዓታቸውን ፍትሃዊነት ጠብቀው ለመቆየት በሚውተረተሩ ስካንዲኔቪያን የመሳሰሉ ሃገራት ውስጥ በስፋት የሚገለጽበት ሁኔታ የለየለት ኒዮሊበራል አጀንዳ ከሚያራምዱ ሃገራት ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ነው ሊባል ይችል ይሆናል፡፡ ይሁንና በነዚህ ሃገራትም ውስጥ ቢሆን ካሁን በፊት በሥልጣን ላይ የነበሩ ፖርቲዎች ፍትሐዊነትን ለማረጋገጥ የነበራቸው ቁርጠኝነት እየተሸረሸረ ለኒዮሊበራል ገበያ አክራሪ አስተሳሰብ መንበርከክ በጀመሩበት ሁኔታ ሊበራሊዝምን በሶሻል ዴሞክራቲክ ቅኝት ለማዳን ያስቻሉ ስኬታማ የነበሩ አካሄዶች ቀውስ ውስጥ የገቡበት ሁኔታ መፈጠሩ አልቀረም፡፡

ኒዮ ሊበራሊዝም ያባባሰው ኢፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል ካፒታሊዝም ከገባበት መዋቅራዊ ቀውስ የመጣ ቢሆንም በነዚህ ሃገራት ዘንድ

☞

በስፋት እንደሚታየው በዚህ መዋቅራዊ ቀውስ ሳቢያ ሕይወታቸው የተመሰቃቀለባቸው ዜጎች ተጠያቂ የሚያደርጉት ችግሩን ያመጡትን ኃይሎችና ይኸንን ቀውስ ያመጣውን ሥርዓት ሳይሆን “ሌሎችን” ነው፡፡ የፖለቲካ እንቅስቃሴው መፋዘዝ ባለበትና ዜጎች ገዥዎች በልካቸው መጥነው በሚልኩላቸው የኒዮሊበራል ሚዲያ ቀጣይ ሰበካዎች ላይ ብቻ ተመስርተው አቋም በሚያራምዱበት ሁኔታ ለችግሮቻችን ሁሉ ተጠያቂዎች እኛን የማይመስሉት “ሌሎች” ናቸው በሚል የተበከለ አዝማሚያ የሚጋለጡበት ሰፊ ዕድል መፈጠሩ አይቀሬ ነው፡፡

በኒዮ-ሊበራሊዝም አውዳሚ ጀብዶች ህይወቱ የተመሰቃቀለ ህዝብ “ሌሎችን” ተጠያቂ ሲያደርግ ምን ሊመስል እንደሚችል ለመረዳት በመካከለኛው ዩኤስኤ ግዛቶች ውስጥ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ፋብሪካዎች መዘጋት ጋር ተያይዞ “የዝገት ቀለበት” “Rust Belt” በመባል የሚታወቁትን ከፔንሲልቫኒያ እስከ ዊስከንሲን ያሉ ስቴቶችን ህዝብ ማየቱ ይበቃል፡ ፡ይህ ባንድ ወቅት የአሜሪካ ታላቅነት ምንጭ የሆነ፣ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን ቀጥ አድርጎ ይዞ የነበረና ለአስር ሚሊዮኖች የገጠር እና ከተማ ነዋሪ የሆኑ ነጮች ኑሮ መሻሻልና ሰፊ መካከለኛ መደብ መፈጠር አስተዋጽኦ ያደረገው አካባቢ በአሁኑ ሰዓት በሺዎች የሚቆጠሩ ፋብሪካዎች ተዘግተው፣ ሥራዎች ወደ ቻይናና ሜክሲኮ የሄዱበት ሁኔታ ተፈጥሮ የሙት መንፈስ የሰፈረበት እስከመምሰል ደርሷል፡፡ አንድ ወቅት የከፍተኛው መካከለኛ መደብ የኑሮ ደረጃ የነበራቸው አስር ሚሊዮኖች አሜሪካውያን ለፍፁም ድህነት የተዳረጉበት ሁኔታ ተፈጥሮ በከፍተኛ ተስፋ መቁረጥና ቁጣ ውስጥ የገቡበት እውነታ ላይ ተደርሷል፡፡

ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ማን ነው? ለሚለው ጥያቄ በርካታ መልስ ሊኖር እንደሚችል ይታመናል፡፡ ፋሪድ ዘካሪያ በዚህ ጉዳይ ላይ በፃፈው ዕሑፍ በትክክል እንዳስቀመጠው በምዕራቡ ዓለም ያለው ፖለቲካ አሁን ለገባበት አጣብቂኝ አስተዋጽኦ ያደረጉ በማለት አራት ነገሮችን ይጠቅሳል፡፡ የመጀመሪያውና ከህዝብ ቁጥር ጋር የተገናኘው (demographic factor) የሚባለው ነው፡፡ ይኸውም ባደጉት ሃገሮች ዘንድ ያለው የወሊድ መጠን ዝቅተኛ መሆን አምራች የሆነው የኀብረተሰብ ክፍል እንዲቀንስና በጡረታ የሚኖረው የህብረተሰብ ክፍል እንዲጨምር በማድረግ ከፍተኛ መዋቅራዊ

☞

ጣጣ ማምጣቱ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ የቴክኖሎጂ እድገትና መስፋፋት ለወትሮው በትንሽ ክህሎትም ጭምር የፋብሪካ ስራ ላይ ተሰማርተው የነበሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ሥራ የሚያሳጣበት ሁኔታ ፈጥሯል ይላል፡፡

ብዙዎች እንደሚስማሙት ምንም እንኳ በአሜሪካ ውስጥ የተለመዱት የማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች በተለይም ብረታ ብረት፣ ጨርቃጨርቅና አልባሳት ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ የተዘጉ ቢሆንም የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ በአጠቃላይ ያደገበት ሁኔታ እንዳለ ያስቀምጣል፡፡ በራሱ እምነት የተለወጡት አዲሶቹ የማኑፋክቸሪንግ እንቅስቃሴዎች እጅግ ዘመናዊና በባህሪያቸው ጥቂት ከፍተኛ ክህሎት ብቻ ያላቸው ሰዎች የሚቀጥሩ መሆናቸው ነው፡፡ የየሃገራቱ የትምህርትና ስልጠና ሥርዓት ባለንበት ዘመን መፈጠር የጀመሩ ቴክኖሎጂዎችን ቆየት ላሉ ምሩቃንና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ከሥራ ላፈናቀላቸው ዜጎች በስፋት ማቅረብ ባልቻለበት ሁኔታ ባነሰ ክፍያ ይህንኑ ሥራ መስራት የሚችሉ የቻይና፣ የህንድና፣ የፊሊፒንስ ባለሙያዎች በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የሰው ኃይል እጥረትን ለማሟላት ተመራጭ እየሆኑ መምጣታቸው እንደማይቀር ግልፅ ሆኗል፡፡ በተለመደው የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ተቀጥረው ይኖሩ የነበሩ ሚሊዮኖች ከዘመን አመጣሽ ቴክኖሎጂ ጋር መግባባት ሳይችሉ ቀርተው ለተስፋ መቁረጥ የተዳረጉበትና ለችግራቸው ሌሎችን ተጠያቂ ማድረግ የጀመሩበት ይህ ጥያቄ ካፒታሊዝምን ለተጨማሪ ቀውስ ዳርጓል፡፡

በሦስተኛ ደረጃ ለቀውሱ አስተዋፅኦ ያደረገው በነዚህ አገሮች ዘንድ ያለው ሰፊ የገንዘብ እጥረት እንደሆነ ይታመናል፡፡ የአውሮፓ ህብረትን የገንዘብ እጥረት እንደምሳሌ ብናይ የህብረቱ ዕዳ መጠን ከአጠቃላይ የአውሮፓ ውስጥ ምርት (ጂዲፒ) 67 በመቶ ደርሷል፡፡ በዩናይትድ ስቴትስ ደግሞ ይህ አሃዝ 81 ፐርሰንት ይደርሳል፡፡ የጡረታ ወጪና የማህበራዊ ዋስትና በብዛት መደጎም ባለበት ሁኔታ የህብረተሰቡን ኑሮ ለማሻሻል መከናወን ያለባቸው መዋቅራዊ እርምጃዎች ለምሳሌ አዳዲስ መሠረተ ልማቶችን መዘርጋት ወዘተ - ግዙፍ ገንዘብ ካፒታል የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ ሊተገበሩ የሚችሉበት ዕድል እጅግ ጠባብ መሆኑ አይቀርም፡፡

በአራተኛ ደረጃ ለቀውሱ መባባስ ተጠያቂ የሚደረገው የግሎባላይዜሽን ሥርዓት ነው፡፡ ኒዮ ሊበራሊዝም ባስከተላቸው መዋቅራዊ

☞

ችግሮች ምክንያት ተወዳዳሪነቱ በሂደት እየቀነሰ ለመጣው የዩ.ኤስ.ኤም ሆነ የሌሎች ምዕራባውያን ሃገራት አምራች ዘርፍ ለገባበት ጣጣ ተጠያቂ የሚሆነው ይኸው ስርዓት ነው፡፡

ይሁንና በአሜሪካም ሆነ በሌሎች የበለፀጉ ሃገሮች ዘንድ የፖለቲካውን ትኩሳት የሚወስነውና አሁን በስፋት እየታየ ላለው ትርምስ ከችግር ውስጥ ባሉም ሆነ ባልተነኩ ዜጎች ዘንድ እንደ ችግሩ ምንጭ የሚቆጠሩት "ሌሎች" ናቸው፡፡ በከተማ ውስጥ በድህነት የሚኖሩ ጥቁሮችና ስደተኞች ስራ ይሻማሉ ስለሚባሉ፣ ግብረሰዶማውያንም ሆኖ ሌሎች ከማህበረሰቡ ወጣ ያለ አኗኗር ዘይቤ የሚከተሉ ወዘተ ሁሉ በዚህ "በሌሎች" በሚባለው ሰፈር የሚመደቡበት ሁኔታ በስፋት ይፈጠራል፡፡ በተለይም ደግሞ በአውሮፓም ሆነ በአሜሪካ ከስደተኞች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ መጨመር ጋር ተያይዞ "ባህላችን አደጋ ላይ ወደቀ" "የነጭ ዝርያ ሊዋጥ ነው" የሚሉ መፈክሮች የፖለቲካውን ድባብ በፅንፎች መካከል የሚደረግ ፍልሚያ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

የምዕራቡን ዓለም ፖለቲካ ወደ ትርምስ ካስገቡትና ከላይ ለመጥቀስ ከሞከርናቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ባልተናነሰ ፅንፈኝነትን እያባባሰ ያለ ሌላ መሠረታዊ ሃቅም አለ፡፡ እንደሚታወቀው ሁሉ በምዕራቡ ዓለም ያለው ፖለቲካ በሂደት ሚሊዮኖችን ከዋነኛ ተዋናይነት ወደ በይ ተመልካችነት የገፋና ጥቂቶች ባለ ሃብቶች የህዝቡ አንድ በመቶ የማይበልጥ ቁጥር ባላቸው የሚዲያም ሆነ የሌሎች ሃብቶች የበላይነት ላይ ተመስርተው የሚያሽከረክሩበት የልሂቃን ጨዋታ (plutocracy) ከሆነ ቆይቷል፡፡ የህዝብ ተሳትፎ የቅንጡ ፖለቲከኞችን ሰርግ ከማድመቅ በዘለለ በፖለቲከኞች የፖሊሲም ሆነ የአደረጃጀት ምርጫ ላይ ያለው ተጽእኖ ወደ ዜሮ የተጠጋ በሆነበት ሁኔታ ዜጎች በፖለቲከኞችና በዴሞክራሲ ተቋማት ላይ ተስፋ ቢቆርጡ የሚያስገርም አይሆንም፡፡ በየደረጃው ያሉ በምርጫ የሚሞሉ የሥልጣን ክፍተቶች በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ በባለፃብቶች ወይም የባለሃብቱን ይሁንታ ባገኙ አገልጋዮቻቸው ብቻ በሚሞሉበት፣ ቾሚስኪና ኤድ ሄርማን እንደሚሉት ኒዮሊበራል ሚዲያው ህዝቡ ለባለፀጋ ፖለቲከኞች ሳይወድ በግዱ "የሚሰጠውን" ይሁንታ "በሚፈበርኩበት" ሁኔታ የተገፉ ሚሊዮኖች ያልበላቸውን ስፍራ የሚያኩበት ዕድል በስፋት መፈጠሩ

☞

አይቀሬ ነው፡፡ አሁን በተለያዩ የበለፀጉ ሃገራት እንደምናየው በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች በነዚህ የዴሞክራሲ ተቋማት ላይ ያላቸው እምነት ተሟጦ ለችግሮቻቸው መፈታት አንዳች ተአምራዊ ለውጥ ያመጣሉ በሚሏቸው ግለሰቦች ወይም ፖርቲዎች ላይ የሚንጠላጠሉበት ሁኔታ በስፋት ይስተዋላል፡፡

ፋሪድ ዘካርያ ከላይ በጠቀስነው ፅሑፍ እንደሚያስቀምጠው፣

"በዴሞግራፊ፣ በግሎባላይዜሽን፣ በቴክኖሎጂና በበጀት እጥረት የሚገጥሙ ችግሮችን ለመፍታት ፖሊሲ አመንጪዎች እጅግ የጠበበ የመፍትሄ አማራጮች ብቻ ነው የሚኖራቸው፡፡ ማድረግ ካለባቸው ውስጥ ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ወጪ፣ የተሻለ የሰራተኛ ስልጠና እና የተሟላ የጤና ሥርዓት ለውጥ ማድረግ ይገኙባቸዋል፡፡ ይሁንና በነዚህ መፍትሔዎች ብቻ የሚመጡ ተጨማሪ ለውጦች እጅግ ተዓምራዊ ለውጥን ለሚጠብቅ ህዝብ የበለጠ የብስጭት ምንጭ ከመሆን የዘለለ ሚና አይኖራቸውም፡፡ ለዚህም ነው መራጮች የሚፈልጉት እነዚህን ተዓምራዊ ለውጦች ማምጣት የሚችል ደፋርና ባለራዕይ መሪን የሚሆነው፡፡ መራጮች ይህ አይነት ደፋር ሰው የዴሞክራሲ አሰሪ ተቋማትን አሽቀንጥሮ ጥሎ የሚፈልጉትን ተዓምር እንዲሰራ መሻታቸው አያስገርምም፡፡"

ጄዲቫንስ "A Hilibily Elegy" በሚለው መፅሐፉ በትክክል እንዳስቀመጠው "በአፖላቺያን ድሃ ለችግሩ ሁሉ ተጠያቂ የሚያደርገው ጥሩ የእንግሊዘኛ ዓረፍተ ነገሮችን የሚናገር እና ተክለ ቁመናው የተስተካከለ ኦባማና ስለ ጤነኛ አመጋገብ አገር ምድሩን የምትመክር ሚስቱን ነው ይላል"፡፡ ይህ የሚያሳየን ለኦባማ ያለ ተቋውሞ ወይም ለትራምፕ ያለ ድጋፍ አለን ከሚሉት ፖሊሲ ጋር የግድ የተቆራኘ አለመሆኑ ነው፡፡

በታሪክም እያየነው እንደመጣነው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ በስፋት በታየባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ ለችግር ሁሉ መፍትሔ አለን ብለው አቧራ የሚያስነሱ ሃሳውያን መሲሆች መፈጠራቸው አይቀርም፡፡

አሁን በአውሮፖና በአሜሪካ እያየን ያለነው ለእንደዚህ ዓይነቱ መሪ ያለ ፍላጎት የዴሞክራሲ ተቋማትንም ጭምር ህልውና በሚፈታተን መልኩ እውን እየሆነ በስፋት እየታየ መሆኑን ነው፡፡ እነዚህ መዋቅራዊ ችግሮችን በተዓምር የሚፈቱ የሚባሉት መሪዎች ራሱን ዴሞክራሲን ሆነ ግሎባላይዜሽንን እስከምን ድረስ ይፈታተኑታል የሚለውን በሚቀጥሉት ገፆች ለማየት እንሞክራለን፡፡

☞

### 2.1.1. ህዝበኝነትና የፋሽዝም አዝማሚያ በምዕራቡ ዓለም

የምዕራቡ ካፒታሊዝምም አሁን የሚያራምደው ሊበራል ዴሞክራቲክ ፖለቲካ አሁን የገቡበት አጣብቂኝ በዋናነት ሥርዓቱ ካሉበት መዋቅራዊ ድክመቶች የሚነሱና እራሱ የፈጠራቸውን ቀውሶች ለመፍታት ያስችላሉ ተብለው የሚወሰዱ የእርምት እርምጃዎችም ሆኑ ኒዮ ሊበራሊዝምን የመሠሉ ፅንፈኛ አስተሳሰቦች ችግሩን ከመፍታት ይልቅ ወደ ተባባሰ መካረር ደረጃ የሚወስዱ ከመሆናቸው የሚመነጬ መሆኑን በጥቂቱ ለማየት ሞክረናል፡፡

የሊበራል ካፒታሊዝም በየወቅቱ ባመጣቸው ትሩፋቶች ተጠቅመናል ብለው የሚያምኑ ሰዎች ሳይቀሩ ከባህሪይው በመነጨ የሚያስከትላቸውን ማሕበራዊ ቀውሶች የሚያዩበት መነፅር አጠቃላይ ሥርዓቱን በመፈተሽ ላይ ያተኮረ ሳይሆን በስሜትና ስነ-ልቦና ላይ ያተኮረ ቁጣና ኩርፊያ ያመዘነበት ምላሽ የሚሆንበት ጊዜ ይበዛል፡፡ ለዚህም ነው የሥርዓቱን መዋቅራዊ ችግሮችና ክፍተቶች በሚገባ ተንትኖ ትሩፋቶቹን የሚያበረክት፣ አደጋዎቹን የሚያስቀር መፍትሔ ከመሻት ይልቅ የለየለት አጥፊ "እኛና" "ሌሎች" ላይ የተመሠረተ የፈጠራ ቅራኔ የበላይነት አግኝቶ የበለፀጉት ሃገራትን ወደ ተካረረ የፅንፍ ፖለቲካ ሲያስገባ የምናስተውለው፡፡

ከላይ በጨረፍታም ቢሆን ለማየት እንደተሞከረው በምዕራቡ ዓለም ካሁን በፊት የምናውቃቸው በዋናነት በኢኮኖሚ ፖሊሲ ትንታኔ ላይ የሚመሰረቱ የቀኝና የግራ አሰላለፍና ደረጃዎች ድሮ የነበራቸው መሠረታዊ ልዩነት ወደ መፍረሱ እየተጠጋ የፖለቲካ አሰላለፍ ከኢኮኖሚም ሆነ ከፖለቲካ ተጠቃሚነት ስሌት ወጥቶ በሰዎች ግልብ ስሜቶች ላይ ቁማር በሚጫወቱ ፖለቲከኞች የመፈክር ጨዋታ ሲሽከረከር በስፋት ይታያል፡ ፡የነዚህ አሰላለፍ አቀንቃኝ የሆኑ ፓርቲዎችም ጭምር ጊዜያዊ የምርጫ ውጤት ላይ በማማተር ከጽንፈኝነት ጋር ወደ መደራደርና መቋጫው የማይታወቅ ማፈግፈግ ውስጥ ገብተዋል፡፡

☞

በአሁኑ ሰዓት በበለፀጉት ሃገሮች ዘንድ ሊበራል ካፒታሊዝምን የገጠመው ቀውስ በዋነኝነት ኒዮ ሊበራሊዝም በፈጠረው የገበያ አክራሪነት መዋቅራዊ ትርምስ የተፈጠረ መሆኑ እየታወቀና ሳይንሳዊ መፍትሔውም ቀበቶን ጠበቅ አድርጎ መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት መሆኑ ግልጽ መሆን ሲገባው በብዙ ዘመነኛ ፖለቲከኞች ዘንድ ለተፈጠረው ቀውስ ተጠያቂ በመሆን ላይ ያሉት “ሌሎች” በየጊዜው ቁጥራቸው እየሰፋ፣ አናሳዎች፣ ግብረሰዶማውያን፣ የቻይና መስፋፋት፣ የሜክሲኮ እድገት፣ የመካከለኛው ምስራቅ፣ የአፍሪካና የላቲን አሜሪካ ስደተኞች፣ ወይም ደግሞ በደምሳሳው ያልሰሩበትን የሚበሉ “የድሆች ሃገራት ህዝቦች” ጭምር የችግሩ መንስኤዎች የሚደረጉበት ቅጣንባሩ የጠፋ ፖለቲካ ላይ ተደርሷል፡፡

በፈረንሳይ የማሪን ለፔን ቀኝ አክራሪ ፓርቲ ካሁን በፊት በአሁኗ መሪ አባት በጆንማሪለፔን ይመራ ከነበረበትና የዳርኝነት ሚና ብቻ ይጫወት ከነበረበት ሁኔታ ወጥቶ በቅርቡ በተደረገው ምርጫ ለሁለተኛው ዙር የፍፃሜ ውድድር የቀረበበት፤ ብዙዎች በፍርድ ቤት ውሳኔ ጭምር “ፋሽስት” የሚል መጠሪያ ያገኙት የፓርቲው መሪ የመራጮችን 35% ድምጽ ማግኘት የቻሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ የእሷ አለማሸነፍ እንደግልግል የሚቆጥሩ በርካታ ሰዎች መኖራቸው የሚታወቅ ቢሆንም ይህ ሁኔታ ግን የፈረንሳይን ፖለቲካ እስከ ወዲያኛው ከመለወጥ የሚያስቀረው አልነበረም፡፡ ፈረንሳይ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ትታወቅበት የነበረው ሁሉንም ዘሮችና ባህሎች በእኩል የማስተናገድ ዝና ከምኔውና በምን ምክንያት ተሸርሽሮ የህዝቧ ሃያ ምናምን ፐርሰንት የሆኑ ጥቁሮች፣ ኤስያውያንና ሙስሊሞች “ዋነኛ የፈረንሳይ ጠላቶች” ተደርገው በሚሊዮኖች ፈረንሳውያን ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው የሚቆጠሩበት ሁኔታ ሊፈጠር ቻለ? በአሁኑ ሰዓት ቀኝ አክራሪዋን ለፐንን አሸንፈው ወደ ስልጣን የወጡት ማክሮን በምርጫ ዘመቻቸው ወቅትም ሆነ ከድላቸው በኋላ ሁሉንም ወገን የሚያስደስት ከግራም ከቀኝም ያልሆነ ፖሊሲ ለማራመድ ለምን ተገደዱ? በተመሳሳይ መልኩ በቅርቡ በጀርመን በተደረገው ምርጫ ጥጉን ይዞ የቆየው የቀኝ አክራሪ ኤኤፍዲ ፓርቲ በርካታ የፓርላማ መቀመጫ መያዙና ትክክለኛ አቋም ይዞ ሲከራከር የነበረው ሲዩዲ በምርጫ ሂደት በአቋሞቹ መደራደር መጀመሩ ምንን ያሳያል? የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳት ተገቢ ይሆናል፡፡

☞

ለነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች የረባ መልስ ማግኘት ባይቻልም ስለ አንድ ነገር ግን እርግጠኛ መሆን ይቻላል፡፡ የማሪን ለፔንን ፅንፍ የያዘ ፖለቲካና የጀርመኑን ኤኤፍዲ ፓርቲ ወደ ተለመደው መንገድ (mainstream) ያመጣው የመራጮች ቁጣ ከየትኛውም አቅጣጫ ይመንጭ ከየትኛውም ወገን ይነሳ፣ የፈረንሳይና የጀርመን ካፒታሊዝምና የፈረንሳይና ጀርመን ዴሞክራሲ "ጥቅማችንን ለሌሎች አሳልፎ ሰጥቶብናል" የሚሉ ወገኖች የኩርፊያ ውጤት መሆኑን በፍፁም መጠራጠር አይቻልም፡፡ ምንም እንኳ የፈረንሳይ ቀኝ አክራሪ ናሽናል ፍሮንት ፓርቲም ሆነ የጀርመን ኦልተርኔቲቭ ፓርቲ ብዙዎች በበቂ ማስረጃም ጭምር በዘረኝነትና በነጭ የበላይነት የሚከሱት ቢሆንም ወ/ሮ ለፔን በሚመሩት እንቅስቃሴ ውስጥ ሁነኛ ድርሻ የነበራቸው በርካታ "ሃገራችን በስደተኞች ተወራለች፣ ይኽ መቆም አለበት" ብለው ከልባቸው የሚንጨረጨሩ ጥቁር ፈረንሳውያን ጭምር እንደነበሩበት የምርጫውን ዘመቻ በሚዲያ ለመከታተል የቻሉ ሁሉ የሚገነዘቡት እውነታ ነው፡፡ ጥቁሮች በእንጀራዬ መጡብኝ የሚል ነጭ ገበሬ፣ ባህላችን በአፍሪካውያን እየተበረዘ ነው ብሎ እስኪያልበው ከሚናደድ ከቀድሞ ቀኝ ተገዢ አፍሪካውያን የሚወለድ ሦስተኛ ትውልድ ጥቁር ፈረንሳዊ ጋር ባንድ ፅዋ እየጠጡ "ፈረንሳይ ትቅደም" የሚል መፈክር የሚያሰሙበትን ምክንያት ለመረዳት የተለመዱት የፖለቲካ አሰላለፍ መስፈርቶችን መተንተን ብቻውን በቂ እንዳልሆነ ግልፅ ነው፡፡

በኦስትሪያ፣ በኔዘርላንድስ፣በፖላንድ፣ በአሜሪካና በእንግሊዝ የታዩት የህዝብ እንቅስቃሴዎችና የምርጫ ውጤቶች የሚያሳዩን ይህንኑ የተለወጠ እውነታን ነው፡፡ በኦስትሪያና በኔዘርላንድስ ፅንፈኛውን አመለካከት የሚያራምዱት ወገኖች በጠባብ ልዩነትም ቢሆን ወደ ሥልጣን ለመውጣት ያደርጉት የነበረ ጉዞ ለጊዜውም መገታቱ በተወሰነ መልኩ ግልግል ነው ያሉ ባይጠፉም፣ የአውሮፖ ፖለቲካ እየደረሰበት ያለውን አደገኛ ጫፍ ግን እዚህ ግባ በሚባል መልኩ የሚለውጠው አይመስልም፡፡ በነዚህ ሁለት አገሮች በትክክል እንደሚታየው አሁን ለድል የበቁት የፖለቲካ ተቃናቃኞቻቸው የፅንፈኞቹን ፀረ-አውሮፖ ህብረት ፀረ-ስደተኛና አክራሪ ብሔርተኛ አቋም ሙሉ በሙሉ ከማውገዝ መቆጠብ ብቻ ሳይሆን ይልቁንም በስተመጨረሻ ለወጥ ባለ መልኩም ቢሆን ከሞላ ጎደል በትንሹ የተቀባባ የሚመስል ግን

☞

በመሰረቱ ተመሳሳይ የሆነ ዝንባሌ ለማሳየት መገደዳቸውና መደራደር መጀመራቸው አስተሳሰቡ የደረሰበትን ወሳኝ ደረጃ (critical mass) በግልፅ ያሳያል ተብሎ ሊወሰድ ይገባል፡፡

ከሁሉም በላይ ግን በዩናይትድ ኪንግደም የተደረገውና በአብዛኛው መራጭ ዘንድ ተደግፎ ለድል የበቃው ከአውሮፖ ህብረት የመውጣት ህዝበ ውሳኔና በፕሬዚዳንት ትራምፕ ወደ ሥልጣን መውጣት ላይ የታየው የፖለቲካ ትርምስ ውጥንቅጧ እየወጣ ያለችው ዓለም ወደየት እየተጓዘች እንዳለች የተሻለ ጠቋሚ ምልክቶች ያሉት ይመስላል፡፡

ዩናይትድ ኪንግደም ለበርካታ አስርት ዓመታት በአባልነት ከቆየችበት የአውሮፖ ሃገራት ስብስብ ለመውጣት የሚያስችል ህዝበ ውሳኔ እንዲደረግ የተወሰነው የመውጣቱን ሃሳብ ፈፅሞ በማይደግፉትና ህዝባቸው ላፍታም ቢሆን የመውጣትን ሃሳብ ሊደግፍ አይችልም የሚል ጠንካራ እምነት በነበራቸው የቀድሞው ወግ አጥባቂ ጠ/ሚኒስትር ዴቪድ ካሜሮን አማካኝነት ነበር፣ ሰውየው ከመነሻው በፖርቲያቸው አመራርም ሆነ በሚመሩት ካቢኔ ውስጥ ትልቅ ስፍራን ከያዙ ፀረ-አውሮፖ ህብረት አቋም ከሚያራምዱ ጓዶቻቸው የሚደረግባቸውን ጫና በህዝበ ውሳኔ “ልክ ለማስገባት” በማሰብ ነበር ሪፈረንደሙን የጠሩት፡፡ እሳቸው በለመዱት “ኖርማል” ፖለቲካዊ ስሌት ውስጥ ዜጎች የተወሰነ ቅሬታ ቢኖራቸውም የሚጠቅማቸውን “የአውሮፖ ህብረት ልጅ ከነ እጣቢው” የሚጥሉበት አጋጣሚ ይኖራል የሚል ግምት አልነበረም፡፡ በብሪግዚት ሪፈረንደም ወቅት አብላጫውን ድምፅ የሰጡት ወገኖች ከአውሮፖ ህብረት መውጣትን በሚመለከት የነበራቸው ግንዛቤ አንድና ያው አልነበረም ብቻ ሳይሆን ውጤቱ እንደታወቀ ወዲያውኑ ግልፅ እንደሆነው “ከአውሮፖ እንውጣ” ብለው ድምፅ ከሰጡት ውስጥ ቁጥራቸው የማይናቀው የውሳኔያቸውን ትክክለኛ ትርጉምም ሆነ የሚያስከትለውን ውጤት በሚመለከት እዚህ ግባ የሚባል ግንዛቤ አልነበራቸውም፡፡ እንዲያውም አንዳንዶች ጭራሹኑ ብሪግዚት የሚለው ሪፈረንደም በየአጋጣሚው በመንግስታቸው ላይ ይሰማቸው የነበረውን ቁጣ ለመግለጽ የሚያስችል መድረክ ብቻ አድርገው የወሰዱ እንደነበሩ በግልፅ ሲናገሩ ተደምጧል፡፡ በተለይም ደግሞ በዩናይትድ ኪንግደም የነበረው ሁሉንም ባህሎችና እምነቶች አክብሮ የመጓዝ መንግስታዊ አካሄድ (multiculturalism) ከገጠሙት በርካታ ፈተናዎች ጋር ተያይዞ የኒዮ ሊበራሊዝም መዋቅራዊ ቀውስ ያማረራቸው ዜጎች ቁጣቸውን ለመግለጽ

☞

አጋጣሚውን እንደተጠቀሙበት ይታመናል፡፡ ከስራ ማጣትና ከኑሮ መቃወስ ጋር በተያያዘ በዩናይትድ ኪንግደምም ቢሆን ለኢፍትሃዊ የሃብት ክፍፍሎች "ሌሎችን" ተጠያቂ የማድረጉ አዝማሚያ ሲከመር የመጣ ችግር መሆኑ ይታወቃል፡፡

ከዚህ አንፃር ሲታይ ከላይ ያነሳናቸው የዴሞግራፊ፣ የቴክኖሎጂና የአምራች ዘርፉ ተወዳዳሪነት መዳከምና ግሎባላይዜሽን አመጣብን ተብለው የሚወሰዱት ቀውሶች አሁን ተፈጥሮ ያለውን ሁኔታ በማምጣት ረገድ የነበራቸውን የማይናቅ ድርሻ ማየት ይቻላል፡፡

ከላይ በጠቀስነው መፅሐፍ ኘራንካጅ ሚሽራ በግልፅ እንደሚያስቀምጠው ካፒታሊዝም የፈጠራቸው የኑሮ መቃወሶች (disruptions) ለተወሰኑት መልካም ትሩፋቶችን ያስገኘ ለውጥ የማምጣታቸውን ያክል በለውጡ ምክንያት ኑሮአቸው የተቃወሰባቸው ወገኖች ቁጣቸውን የሚያበርዱት ቀውሱን በፈጠረው ሥርዓት ላይ ሳይሆን በዘር፣ በኃይማኖት፣ በጎሳና በሃገር ከነሱ በተለዩ "ሌሎች" ላይ ነው፡፡ የእንግሊዝ ከአውሮፖ ህብረት የመውጣት ውሳኔ ከ "ሌሎች" የመገላገል ፍላጎትና ቁጣ የወለደው ከመሆን በዘለለ ዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ ላለውም ሆነ የተቆጡ ወገኖች ለሚያዩት ችግር መዋቅራዊ መፍትሄ ለማምጣት የሚችል እንዳልሆነ ቢያንስ ቢያንስ ለታላቋ ብሪታንያ ከአውሮፖ ህብረት መውጣት ከማንም በላይ ዘመቻ ያደረጉት ሰዎች ያውቁታል፡፡ ለዚህም ነው የዚህ ዘመቻ ዋነኛ አቀንቃኝ የነበሩት የዩኪኘ መሪ ናይጀል ፋራጁም ሆኑ የወግ አጥባቂው ፖርቲ ከፍተኛ ባለሥልጣን ቦሪስ ጆንሰን ድህረ- ብሪግዚት ብሪታንያን የማስተዳደር ፍፁም ፍላጎት ያላሳዩት፡፡

የብሪግዚትን ሪፈረንደም ከአውሮፖ ህብረት ለመውጣት በመወሰን አብዛኛውን ድምፅ ከሰጡት ሰዎች መካከል ስደተኞች (የውጭ ተወላጆችን) ብሪታንያ እንዳይገቡ ማድረግ ብቸኛ መፍትሔ ነው ብለው ያመኑ ጥቂቶች እንዳልሆነ ግልፅ ነው፡፡ ይሁንና በዚህ ሪፈረንደም ውጤት መሰረት እንግሊዝ እንዳይገቡ የሚከለከሉት ቢያንስ ቢያንስ ዋናዎቹ አቀንቃኞች በፈለጉት መንገድ ከተሄደ-የሴኔጋል ወይም የኤርትራ ስደተኞች ሳይሆኑ "የፈረንሳይ ስደተኞች"ወይም ደግሞ "የስፔን ስደተኞች ናቸው፡፡"በአሁኑ ሰዓት ያለው የብሪታንያ ፖለቲከኞች መራኮት የሚያሳየውም አሁንም ☞

ቢሆን ስለገጠማቸው ችግር በጥልቅ ትንታኔ ላይ የተመሰረተ መፍትሔ ለመስጠት ዝግጁ አለመሆናቸውን ነው፡፡ ይባስ ብሎ ቀድሞውኑ የተቃወሙትን ከአውሮፓ ህብረት የመውጣት ውሳኔን ለማስፈፀም ደፋ ቀና የሚሉት ጠ/ሚኒስትር ቴሬዛ ሜይ በጠባብ ወንበርም ቢሆን በበላይነት የሚመሩትን ፓርላማ በትነው የተሻለ አብላጫ ድምፅ ያስገኝልኛል ያሉትን ምርጫ ጠርተው የነበራቸውንም ጠባብ አብላጫ ድምፅ አጥተው የለየለት ውጥረት ውስጥ የገቡበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ አሁንም ቢሆን በልሂቃኑና በአብዛኛው የተቆጣ ህዝብ መሃከል ያለው ልዩነት ከዚህ በሰፋ መልኩ ቢቀጥል የሚያስገርም አይሆንም፡፡ ዞሮ ዞሮ የጋራ ጥቅም ሳይሆን የሚጋሩት ቁጣ ያዋሃዳቸው ግን በተግባር ያልተዋሃዱ ኃይሎችን እውነተኛ የልብ ትርታ ለማዳመጥ በሚያስችል መልኩ የችግርን ትክክለኛ ምንጭና ባህሪይ ለመረዳት ጥረት እስካልተደረገ ድረስ ትርምሱ ለወደፊቱም ከመቀጠል እንደማይቆም ለመናገር ነቢይ መሆን አይጠይቅም፡፡

በዶናልድ ትራምፕ ፍፁም ያልተገመተ ፕሬዝዳንት ሆኖ መመረጥ የተጠናቀቀው የ2016 የአሜሪካ ምርጫ ሊበራሊዝም በአሁኑ ሰዓት ገብቶበት ስላለው ቀውስ ከሌሎች የተሻለ ግንዛቤ ይሰጣል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከዚህ በላይ ግን የዓለም አቀፍ ፖለቲካ ትኩሳትን በማናርም ሆነ በማቀዝቀዝ ከማንም ሃገር በላይ ትልቁን ሚና ስትጫወት የመጣችው አሜሪካ አሁን ያለችበትን ትርምስና አመጣጡን መረዳት ከብዙ ነገር ሊያድነን ስለሚችል ትንሽ ዘርዘር አድርጎ ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

የዶናልድ ትራምፕ መመረጥ የብዙ የፖለቲካ ተንታኞችን ግምት ያዛባ፣ የአሜሪካ የፖለቲካ ባህልን ትርምስ ውስጥ የከተተ፣ በቀኝና ግራ ዘመም ኃይሎች መካከል የነበረን አሰላለፍ እጅጉን ያመሰቃቀለ፣ ከምንም በላይ ግን ብዙዎች ወገኖች እንደሚስማሙበት "ከእውነት ጋር በኩራት መላተምን" ልዩ መለያው ያደረገ ክስተት ሆኖ እውን ከሆነ መንፈቅ አስቆጥሯል፡፡ ዶናልድ ትራምፕ በርግጥም የተለመደ የአሜሪካ ፕሬዚዳንታዊ ተወዳዳሪም ሆነ የምናውቀው ዓይነት ፕሬዝዳንትም አይደለም፡፡ የአሜሪካን ያረጀ ፖለቲካና የዋሽንግተን ዲሲን የልሂቃን አድራጊ ፈጣሪነት ማስቆምን ዋነኛ የምርጫ መፈክሩ አድርጎ የተነሳው ዶናልድ ትራምፕ በአንድ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ዘመን ለመፈፀም በጣም የሚከብዱ በርካታ ሥራዎችን ለማከናወን የገባውን

☞

ቃል ለመተግበር ባለ በሌለ አቅሙ እየተንቀሳቀሰ እንደሆነ እየገለፀ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ለግምት ያስቸገረ ተገለባባጭነት እያሳየ ከመምጣቱ በዘለለ እዚህ ግባ የሚባል ተጨባጭ ውጤት አስመዝግቧል ተብሎ አይወሰድም፡፡

የትራምኘ ፖለቲካ ምን ይመስላል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ከመሞከራችን በፊት ኘሬዚዳንቱ የብዙዎቹን የቀኝና የግራ ተንታኞችና የሚዲያ ነቢያትን ግምት አዛብተው ለመመረጥ የቻሉበትን ሂደት ያነሷቸውን ጉዳዮች ማንሳቱ የአሜሪካ ሊበራል ዴሞክራቲክ ሥርዓትና ሊበራል ካፒታሊዝም የገቡበትን አጣብቂኝ ለማየት ያግዘናል፡፡ የምርጫ ተፎካካሪው ትራምኘ ዋነኛ መፈክር "አሜሪካን እንደገና ወደ ትልቅነቷ መመለስ" የሚል ነው፡፡

በኘሬዝዳንት ትራምኘ እምነት አሜሪካ በኢኮኖሚም ሆነ በፖለቲካ የነበራት ዝና ተሸርሽሮ የነቻይና መጫወቻ ሆናለች፤ የአሜሪካ ማኑፋክቸሪንግ ሥራዎች በሙሉ ወደ ቻይናና ሜክሲኮ ተጉዘዋል፤ የኔቶም ሆነ የሌሎች አጋሮችን ሰላም እናስጠብቃለን እያልን ወጭ በማይጋሩ ወዳጆች እየተበዘበዝን ኖረናል ወ.ዘ.ተ.. የሚሉ በብዙ አሜሪካውያን ዘንድ ብዙ ድጋፍ ያስገኘላቸውን አቋሞች ሲያራምዱ ከርመዋል፡፡ የቀኝ አክራሪ ፖለቲከኞች ባልተለመደ መልኩ "እስላም የሁከት ሃይማኖት ነው" የሚሉ ፅንፈኛ አመለካከቶችን ሳይቀር በይፋ እያራመዱ የብዙ በድህነትና በስጋት ቆፈን የተሸበቡ አሜሪካውያንን ግልብ ስሜት ማነሳሳት የተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በዚሁ ሁሉ ሂደት ውስጥ እጅግ አስገራሚ የነበረው በአሜሪካ ፖለቲካ ታሪክ ውስጥ የቀኝና የግራ ኃይሎችን አሰላለፍ የሚወስኑት ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ትርጉም አጥተው በትራምኘ በአብዛኛው ለሃብታሞች ባደላ ፖሊሲ የሚጎዱ ነጭ ድሆች አብዛኛውን ድምፃቸውን ለትራምኘ የሰጡበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ከጠመንጃ የመያዝ መብት፣ የግብረሰዶማውያን መብት፣ በአየር ንብረት፣ በባህልና በአሜሪካዊ እሴቶች ዙሪያ የሚደረገው የመስመር ልዩነት አሜሪካ ውስጥ በተከታታይ ምርጫዎች እየጎላ እንደመጣ የሚታወቅ ቢሆንም፣ እንደዚህ ዓመቱ ምርጫ ባህልና መደባዊ ያልሆኑ ጉዳዮች የምርጫውን ውጤት በመወሰን ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉበት ጊዜ አለ ተብሎ አይታመንም፡፡ ይሁንና የሁሉም ነገር ማጠንጠኛ ኒዮ ሊበራሊዝም የፈጠራቸው መዋቅራዊ ችግሮችና

☞

እሱን ተከትሎ የመጣው ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡በኘሬዝዳንት ትራምኘ እምነት ከልባቸውም ይሁን ለይስሙላ የአየር ንብረት ለውጥ በሚባል ተረት ተረት የአሜሪካ ንግድና አምራች ተቋማት ተወዳዳሪነታቸውን ማጣት ስለሌለባቸው ከአየር ንብረት ጋር ተያይዘው የሚመጡ ግዴታዎችን መቀበል ተገቢ አይሆንም፡፡ በድንጋይ ከሰል ላይ ተጥሎ የነበረን ቁጥጥር ከማንሳት ጀምሮ፣ የባህሮችና ምንጮችን ንፅህና ለመጠበቅ ተብሎ የወጡ አዋጆችን እስከ መሻር የደረሱት ትራምኘ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት ለቀው እስከመውጣት ደርሰዋል፡፡

ራሳቸው ትራምኘና ቤተሰቦቻቸው ሥራዎቻቸውን ወደ ቻይናና ሌሎችም የተሻለ አትራፊ የሚባሉ ሃገራት እንደሚወስዱ ቢታወቅም የአሜሪካን የማኑፋክቸሪንግ ሥራዎች ከቻይናና ከሜክሲኮ እመልሳለሁ በሚል ዘርፉ በገጠመው መዋቅራዊ ችግር ምክንያት ለድህነትና ለሥራ አጥነት የተዳረጉ በአስር ሚልዮኖች የሚቆጠሩ ከፔንሲልቫንያ እስከ ዊስኮንሲን ያሉ ነጭ መራጮችን ድምፅ ለማግኘት በቅተዋል፡፡ ለድህነታቸው ኒዮ ሊበራሊዝም ያመጣውን ትርምስ ሳይሆን ጥቁሮችን፣ ድሃ ሜክሲኮውያንና ላቲኖ ስደተኞችንና በሰላም ለፍተው የሚያድሩ የመካከለኛው ምስራቅ ዝርያ ያላቸው አሜሪካውያንን ጭምር ተጠያቂ የሚያደርጉ የተወናበዱ መራጮች ለዶናልድ ትራምኘ መፈክር በቀላሉ የተጋለጡበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

በዶናልድ ትራምኘ ዘመቻ ወቅትም ሆነ ኘሬዚዳንት ከሆኑ በኋላ ትልቅ ጥቃት ከተሰነዘረባቸው ኢላማዎች መካከል ግሎባላይዜሽን እንደ ማዕቀፍ፣ የተባበሩት መንግስታትና ኔቶን ጨምሮ ሌሎች የአሜሪካን ታላቅነት የተገዳደሩ የተባሉ በርካታ ተቋማት ይገኙበታል፡፡ በእያንዳንዱ የአሜሪካ ግንኙነት ውስጥ ግልብ የሰጥቶ መቀበልን (Transactional) ስሌት ማስገባት እንዳለባቸው የሚያምኑት ኘሬዝዳንት ትራምኘ ይኸው መጥቻለሁ የሚሉት አጀንዳ ከትብብር ይልቅ፣ መፋጠጥን፤ ከህብረት ይልቅ በተናጠል መሄድን በአጠቃላይ በግሎባላይዜሽን ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ ከመክበር ይልቅ በማንኛውም ስሌት "አሜሪካ ማስቀደምን" ዋነኛ መርሁ ያደረገ የመነጠል (Isolationist) አዝማሚያ በስፋት ይታይበታል፡፡

በአሜሪካ "ረስት ቤልት" እየተባለ በሚታወቀው አካባቢ የተዘጉት በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ፋብሪካዎችና በፋብሪካዎቹ መዘጋት ምክንያት

☞

ወደ ቻይናና ሜክሲኮ የተጋዙት ሥራዎች በምንም ተዓምር ተመልሰው ወደ አሜሪካ ሊመጡ እንደማይችሉ የትራምፕም ሆነ የአማካሪዎቻቸው ልቦና ያጣዋል ተብሎ አይገመትም፡፡ በስደተኞች የተመሰረተችው አሜሪካ ፀረ ስደተኛ አቋም አራምዳ ታላቅነቷን ማስመለስ ይቻላታል የሚል የዋህ እምነትም በብዙዎች ዘንድ አለ ተብሎ አይገመትም፡፡ በርካሽ የነዳጅ ምርት መጥለቅለቅ (Fracking) ተወዳዳሪነቱን ያጣው የድንጋይ ከሰል ተመልሶ ጥቅም ላይ እንዲውል ትራምፕ በማበረታታቸውም በድህነት አረንቋ ውስጥ መዘፈቅ የጀመሩት የአፓላቺያን ነዋሪዎችና የዌስት ቨርጂኒያ ላብአደሮች ኑሮ በፍፁም ሊሻሻል አይችልም፡፡ የአሜሪካ የፀጥታ ችግሮችም ሆኑ የሽብር ስጋቶች ሙሉውን የአረብ ዓለም ወይም እስልምናን እንደ ኃይማኖት በማውገዝ ሊፈቱ እንደማይችሉም የተለየ ዕውቀት አይጠይቅም፡፡ በአጠቃላይ ፕሬዚዳንት ትራምፕ በምርጫ ዘመቻቸውም ሆነ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ ያራመዷቸው አቋሞች ሊያመጡት ከሚችሉት ውጤት አንፃር እዚህ ግባ የሚባል የህዝብ ድጋፍ ያስገኛሉ ተብሎ አይጠበቅም ነበር፡፡ የሆነው ግን ከዚህ የተለየ ነው፡፡ መዋቅራዊ መፍትሔ የሚጠይቁ ከባድ ችግሮች ቀላል መፍትሔዎችን በመፈክር መልክ ማቅረብ ቢያንስ የህዝበኝነት ግፋ ሲል ደግሞ የጽንፈኝነትን ዳዴ መጀመርን ሊያመለክቱ ይችላሉ በማለት ብዙዎች መሞገት ከጀመሩ ውለው አድረዋል፡፡ ለውስብስብ ችግሮች ቀላል መልሶችን መስጠት የአምባገነንነት አጭር ወሰነ ትርጉም ነው ይላል አንድ ፀሐፊ፡፡ "የምንበላውን አጣን" ብለው ሰልፍ ለወጡ የፈረንሳይ ድሆች "ለምን ኬክ አይበሉም" ብላ መልስ ሰጥታለች እንደምትባለው የሉዊ አስራ ስድስተኛ ባለቤት ማርያአንቶኔት መዋቅራዊ መፍትሔ ለሚጠይቁ ጉዳዮች መፈክሮችን እንደ ምላሽ ማቅረብ መጨውን የሚያመለክት ተደርጎ ቢወሰድ የሚያስደንቅ አይሆንም፡፡

በእርግጥም በአውሮፓም ሆነ በአሜሪካ እየታዩ ያሉት ክስተቶች የሚያመለክቱት ዴሞክራሲና ተቋማቱ እንዲሁም ሊበራል ካፒታሊዝም እንደ ሥርዓት ወደ ተከላካይነት የገቡበትና ህዝበኝነትና ምናልባትም ጽንፈኝነት የሚያቆጠቁጡበት ዕድል መፈጠር የጀመረበት እንደሆነ ነው፡፡

በአሜሪካም ሆነ በአውሮፓ የቀኝ አክራሪ ፓርቲዎች በሥልጣን ላይ ለረዥም ዘመናት የነበሩ ፓርቲዎችንና ተቋማትን ለሥጋት የዳረገ

☞

እንቅስቃሴ ማድረግ ከጀመሩ ወዲህ በበርካታ ተንታኞች ዘንድ ህዝበኝነትና ፋሺዝም አንደኛው እንደሆኑ ተደርገው የሚነሱበት ሁኔታ በስፋት ይስተዋላል፡፡ እንደሚታወቀው ሁሉ ፋሺዝም በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መካከል በአውሮፖ ውስጥ የተከሰቱ የቀኝ አክራሪ ካፒታሊዝም ስርነቀል እንቅስቃሴ ነው፡፡ ፋሽዝም እንዲከሰት ምክንያት የሆኑ በርካታ ነገሮች ቢኖሩም ዋነኛው መንስኤው በዚህ ወቅት የነበሩት ፖለቲከኞችና የፖለቲካ ተቋማት ህብረተሰባቸው የገጠመውን ዘርፈ ብዙ ቀውስ ለመፍታት የሚያስችል ቁመና ላይ አለመገኘታቸው እንደሆነ ይታመናል፡፡

በመጀመሪያ የዓለም ጦርነት ወቅት እንደታየው በጦርነቱ የተሸነፉት ጀርመን፣ ጣልያንና ኦስትሪያ ከደረሰባቸው ከፍተኛ የኢኮኖሚ ድቀትና ቀውስ በተጨማሪ ከጦር ግንባር በሽንፈት የተመለሱ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ወታደሮችን ሥራ የማስያዝ ትልቅ ፈተናን መጋፈጥ ግድ ሆኖባቸው ነበር፡፡ ይሁንና በወቅቱ የነበሩት የዴሞክራሲ ተቋማት ይህንን ግዙፍ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውስ በወጉ ለማስተናገድ የሚያስችል አቅምም ሆነ ዝግጁነቱ አልነበራቸውም፡፡ ይህም ሁኔታ ያጋጠሙት ችግሮችና ይታዩ የነበሩ ቀውሶች በተለመደው የቁጥቁጥ ምላሽ መፍትሄ ሊሰጣቸው የሚችሉ ስላልነበሩ ለገጠሙት ችግሮች ሁሉ ተዓምራዊ መልስ መስጠት እንችላለን ብለው የህብረተሰቡን ግልብ ስሜት በመኮርኮር ላይ ያተኮረ እንቅስቃሴ የጀመሩ ቀኝ አክራሪ ብሔርተኞች በስፋት ብቅ ብቅ የሚሉበትን ሁኔታ ተፈጠረ፡፡

በዚህ መልኩ የተጀመረው እንቅስቃሴ ከመነሻው ሰፊ የህዝብ ድጋፍ የነበረው ባይሆንም ከቀውሶች መባባስ ጋር ተያይዞ "በውጭ ኃይሎች ሴራ ጭምር አደጋ ላይ ወድቋል" የሚሉትን ብሔራዊ ክብር ለማስመለስና የተፈጠረውን ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ለመፍታት ተዓምራዊ መፍትሔ አለን የሚሉ አክራሪ ብሔርተኛ ፖለቲከኞችና ፖርቲዎች በሂደት የአብዛኛውን መራጭ ቀልብ ለመሳብና የስልጣንን እርካብ ለመቆናጠጥ የቻሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ችሏል፡፡

በኢጣልያና በጀርመን እንደታየው ምንም እንኳን የዴሞክራሲ ተቋማት ይነስም ይብዛም ለበርካታ አስርት ዓመታት ሥራ ላይ ውለው

☞

የነበሩ ቢሆንም ከቀውሶች መባባስ ጋር ተያይዞ የመጣውን የፋሽዝምን የአብዮታዊ ለውጥ ጥያቄን በወጉ ለመግራት የሚያስችል ጥንካሬም ሆነ ልምዱ አልነበራቸውም፡፡ ለዚህም ነው መሶሎኒም ሆነ ሂትለር ወደ ሥልጣን "ዴሞክራሲያዊ" ሊባል በሚችል መንገድ ከመጡ በኋላ ተግባራዊ ማድረግ የቻሉት ሥርዓት ፍፁም አምባገነናዊና ሚሊዮኖችን ለሞትና እንግልት ከመዳረግ አልፎ ሁለተኛው የዓለም ጦርነትን ቀስቅሶ ለአጠቃላይ ዓለማዊ ውድመት እውን መሆን ምክንያት ሊሆን የቻለው፡፡

ስለዚህ የፋሽዚም ዓይነተኛ ባህሪይ ዜጎች በዴሞክራሲ ተቋማት ላይ ያላቸውን እምነት ከመሰረቱ ከመሸርሸሩና አጠቃላይ እምነታቸውን አንዳች ተዓምራዊ መፍትሔ ለችግሮቻችን ያመጡልኛል ብለው በሚከተሏቸው አክራሪ ብሔርተኛ ፖለቲከኞችና ፖርቲዎች ላይ የሚያደርጉ ከመሆኑ ጋር ይያያዛል፡፡ ፋሽስቶች ከሌሎች ህዝበኛ ፖለቲከኞች የሚለያቸው ጉዳይ ቢኖር ፋሽስቶች የማታ ማታ ራሱን ዴሞክራሲንና ተቋማቱን በመቅበር ትግላቸው የቀኝ አክራሪ አምባገነናዊ ሥርዓት በመመሥረት የሚጠናቀቅ ሲሆን ህዝበኛ ፖለቲከኞች ግን ዴሞክራሲና ተቋማቱ ያለባቸውን ድክመቶች በማረም የተሻለ ሁኔታን እንፈጥራለን በሚል የሚንቀሳቀሱ መሆኑ ነው፡፡ ዞሮ ዞሮ በህዝበኛ መንገድ የሚመረጡ ፖለቲከኞች እናመጣዋለን የሚሉት ተዓምራዊ መፍትሔ ባሰቡት ፍጥነት ሳይመጣ ሲቀር ወደ ለየለት ፋሽዝም ለማምራት የሚያስችል አክራሪ ብሔርተኛ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚገቡበት ዕድል ዝግ አይደለም፡፡

በአሁኑ ሰዓት በአብዛኛው አውሮፖ በተለይም በፈረንሳይ የምናየው ሁኔታ የህዝበኝነት ሁነኛ ምልክቶች የሚታዩበት ሆኖ ወደ ፋሽዝም ሊያድግ የመቻልና ያለመቻሉ ጉዳይ በየሃገራቱ ባሉት የዲሞክራሲ ተቋማት ጥንካሬ ላይ የሚመሰረት ነው የሚሆነው፡፡በተጠናከረ የህዝበኝነት ዘመቻ የመንግስት ሥልጣንን ለመያዝ ያለውን ሰፊ እድል በአሜሪካ እንዳየነው ዝግ እንዳልሆነ ግልፅ ነው፡፡ በሌሎች ሃገራትም ቢሆን ከሞላ ጎደል ለሥልጣን አደገኛ በሆነ ደረጃ መቅረብ የቻለበትና የፈረንሳይና የኔዘርላንድስ ምርጫ በከፊልም ቢሆን የጀርመን ምርጫ እንደሚያሳየን ያሸነፉት ሰዎችም ቢሆኑ ያሸነፏቸውን ሰዎች አስተሳሰብ በተበረዘ መልክም ቢሆን ለመቀበል የተገደዱበት ሁኔታ እንደነበር አይተናል፡፡

☞

የተጋጋሉ የህዝበኝነት እንቅስቃሴዎች ጭልጥ ወዳለ ፋሽስታዊ ስርዓት እንዳይሄዱ በማድረግ ረገድ ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት የመኖራቸውን ፋይዳ በ1920ዎቹና ሰላሳዎቹ በአውሮፖና በአሜሪካ የተከሰተውን የፖለቲካ ትኩሳት በማየት መረዳት ይቻላል፡፡ በወቅቱ ዘግሬት ዲፕሬሽን የተባለው የኢኮኖሚ ቀውስ በጀርመንና በጣልያን ብቻ ሳይሆን በአሜሪካም በስፋት የታየበት ወቅት እንደነበር ይታወቃል፡፡ ይሁንና በወቅቱ የነበረው የፋሽዝም አዝማሚያን ተቋቁመው ስልጣን ላይ የወጡ ፖርቲዎች የህዝባቸውን ችግር በመፍታት በስተመጨረሻም ለዌልፌር ስቴት መፈጠር ምክንያት ሊሆን የቻለን እርምጃ መውሰድ ችለው ሃገራቸውን ወደ ተረጋጋ ዴሞክራሲ ጎዳና ያስቀጠሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ችሏል፡፡ ይሁንና የዴሞክራሲ ተቋማቱ ጥንካሬ እዚህ ግባ የሚባል ባልሆነባቸው የአውሮፖ ሃገራት ተመሳሳይ ቀውስና ቀውሱን ተከትሎ የመጣው የህዝበኝነት አዝማሚያ ወደ ለየለት ፋሽዝም ያደገበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

የጠንካራ ዴሞክራሲ ተቋማት መኖር አለመኖር ጉዳይ አሁን ባለንበት ሁኔታም የትራምፕ ህዝበኛ ፖለቲካ ወደ ለየለት ፋሽዝም እንዲያድግም ሆነ እንዳያድግ ብቸኛ ዋስትና የሚሆነውም ለዚህ ነው፡፡ የአሜሪካ የዴሞክራሲ ተቋማት ሊበራሊዝም በአሁኑ ሰዓት ገጥሞት ያለውን መዋቅራዊ ቀውስ ለመፍታት የሚያስችል ጥንካሬ ይዘው እስከቀጠሉ ድረስ የፕሬዚዳንት ትራምፕ ህዝበኛ ፖለቲካ የረዥም ጊዜ ቆይታ ይኖረዋል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ሼሪ በርማን እንደምትሞግተው “የዴሞክራሲ ትልቁ ጠንካራ ጎን ህዝቦች በአንድ የምርጫ ሞቅታ ወቅት በህዝበኛ ፖለቲከኞች ቅስቀሳ ተነሳስተው የፈፀሙትን ስህተት ለማረም የሚያስችል ዕድል በየአራት አመቱ መፍጠር መቻሉ” ነው፡፡

ለማጠቃለል ያክል ህዝበኝነት ዴሞክራሲ ችግር ውስጥ መግባት እንደጀመረ ከሚያሳዩ ምልክቶች አንዱ ሲሆን ፋሽዝም ዴሞክራሲ እንደ ሥርዓት በከባድ ቀውስ ላይ መውደቁን የሚያሳይ ክስተት ነው፡፡ በአንድ ወይም በሁለት የምርጫ ዘመን የሚታይ የህዝበኝነት አዝማሚያ በዴሞክራሲ ተቋማቱ የውስጥ ጥንካሬ አማካኝነት ወደ ትክክለኛ ይዞታው የሚመለስበት ዕድል ካልተፈጠረና ለህዝብ ጥያቄዎች በቂና ጤናማ ☞

ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ስራዎች ካልተሰሩ ዞሮ ዞሮ ቀውስን እየወለደ ህዝብኝነት ወደ ለየለት ፋሽዝም የማይገባበት ምክንያት እንደማይኖር ታሪክ በቂ ምስክርነት ስለሚሰጠን በዚህ ረገድ ያለውን ሥጋት በትክክል መረዳት ያስፈልጋል፡፡

አሁን በአውሮፖም ሆነ በአሜሪካ እየታየ ያለው የህዝበኝነት አዝማሚያ የየሃገራቱን የውስጥ ፖለቲካ ለእስከ ወዲያኛው እየቀየረው ስለመሆኑ በርካታ ምሳሌዎችን አንስቶ መነጋገር ይቻላል፡፡ ፋሽዝም ዓለምን ለአጥፊ ውድመት በዳረገበት የአንደኛና ሁለተኛው ዓለም ጦርነት ወቅትም ሆነ በአሁኑ ዘመን በአውሮፖና አሜሪካ እየታዩ ያሉ ምልክቶች ቢያንስ በሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ተመሣሣይነት ይስተዋልባቸዋል፡፡ በሁለቱም አጋጣሚዎች ለህዝበኝነትም ሆነ ለለየለት ፋሽዝም መከሰት ምክንያት የሆነው ለከት አልባ ሊበራል ካፒታሊዝም ሄዶ ሄዶ በሚገጥመው ውስጣዊ ቀውስ ምክንያት ኑሮአቸው በከፍተኛ ደረጃ የተመሰቃቀለባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በከፍተኛ ደረጃ ተስፋ መቁረጥ (frustration) ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታ በስፋት የሚታይ መሆኑ አንዱ ገፅታ ነው፡፡ ሊበራል ካፒታሊዝም የሚፈጥረው እጅግ ሰፊ የፍትሐዊ ተጠቃሚነት ክፍተት መንግስታት ለችግሮች መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችል ቁርጠኝነቱም ሆነ አቅማቸው በከፍተኛ ደረጃ እየተዳከመ በሚመጣበት ወቅት የህብረተሰቡን ቁጣ በሌላ መልኩ ለማዳፈን የሚያስችል ዕድሉም የዚያኑ ያክል የሚዳከምበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ በየሃገራቱ ባሉት የዴሞክራሲ ተቋማት የሚከናወኑ ምርጫዎች፣ የየሃገራቱ የፖለቲካም ሆነ የፍትህ ተቋማት ተስፋ የቆረጠውን የህብረተሰብ ክፍል ጥያቄዎች አዎንታዊ በሆነ መንገድ ከመመለስ ይልቅ የጥቂቶች ብቻ ጠበቃ መስለው የሚታዩበት ወይም ደግሞ በተግባር የጥቂቶች ጥቅም ማስከበሪያ የአድልዎ ተቋማት የሚሆኑበት ሁኔታ ይከሰታል፡፡ ምርጫዎች እጅግ የናጠጡ ባለፀጋዎች አብዛኛውን መራጭ በአጃቢነት እያሳተፉ ለሥልጣን ሽሚያ የሚራኮቱባቸው ሰርከሶች እየሆኑ፣ ፍርድ ቤቶች ባለፀጋው መደብ ለዘመናት ያካበተውን ግዙፍ ኃብት ባለቤትነት በድሆች እንዳይነጠቅ ሽንጣቸውን ገትረው የሚሟገቱ አገልጋዮች ተደርገው እየተቆጠሩ አብዛኛው ህዝብ በነዚህ ተቋማት ላይ ያለው እምነት በየጊዜው እየተሸረሸረ መሄዱ አይቀሬ ነው።

☞

በእንደዚህ ዓይነቱ የተካረረ ከባቢያዊ ሁኔታ ውስጥ የሚከሰት ሌላ ጉዳይም አለ። ይኸውም በዘልማድ የህዝብን ጥያቄና ቅሬታ የመመለሥ ተስፋ የሚጣልባቸው የዴሞክራሲና የፍትህም ሆነ መሠል ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ተቋማት ላይ ህዝቡ የሚኖረው ዕምነት እየተሸረሸረ በመጣበት ሁኔታ ለተነሱ የህዝብ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ብቸኛ ባለመልሶቹ እኛ ነን ብለው ምለው የሚገዘቱ ማንኛውንም ስሜት የሚኮረኩር መፈክር እየደጋገሙ ዕድሉ ብቻ ከተሰጠን ተዓምር ሰርተን ከመከራ እናወጣችሁዋለን ብለው ተስፋ የቆረጠን መራጭ ህዝብ የሚያማልሉ ህዝበኛ ፖለቲከኞች የመከሰታቸው ጉዳይ ነው። በእንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ውስጥ ነው ብዙዎቹ የምዕራቡ ዓለም ህዝበኛ መሪዎች ብቅብቅ ማለት የሚጀምሩት።

## 2.1.2. የህዝበኛ አመለካከት መነሻዎች

ይህ ዘመን የሰው ልጆች አቅም ከዚህ ቀደም ባልታየ ደረጃ መሻሻል ያሳየበት እና ቁሳዊ ሐብት የተትረፈረፈበት ዘመን ቢሆንም፤ በአንጻሩ በጣም አሳሳቢ የሆነ ጊዜ ነው፡፡ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ወዲህ ባሉት ዓመታት ቅርጽ የያዘው እና ከሰባት አስርት ዓመታት በላይ ፀንቶ የቆየው የዓለም አቀፋዊ ስርዓት መሰረት የሆኑት እሴቶች እየተናዱ ነው፡፡ የመጨረሻው ሰው በሞት ከዓለም እስኪሰናበት ድረስ ‹‹ታሪክ መጨረሻ›› እንደማይኖረው እያየን ነው፡፡ ለዓለም ዋልታ እና ማገር ሆነው የቆዩት የፖለቲካ አስተሳሰቦች ኪሳራ እያስተናገዱ ነው፡፡ ዓለምን ከውድቀት የሚታደግ አዲስ የጠራ የፖለቲካል-ኢኮኖሚ አስተሳሰብ እንጂ ጥገና ለውጥ ሊያመጣ እንደማይችል በግልጽ እየታየ ነው፡፡ የምዕራቡ ዓለም የእጅ ሥራ የሆነው እና በኃያል ምዕራባዊ መንግሥታት ፈቃድ ሲዘወር የቆየው ዓለም አቀፋዊ ስርዓት ለረጅም ጊዜ እየተንገራገጨ መጥቶ አሁን ትንፋሹ እያጠረው ነው፡፡ የምዕራቡ ዓለም በጥገና ሊሻገረው ከማይችለው እና እየተጠናከረ ከመጣ የፀረ-ሊበራል አስተሳሰብ ጋር ተፋጥጦ መቆሙን እያየን ነው፡፡

ኤሪክ ሆብስባውም (Eric Hobsbawm) የተባለ አንድ ፀሐፊ፤ ‹‹ዓለም በ1980ዎቹ እና 1990ዎቹ ያስተናገደችው ውድቀት፤ እንደ ሂትለር ፕሮጀክት፣ እንደ ስታሊን ሸብር አረመኔያዊ ተብሎ ሊፈረጅ በሚችል የውሳኔ ሰጪዎች ተግባር የተነሳ የተከሰተ ውድቀት አይደለም፡፡ የኒዩክለር ጦር መሣሪያ እሽቅድድምን ተገቢ ሥራ አድርጎ ለማቅረብ እንደመሞከር ☞

እና እንደ ማኦ የባህል አብዮት ባለ የእብደት ሥራ የተከሰተ ውድቀትም አይደለም፡፡ይልቅስ፣ ውሳኔ ሰጪዎች ከእነሱ እና ከእኛ ቁጥጥር ያመለጠውን ዓለም ለመመለስ ሊያደርጉ የሚችሉት ነገር ግራ ገብቷቸው፣ ከ1950ዎቹ አንስቶ በተፈጠረው ፈጣን ማህበረሰባዊ እና ኢኮኖሚያዊ ትራንስፎርሜሽን ሳቢያ የሰዎች ማህበረሰባዊ ህይወት ደንቦች ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ በመመሳቀላቸው እና በመዛነፋቸው የተከሰተ ውድቀት ነው›› ይላል፡፡

ይህን ችግር የተመለከተው ጆርጅ ሞንቢዮት ‹‹How did we get in to this mess›› (ከዚህ ዓይነት ምስቅልቅል ውስጥ ልንዘፈቅ የቻልነው እንዴት ነው?) ሲል በጻፈውና በ2016 ዓ.ም ባሳተመው መጽሐፉ የምዕራቡን ዓለም እያስጨነቀ ያለውን ችግር ለመፈተሽ ይሞክራል፡፡ ሆኖም ይህ ችግር የምዕራቡን ዓለም ብቻ የሚመለከት ችግር አይደለም፡፡ ከዚያ ውጪ ባለው የዓለም ክፍልም ፀረ- ሊበራል (illiberal) ሊባሉ የሚችሉ ኃይሎች እግር ተክለው እየቆሙ መሆናቸውን ምዕራባውያኑ ምሁራን እየገለፁ ነው፡፡

በአጭሩ፣ የምዕራቡ ዓለም ማህበረሰብ ከውስጡ በፈለቁ የሊበራል-ዴሞክራሲ ዋልታና ማገር የሆኑ እሴቶችን እየሸረሸሩ፣ የስርዓቱን ምሰሶዎች እየነቀነቁ በሚገኙ ህዝበኛ ንቅናቄዎች በመበራከታቸው ጭንቀት ውስጥ ገብቷል፡፡ በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ እንዲሉ፣ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚገኙ ፀረ-ሊበራል አገዛዞችም ጫና እያሳደሩበት ነው፡፡ የምዕራቡ ዓለም ህብረተሰብ በሊበራል ዴሞክራሲ ስርዓት ላይ የነበረው መተማመን እየተሸረሸረ ነው፡፡ ለሰባት አስርት ዓመታት የተጓዘው ዓለም አቀፋዊ ስርዓት እንዲዳከም የሚሹ የውጭ ኃይሎችም የተለያዩ ተግዳሮቶችን እንደደቀኑበት ምሁራን ይናገራሉ፡፡

ጆርጅ ሞንቢዮት፣ አሁን እያስተናገድነው ያለው ቀውስ፣ ከ60 ዓመታት በፊት ከተደረገ አንድ ስብሰባ ተወልዶ፣ በረጅም ጊዜ ሂደት አልፎ የተከሰተ ቀውስ መሆኑን ይገልጻል፡፡ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በዩናይትድ ኪንግደም ሸማቾች ላይ የተከማቸው ዕዳ፣ ከሐገሪቱ ጠቅላላ ሐገራዊ ምርት መጠን ልቆ ሄዷል፡፡ ይህ ዕዳ 1 ነጥብ 35 ትሪሊዮን ፓውንድ መሆኑን በቅርቡ ይፋ የተደረገ አንድ ሪፖርት ያመለክታል፡፡ ዩናትድ ስቴት አሜሪካ 77 ሺህ የመንገድ ድልድዮች ለመፍረስ የተቃረቡ መሆናቸውን

☞

የገምጋሚዎች አንድ ቡድን አስታውቋል፡፡ ከቁጥጥር ውጪ የሆነ የአየር ንብረት ለውጥ ችግር እያንዣበበ ሳለ፣ መንግስታት አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ አይፈልጉም፡፡ የዛሬ ሁለት ዓመት በተከሰተ ካትሪና የተባለ ሐሪኬን (የነፋስ ማዕበል) ሳቢያ ቤት ንብረታቸው ወድሞ ተፈናቃይ የሆኑ፣ 120 ሺህ ሰዎች ዛሬም በጊዜያዊ መጠለያ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ የፖርቶሪኮ ነዋሪዎችም በችግር ላይ ናቸው፡፡ በአሁኑ ሰዓት በከፍተኛ መጠን እየሰፋ የሚሄደው የሐብት አለመመጣጠን ሁኔታ፣ ከአንደኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ በዓለም ታይቶ የማይታወቅ በጣም የተከፋፈለ ህብረተሰብ የሚፈጠርበትን ሁኔታ ደቅኗል፡፡ ገደብ እና ቁጥጥር በሌለው የባንኮች የብድር አሰጣጥ ስርዓት ሳቢያ የተፈጠረው የፋይናንስ ቀውስ በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ከቤት ሊያፈናቅላቸው እየተንደረደረ ሲሆን፣ ችግሩ ማዕበላዊ ኢኮኖሚያዊ ውጥንቅጥ ሊያስከትልም ይችላል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ችግሮች ግንኙነት የሌላቸው መስለው ይታያሉ፡፡ ሆኖም ሁሉም ችግሮች ምንጫቸው አንድ ነው፡፡ በአብዛኛው እነዚህ በሐገረ-ስዊዝ በሚገኝ አንድ የስፓ ሪዞርት ከ60 ዓመት በፊት ከተካሄደ አንድ ስብሰባ የሚመነጩ ችግሮች ናቸው፡፡ ያ ስብሰባ ዛሬ ዓለምን የምትጨነቅባቸው ችግሮች ሁሉ እንዲፈጠሩ ያደረገ የኒዮ ሊበራል መንግስት ፍልስፍና የተቀረፀበት ስብሰባ ነው፡፡ ‹‹ሞንት ፔሌሪን ሶሳይቲ›› በሚል የሚጠቀሰው ቡድን በ1947 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ስብሰባ ሲያካሂድ፣ የያዘው የፖለቲካ ፕሮጀክት ያኔ መጠሪያ ስም አልነበረውም፡፡ ሆኖም ሶሳይቲው ወዴት መሄድ እንደሚፈልግ በግልጽ ያውቅ ነበር፡፡ ሶሳይቲው መሥራች ፍሬድሪክ ቮን ሃይክ (Friedrich von Hayek) በወቅቱ፣ ‹‹በሐሳብ ጦርነት አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት ቢያንስ የአንድ ትውልድ ጊዜን ይጠይቃል›› ሲል ተናግሮ ነበር፡፡ ሆኖም ሃይክ ያሰማራው የሐሳብ ሠራዊት ጠንካራ ደጀን በቶሎ እንደሚያገኝ እርግጠኛ ነበር፡፡ በ1947 የቀመረው ፍልስፍና በኋላ ኒዮ ሊበራሊዝም የሚል ስያሜ ያገኘ ሲሆን ፍልስፍናው እጅግ የባለፀጎችን ፍላጎት የተከተለ በመሆኑም የእነርሱን ሙሉ ድጋፍ ማግኘት እና የፍልስፍናው ሐዋርያ ሆነው አስፋፍተውለታል፡፡

እንደሚታወቀው፣ ኒዮ ሊበራሊዝም ከፍተኛ የገበያ ነጻነት እና የተገደበ የመንግስት ጣልቃ ገብነት ሲኖር ትጠቀማላችሁ ባይ ነው፡፡ “የመንግስትም ሚና ገበያን በመፍጠር እና በመጠበቅ፣ የግል ሐብትን

☞

ከጥቃት በመከላከል እና ዋስትና እንዲያገኝ በማድረግ ሊወሰን ይገባል፡፡ ሌላው ሥራ ሁሉ በላቀ ደረጃ ሊፈጸም የሚችለው፤ ትርፍ ለማግኘት ሲል አስፈላጊውን አገልግሎት ሁሉ ለማቅረብ በሚንቀሳቀሰው በግሉ ባለሐብት ነው፡፡ በዚህ መንገድ ሲኬድ የግል ድርጅቶች ነጻ ይሆናሉ፤ ምክንያታዊ (Rational) ውሳኔ ያደርጋሉ፤ ዜጎችም ሰው የመሆንን ፀጋ ከሚጎዳ የመንግስት እጅ ይጠበቃሉ" የሚል ነው፡፡

ዞሮ ዞሮ ይህ ቲዮሪ ነው፡፡ ሃርቬይ ‹‹የኒዮ ሊበራሊዝም አጭር ታሪክ›› (A Brief History of Neoliberalism) ሲል በሰየመው መጽሐፉ እንደገለጸው፤ የኒዮ ሊበራል ፕሮግራም ሲተገበር፤ በሐብት መሰላሉ አናት ከተቀመጡት እና አንድ ፐርሰንት ከሚሆኑት ባለሐብቶች እጅግ ከፍተኛ ሐብትን ያስገባል፡፡ በትክክል ለመናገር፤ እጅግ ከፍተኛ ሐብት ከአንድ ፐርሰንቱ ከሚመደቡት የመጀመሪያዎቹ አስር ባለሐብቶች እጅ እንዲገባ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም፤ በአሜሪካ 0 ነጥብ 1 ፐርሰንት የሚሆኑት ባለሀብቶች ገና ከ1920ዎቹ ዓ.ም ጀምሮ ከመሰላሉ ጫፍ መቀመጥ ችለዋል፡፡

ኒዮ ሊበራሊዝም ሰዎችን ከመንግስት ባርነት ነጻ ለማድረግ አስፈላጊ ሁኔታ አድርጎ የሚያስቀምጠው፤ ዝቅተኛ የግብር ተመንን፣ የመንግስት አገልግሎት እና የማህበራዊ ዋስትና ስርዓት ማፈራረስን፤ ምንም ዓይነት የቁጥጥር እና የገደብ ስርዓት እንዳይኖር ማድረግን ሲሆን፤ ይህም ጥቂቶችን የበለጠ ሐብታም ለማድረግ የተቀመጠ ቅድመ ሁኔታ መሆኑ ታይቷል፡፡ቀሪው እየሰመጠ እና እየቀዘፈ የሚንገላታ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ከላይ የተጠቀሱት በአሜሪካ እና በእንግሊዝ የታዩ ችግሮች፤ የመንግስት አገልግሎትን በማፈራረስ፣ ንግድ እና የፋይናንስ ገበያው ከቁጥጥር እና ከገደብ ነጻ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ በመደረጉ የተፈጠሩ ችግሮች ናቸው፡፡ ጉዳዩ እንዲህ ከሆነ፤ ኒዮ ሊበራሊዝም ከሞላ ጎደል የሁሉንም ጥቅም የሚጎዳ ፕሮግራም ሆኖ ሳለ፤ መንግስታት ይህን ፕሮግራም የሚከተሉት ለምን ይሆን? አሁን ዓለም ከሞላ ጎደል ኒዮ ሊበራል ሆኗል፡፡ እንደ እንግሊዟ ጠቅላይ ሚኒስትር ማርጋሪት ታቸር ሁሉም መንግስታት ‹‹ሌላ አማራጭ የለንም›› ብለው በማሰባቸው ይሆን? በርግጥ ተራማጅ የነበሩ ፓርቲዎች ወይም መሪዎች ጭምር (ቢል ክሊንተን፣ ቶኒ ብሌር እና .....ብራውን) ጭምር የታቸርን ፕሮግራም ሲከተሉ አይተናል፡፡ ለጊዜው ስኬት አግኝተውበት ነበር፡፡ ግን

☞

አሁን እንደሚታየው የነገሩ መጨረሻ አላማረም፡፡

ታዲያ ኒዮ ሊበራሎች ፕሮግራማቸውን ለማስፈፀም ሰፊ ዕድል ማግኘት የቻሉት፤ የማይነጥፍ የገንዘብ ምንጭ ያላቸው በመሆኑ ነው፡፡ አሜሪካዊ ኦሊጋርኮች እና በስማቸው የሚያቋቁሟቸው ፋውንዴሽኖች -- ኩርስ (Coors)፣ ኦሊን (Olin)፣ ስካይፌ (Scaife)፣ ፔው (Pew) እና ሌሎችም -- ቲንክ-ታንኮችን ለማቋቋም በመቶ ሚሊዮን ዶላር የሚገመት ገንዘብ ወጪ ያደርጋሉ፡፡ የንግድ ሥራ ት/ቤት ይከፍታሉ፡፡ በየዩኒቨርሲቲው የሚገኙ የኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍሎችን የኒዮ ሊበራል አስተሳሰብ ምሽጎች ያደርጓቸዋል፡፡ የሂሪቴጅ ፋውንዴሽን፣ ሑቨር ኢንስቲትዩት፣ የአሜሪካን ኢንተርፕራይዝ ኢንስቲትዩት እና ሌሎችም--በአሜሪካ፤ ዘ ኢንስቲትዩት ኦቭ ኢኮኖሚክ አፌርስ፣ ዘ ሴንተር ፎር ፖሊሲ ስተዲስ እና አዳም ስሚዝ ኢንስቲትዩት -በዩናይትድ ኪንግደም፤ የተመሠረቱት የኒዮ ሊበራል ፕሮጀክትን ለማስፋፋት ነው፡፡ የፕሮግራሙን እውነተኛ ዓላማ ለመሸፋፈን የሚያስችሉ ቃላት እና ሐሳቦችን መፈብረክ ነው፡፡ ለሰው ልጆች ህይወት መሻሻል የሚበጅ ፕሮፖዛል አድርጎ ማቅረብ ነው፡፡

በዚህ መንገድ የሚያደርጉት ጥረት የመሳካት ዕድል የሌለው በመሰላቸው ጊዜ፤ ኒዮ ሊበራሎች እና ደጋፊዎቻቸው ጉቦ እና የኃይል እርምጃን ይጠቀማሉ፡፡ ለምሣሌ በአሜሪካ ዴሞክራቶች የምርጫ ቅስቀሳን ለመደንገግ በወጣ አዲስ ህግ እንቅስቃሴአቸውን የሚያኮላሽ ሁኔታ ተፈጥሮባቸው ነበር፡፡ስለዚህ ከሪፓብሊካኖች ጋር ስኬታማ ፉክክር ለማድረግ፤ አንድ ትልቅ ንግድ የፈለገውን እንዲያገኝ ለማድረግ ተገድደው ነበር፡፡ የመጀመሪያው የኒዮ ሊበራል ፕሮግራም የተተገበረው በቺሊ ነበር፡፡ የቺሊ መሪ ጀነራል ፒኖቼ በመፈንቅለ መንግስት ከተወገደ በኋላ፤ ‹‹ከሞንት ፔሌሪን ሶሳይቲ›› መሥራቾች አንዱ በሆነው ሚልተን ፍሬድማን በሰለጠኑ ኢኮኖሚስቶች እና በአሜሪካ መንግስት ድጋፍ ፕሮግራሙ በቺሊ ተተግብሮ ነበር፡፡ የድጋፍ ከበሮውን መደለቅ ቀላል ነው፡፡ ካልተስማማህ ትመታለህ፡ ፡አይ.ኤም.ኤፍ እና የዓለም ባንክ ተመሳሳይ ፖሊሲ በታዳጊ ሐገራት ለማስፈጸም ያላቸውን ኃይል ይጠቀማሉ፡፡ ሆኖም የዚህ ፕሮግራም ዋና አሻሻጭ ሚዲያ ነው፡፡ ብዙዎቹ ሚዲያዎች የተያዙት በመልቲ ሚሊየነሮች ነው፡፡ ስለዚህ የራሳቸውን ጥቅም ለማራመድ ሚዲያዎቹን ይጠቀሙባቸዋል፡

☞

የእነሱን ፕላን ቸል ያለ ሚዲያ ይጣጣላል ወይም ከነመኖሩም ይረሳል፡፡ ማህበራዊ ጥፋት የሚያስከትሉ የጥቂት ፅንፈኛ ቡድኖች ሐሳብ፤ ‹‹ኮመን ሴንስ›› ከመሆን የደረሰው በጋዜጦች እና በቴሌቪዥን ተቋማት አማካኝነት ነው፡፡ የኒዮ ሊበራል እሳቤዎችን ለማሻሻጥ አዳዲስ ፖለቲካዊ ቃላት ይፈበረካሉ፡፡ኒዮ ሊበራሊዝም በጊዜ ገደብ ካልተደረገበት በውድቀት ላይ ውድቀት የሚጎትት ይሆናል፡፡ ወድቀቶቹም ሊገቱ የሚችሉት፤ ኒዮሊበራሊዝም የሚከለክለውን ጎዳና በመከተል ብቻ ነው፡፡ አሁን ችግሩ በዓለም ሰላም እና ደህንነት ላይ ሥጋት ደቅኗል፡፡ ሥጋቱም ከቀኝ አክራሪ ህዝበኝነት መስፋፋት ጋር የተቆራኘ ነው፡፡

ጆርድ ሚኒቦት እንደሚለው ከኢንዱስትሪ አብዮት ጀምሮ ዓለም በተለያዩ ስርዓቶች ተዳድራለች ፡፡ እንደሱ አባባል ከኢንዱስትሪ አብዮት እስከ 1914 ድረስ ዓለም የተዳደረችው በሊዝፌየር አስተሳሰብ ነበር፡፡ ምንም እንኳን በተለይም የአውሮፓን ኢኮኖሚ ከፍተኛ ዕድገት እንዲያመጣ ቢያግዝም የማታ ማታ በጊዜው አውሮፓ ያጋጠማትን ከፍተኛ የስራ አጥነት ችግርና የዋጋ ግሽበትን ሊፈታ አልቻለም፡፡ በመሆኑም ዓለም ከ1914 ቀደም ብሎ ባሉት 20 ዓመታት ቀስ በቀስ እየተስፋፋ የመጣውና ዕውቁ ካይነስ እየተባለ የሚጠራው እንግሊዚያዊው ኢኮኖሚስት የተቀመረው አስተሳሰብ የዘመኑን ጥያቄ መመለስ አቅቶት ተንገራግጮ የቆመውን ሊዜፊየርን ተካ፡፡ይሄ አስተሳሰብ በአመንጪው ስም ተሰይሞ ኬይኔዥኒዝም ተብሎ ተሰየመ፡፡ አስተሳሰቡ ከ1914-1970 ዎቹ መጨረሻ ዓለምን መርቷል፡፡ ሆኖም ይሄው አስተሳሰብም የማታ ማታ ኪሳራ አጋጥሞታል፡፡ በአንድ በኩል ሁኔታው ያልተመቸው ባለሃብት ስርዓቱን ሲያጠቃ በሌላ በኩል ደግሞ በግዜው ያጋጠመውን ከፍተኛ ስራ አጥነትና የዋጋ ግሽበት ችግር መፍታት ተስኖት ይሄው አስተሳሰብም በተራው የከሰረ ወደ መሆኑ ተሸጋገረ፡፡ ሆኖም የ1930 ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ቀስ በቀስ እያደገ መጥቶ ከዚያም በኃላ ደግሞ በባለሃብቱ ጋሻ ጃግሬነት እየተስፋፋ የመጣና ካይነስ ከሰረ ተብሎ ወደ ቆሻሻ ቅርጫት ሲጣል ለመተካት ዝግጁ የሆነ አስተሳሰብ ነበር፡፡ እርሱም ኒዮ ሊበራሊዝም ይሰኛል፡፡ ኒዮ ሊበራሊዝም በተለይ ዓለምን ከ1970 ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ እስከ 2008 ዓለምን አሰተዳደረ፡፡ ይሄ ስርዓትም ጊዜው ደርሶ ሊፈታው የማይችል ከፍተኛ የሆነ ተግዳሮት ገጠመው፡፡ ተግዳሮቶችም ከፍተኛ የስራ አጥነት፣ የማያባራ የኢኮኖሚ

☞

ቀውስ ፣ ከፍተኛ የገቢ ልዩነት ፣ የምርታማነት መቀዝቀዝና የምዕራቡ አገራት ኢንዱስትሪ አልባ መሆን ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ይሄ አስተሳሰብ ከላይ ያየናቸው ከሰሩ ተብለው ከተጣሉት  አስተሳሰቦች በላይ ጥልቅ የሆነ ቀውስ ገጥሞታል፡፡ በሌላ አባባል ከሊዚፊየርና ከይኔዥኒዝም በላይ በአስተሳሰብ ደረጃ በመክሰሩ አለማችን በአሁኑ ሰዓት ያጋጠማትን ችግር መፍታት ይቅርና የሚያባብስ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ጥያቄ ታዲያ ለምንድነው እንደሌሎች ስርዓቶች በሌላ ስርዓት ያልተተካው? የሚለው ነው፡፡

ከላይ እንደአየነው አንድ ስርዓት ሲከስር ከዚያ በፊት 20ና10 ዓመታት በሆነ ግዜ ውስጥ እየተስፋፉ የሚመጣ  ስርዓቱን ሊተካ የሚችል አስተሳሰብ  እንዲፀነስ ይደረግ ነበር፡፡ ሆኖም በዚህ ወቅት ምንም እንኳ ስርዓቱ ሁለመናው የከሰረ ቢሆንም ሊተካው የሚችል በአግባቡ የተቀመረ ሃሳብ የለም ወይንም ደግሞ በደንብ አልታወቀም፡፡ ስለሆነም በአሁኑ ስዓት አለማችንን በተለይም ደግሞ የምዕራቡን ዓለም እየመራ ያለው የከሰረ ስርዓት ነው ማለት ይቻላል፡፡ እንደሚታወቀው  መንግስት  የህብረተሰቡን ችግሮች የመቅረፍ ግዴታ አለበት ፡፡ ሆኖም የኒዮ ሊበራሊዝም የቀጫጫና ትናንሽ መንግስታት እሳቤ መንግስታት ይሄንኑን ተፈጥሯዊ አቅማቸውን አሳጥቷቸዋል፡፡ እናም መንግስት በተለይም የምዕራቡ ዓለም በአሁኑ ጊዜ የገጠመውን ችግር የመፍታት አቅሙና ተነሳሽነቱ የለውም፡፡ በመሆኑም የከሰረው  ነገር ግን በአማራጭ አሰተሳሰብ እጦት ዛሬም የመኪና መዘውሩን የሚያሽከረክረው የኒዮ ሊበራሊዝም አስተሳሰብ ጥርሱን ነቅሎ ባደገባቸው አገራት መያዣ መጨበጫ በሌላቸው የቀኝ አክራሪ ህዝበኛ ፓለቲካ አቀንቃኞች በቁጥጥር ስር እየዋለ ይገኛል፡፡ በተነፈሰ ጐማ ረጅም ርቀት መሄድ እንደማይቻል ሁሉ በከሰረ አስተሳሰብም ረጅም ርቀት መሄድ አይቻልምና የማታ ማታ ውጥንቅጡ የወጣው ዓለማዊው ሁኔታ በተለይም የምዕራቡ ዓለም አገራት መተካካት እንዳይባል የተደራጀና የተቀመረ አሰተሳሰብ በሌለበት ሁኔታ ንፋሱ ለቀኝ አክራሪ ህዝበኞች እያደላ ይገኛል፡ ፡ለመሆኑ የቀኝ አክራሪ ህዝበኝነት ምንድነው? እስኪ ቀጥለን እንየው፡፡

☞

## 2.1.3. ህዝበኝነት ምንድነው

ቀደም ሲል፣ ህዝበኝነት (Populism)፣ አክራሪ ቀኝ (Radical right)፣ ተስፈንጣሪ ቀኝ (Far right) ወይም ጽንፈኛ ቀኝ (Extremist right) በሚል ከሚጠቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ተያይዞ ይታይ ነበር፡፡ ሆኖም እያደር የተለየ ባህርይው ጎልቶ በመታየቱ ከቀኝ ጋር ተጎዳኝቶ መታየቱ እየቀረ መጥቷል፡፡

ህዝበኝነት ‹‹ፖፑሊዝም›› የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ትርጉም ሲሆን፣ ቃሉ ከላቲን ቋንቋ የመጣ ነው፡፡ ‹‹Populus›› የሚለው የላቲን ቃል ፍቺም ህዝብ የሚል ነው፡፡ ከዴሞክራሲ ጋር ጥብቅ ዝምድና ያለው ቃል ነው፡፡ ስለሆነም ዴሞክራሲ ባለበት ሥፍራ ፖፑሊዝም ይኖራል ማለት ይቻላል፡፡ እንዲያውም ህዝበኞች ራሳቸውን እንደ ‹‹እውነተኛ ዴሞክራት›› ሊያስቡ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ህዝበኞች ‹‹ህዝብ›› ሲሉ ‹‹እኛ›› እና ‹‹እነርሱ›› የሚል አስተሳሰብ ይዘው ነው፡፡ ልዩነትን በሚያጣጥል ወይም በሚጨፈልቅ አመለካከት ተቃኝተው ነው፡፡ ‹‹የእኛ ህዝብ›› ሲሉ ከእነሱ ወገን የማይካተቱ ሌሎችን (ለምሣሌ ስደተኞችን) ታሳቢ እያደረጉ ነው፡፡ ለህዝበኞች፣ ህዝብ አንድ ወጥ ነው፡፡ ተለይቶ ሊጠቀስ የሚችል ነው፡፡

በቲዮሪ ደረጃ ህዝበኞች ‹‹የእኛ ህዝብ›› ሲሉ፣ ነገሩ ግልጽ መስሎ ቢታይም፣ በተግባር ስለየትኛው ቡድን ወይም የህዝብ ክፍል እያወሩ መሆኑን ለማወቅ ያስቸግራል፡፡ ለምሣሌ፣ ሁለት የብሪቲሽ ፓርቲዎች ቃሉን የተለያየ መልዕክት በሚሰጥ ሁኔታ ይጠቀሙበታል፡፡ የብሪቲሽ ወግ አጥባቂ ፓርቲዎች እና ‹‹የብሪቲሽ ናሽናል ፓርቲ›› ቃሉን በማይጣጣም ሁኔታ ይገለገሉበታል፡፡ ወግ አጥባቂዎቹ ‹‹ማዕከላዊ ኢንግላድ››ን በማሰብ፣ “የብሪቲሽ ናሽናል ፓርቲ” ደግሞ ነባር የሚባለውን የብሪቲሽ ህዝብ በማሰብ ቃሉን ይጠቀሙበታል፡፡

“ህዝበኛነት” በጣም አሻሚ እና ወላዋይ ትርጉም ያለው ቃል ነው፡፡ጽንሰ ሐሳቡን በአንድ ብያኔ መግለጽ አዳጋች ነው፡፡ አንዳንዶች የህዝበኝነት አመለካከትን መለየቱ ከባድ አይደለም ይላሉ፡፡ ‹‹ሳየው አውቀዋለሁ›› ብለው ሊያልፉት ይችላሉ፡፡ ሆኖም ጉዳዩ ጥናት የሚያደርጉ አዋቂዎች ነገሩ እንዲህ ቀላል አይደለም ይላሉ፡፡ኢሳያህ በርሊን(Isaiah Berlin)

☞

የተባለ ፀሐፊ፤ ‹‹የህዝብኘኝነት ቅርጽ የያዘ ጫማ ማግኘት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ለጫማው ልክ የሚሆን እግር ከቶ አይገኝም›› ያለው የብያኔውን አስቸጋሪነት ለመግለጽ ነው፡፡ ፖል ታጋርት (Paul Taggart) የተባለ ምሁር በበኩሉ፤‹‹ህዝበኝነት በመሠረቱ ሁልጊዜም የተከሰተበትን አካባቢ ቀለም ይዞ የሚገኝ እስስታዊ ባህርይ ያለው ጉዳይ ነው›› ብሏል፡፡ በአጠቃላይ ለህዝበኝነት ብያኔ ለመስጠት መሞከር፤ በአንዱ ጉዳይ ትኩረት ሰጥቶ ሌላውን የመተው ችግር ያስከትላል፡፡

የሆነ ሆኖ፤ ህዝበኝነትን ለመበየን ሦስት ጎዳናዎችን መከተል ይቻላል፡፡ ህዝበኝነት የአክራሪ ቀኝ ክንፍ ፓርቲ አድርጎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ሆኖም ይህ የጉዳዩን ትክክለኛ ይዘት ለማሳየት የሚችል አይሆንም፡፡ አንዳንድ ፓርቲዎችም የተወሰነ ዓላማን ለማሳካት ሲሉ፤ ለዴሞክራሲ ሥርዓት አደጋ በማይሆን መንገድ ህዝበኝነትን እንደ ታክቲክ ሊጠቀሙት ይችላሉ፡፡ ህዝበኝነት፤ እንደ አንድ ርዕዮተ ዓለም ሊታሰብም ይችላል--የተሟላ እና የተደራጀ የህብረተሰብ ህይወት አመለካከት ባይኖረውም፡፡ እንዲሁም ህዝበኝነትን እንደ ማህበራዊ ንቅናቄም ማየት ይቻላል፡፡ ሆኖም ንፁህ ንቅናቄ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አድርጎ መውሰድ አይቻልም፡፡

በአካዳሚው መስክ፤ ህዝበኝነት ምንድነው ለሚለው ጥያቄ አስማሚ ምላሽ ባይኖርም፤ አብዛኞቹ ብያኔዎች ሁለት ጉዳዮችን ሳይጠቅሱ አያልፉም-- “ልሂቃን” እና ‹‹ህዝብ››፡፡ ካስ ሙዴ ህዝበኝነትን የሚመለከተው፤ “ህብረተሰብን ወጥ መልክ እና ተቃራኒ ፍላጎት ባላቸው ሁለት ቡድኖች ከፍሎ የሚመለከት ርዕዮተ ዓለም አድርጎ ነው” -- “ንፁህ ህዝብ” እና “የተበላሹ ልሂቃን”፡፡

ስለዚህ ህዝበኝነት ለብያኔ አስቸጋሪ በመሆኑ፤ ጉዳዩን በአግባቡ ለመረዳት፣ አጠቃላይ የሆነ ግንዛቤ ለመያዝ እና ከሌሎች ርዕዮተ ዓለሞች ለይቶ ለማውጣት ከወቅታዊ ማህበረ-ባህላዊ እና ማህበረ-ባህላዊ ጉዳዮች ጋር አስተሳስሮ ማየት ያስፈልጋል፡፡

☞

ህዝበኝነት በማናቸውም የዴሞክራሲ ስርኣት ውስጥ ሊታይ የሚችል ክስተት ነው፡፡ በተለይ ለህዝበኛ ፖለቲካ ተጋላጭ የሚሆነው በተቋማዊ ሽግግር ውስጥ የሚገኝ የፖለቲካ ስርዓት ነው፡፡ ለዚህ እንደ ዓይነተኛ ምሣሌ ሊወሰድ የሚችለው የሲልቪዮ ቤርሎስኮኒ ፓርቲ ‹‹ፎርዛ ኢታሊያ›› ነው፡፡ ከፍተኛ የህዝብ ቅሬታ በሚኖርበት ሁኔታ ለህዝበኝነት መከሰት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ይህን ቅሬታ ለመጠቀም የሚሻ መሪ ሲኖር ህዝበኝነት ተጸንሶ ይወለዳል፡፡

አንዳንድ ፓርቲዎች፣ ፖለቲከኞች ወይም አስተዳደሮች አካባቢያዊ መስተዳድሮችን እንደ ህዝብ አደራ መወጫ መሣሪያ ሳይሆን እንደ ራሳቸው የግል ሐብት ሊጠቀሙበት ሲጀምሩ ህዝበኝነት ምቹ መደላደል ያገኛል፡፡ እንዲሁም ሥራ አጥነት፣ የኑሮ ዋስትና ማጣት እና ለችግር ተጋለጭነት የዕለት ህይወት ክስተት ሲሆኑ ህዝበኝነት ሊያቆጠቁጥ ይችላል፡፡ ግሎባላይዜሽን፣ ፖስት-ሞደርናይዜሽን በዚህ ጉዳይ አስተዋጽዖ ይኖራቸዋል፡፡ የሥራዎች ወደ ሌላ ክፍለ ዓለማት መፍለስ፣ የመለስተኛ ባለሙያ ፍላጎት መቀነስ፣ ከታዳጊ ሐገራት ከፍተኛ ቁጥር ያለው ስደተኛ መምጣት፤ በአውሮፓውያን ዘንድ በኑሮ እርግጠኝነት የማጣት፣ የፍርሃት እና የተስፋ ቢስነት ስሜትን ፈጥሯል፡፡ ይህም ለህዝበኛ ፓርቲዎች ብቅ ማለት ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

### 2.1.4. የህዝበኝነት መገለጫ ባህርያት

ካስ ሙዴ የተባለ በህዝበኛ ፍልስፍና ላይ ሰፊ ጥናት ያደረገ አንድ የደች የፖለቲካ ተንታኝ የህዝበኛ ፍልስፍናን በሦስት መሠረታዊ መገለጫዎቹ ሊገልፀው ይሞክራል፡፡ ሙዴ፤ ጸረ ነባራዊነት (Anti-establishment)፣ የአምባገነን ዝንባሌ ያለው (Authoritarian) እና ‹‹ሐገሩ ለባለሐገሩ›› (Nativism) የሚል አመለካከት የህዝበኛ የፖለቲካ ፓርቲ መገለጫዎች መሆናቸውን ይጠቅሳል።

በመጀመሪያ ደረጃ፤ ህዝበኛ ፍልሰፍና የዘቀጠ የሚለውን ነባራዊ ስርአት በማጥላላት፤ በብዙሀኑ ድምጽ አልባ ተራ ህዝብ አስተሳሰብና ጥበብ ላይ እምነት ያሳድራል፡፡ ህዝበኝነት ፀንቶ በሚገኘው የአስተዳደር ስርአት

☞

እና የመወሰን ስልጣን ባላቸው፣ በታላላቅ ንግዶችና ባንኮች፣ በድንበር ዘለል መልቲ ናሽናል ኮርፖሬሽኖች፣ በመገናኛ ብዙሀን፣ በተመራጭ ፖለቲከኞች፣ በልሂቃንና በሳይንስ ኤክስፐርቶች፣ እንዲሁም ኃጠወጥ እና የሥርዓቱ ልዩ ተጠቃሚ ናቸው በሚላቸው ከበርቴዎች ላይ ያለመተማመን እና ተቃውሞ መግለጽን ያቀነቅናል። በህዝበኞች አስተሳሰብ ከማይታመነው ልሂቃን በተቃራኒ ተራው ህዝብ ወጥነት ያለውና በተፈጥሮው መልካምና ጨዋ የሆነ መሆኑን ያምናል።

ሁለተኛ፤ የህዝበኞች መገለጫ አምባገነናዊነት ነው። ህዝበኛ አስተሳሰብ የህዝብን ፍላጎት ሊያራምድ የሚችል ግርማ ሞገስን የተላበሰ የጠንካራ ግለሰብ አመራር መኖርን ያቀነቅናል። በህዝበኛ ዘንድ የብዙሀኑ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ተግባራዊ መሆን ያለበት በህዝቡ ቀጥተኛ የድምጽ አሰጣጥ ወይም ውሳኔ ህዝብ እንጂ የእናሳው ቡድን መብት ሊጠበቅና ሊሰማ በሚችልበት የውክልና ዴሞክራሲ አይደለም።

ሶስተኛ፤ ህዝበኛ አስተሳሰብ "ሐገሩ ለባለሐገሩ" የሚል አመለካከት በማቀንቀንና የውጭ ዜጎችን የመጥላት ብሄረተኛነትን የማራመድ፣ ህዝብ ወጥነት ያለው የአንድ አገር ዜጋ ስለሆነ በስደትም ሆነ በተለያየ ምክንያት ወደ ሐገር የሚገቡ ሰዎችን የማስወገድ አስተሳሰብን በማራመድ ይገለጣል፡፡

ህዝበኝነት ከብዝሀነት ይልቅ አሀዳዊነትን፣ ከአለም አቀፍ ትብብርና ልማታዊ እርዳታ ይልቅ የአገርን ብሔራዊ ጥቅም ብቻ መመልከትን፣ ከሰዎች የጉልበት፣ የእውቀትና የሐብት ነጻ ዝውውር ይልቅ ድንበር ማጠርን፣ ከተራማጅ አስተሳሰብ ይልቅ ዘልማዳዊ ባህልና ስርአትን አጥብቆ የሚያቀነቅን አስተሳሰብ ነው። የዶናልድ ትራምፕ፤ ጸረ ብዝሀነት፣ የጥንት ስርአት ናፋቂነት፣ የውጪ ዜጎች ጥላቻ፣ ሴቶችን ዝቅ አድርጎ የማየት፣ የዘረኛነትና የጸረ ሙስሊም ይዘት ያለው የምርጫ ዲስኩርም ለዚህ አንዱ ማሳያ እንደሆነ ካስ ሙዴ ያስቀምጣል።

በሌላ በኩል፤ ፖል ታጋርት እንደሚለው የህዝበኝነት መገለጫ ባህርያት፤ "ህዝብን" የርዕዮተ ዓለም ማዕከል አድርጎ መነሳት፣ መሠረታዊ

☞

የሚባል እሴት ማጣት፣ የአቋም ፈጣን ተለዋዋጭነት፣ የተፈጠረን አንድ ቀውስ ተከትሎ መድህን መስሎ መቅረብ ወዘተ ናቸው ይላል፡፡

ህዝበኞች ራሳቸውን የህዝብ ድምጽ እና "እውነተኛ ዴሞክራት" አድርገው የሚመለከቱ እና የህዝቡን ሉዓላዊነት ለማስከበር የሚታገሉ አድርገው ያቀርባሉ፡፡ ብዙዎቹ በአካባቢያዊ ችግሮች ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ "በብልሹ" ልሂቃን ሽፍጥ (ደካማነት) ‹‹የጠፋችውን ገነት›› እና የጥንቱን ገናናነት የማስመለስ መፈክር የሚያነሱ ናቸው፡፡ ህዝበኞች የተወሰኑ መራጮችን ዒላማ የሚያደርጉ እና ግልጽ፣ ቀጥተኛ እና ለየት ያለ የቋንቋ አጠቃቀም ያላቸው ናቸው፡፡ ቢሮክራሲያዊ ከሆነ የፖለቲከኞች ቋንቋም ይርቃሉ፡፡ በህዝበኞች አመለካከት፤ ዓለም በጠላቶች እና በወዳጆች የሚከፈል ነው፡፡ ህዝበኞች ቀንደኛ ጠላት አድርገው የሚመለከቷቸው ሁለት ቡድኖች አሉ፡፡ "ከላይ" ልሂቃኑ፤ "ከታች" ስደተኞች ወይም በማህበረሰቡ አንድነት ላይ አደጋ የጋረጡ አድርገው የሚመለከቷቸው ሌሎች ቡድኖች በሚል ይከፈላሉ፡፡

ከዚህ በተቃራኒው የሚቆሙት "ሊበራል ኮስሞፖሊታን" እሴቶችን የሚያቀነቅኑት ናቸው፡፡ "ኮስሞፖሊታን" (Cosmopolitans) የሚለው ቃል ምንጩ  ከግሪክ ሲሆን፤ግሪኩ Kosmopolitês ሲል "የዓለም ዜጎች" ማለቱ ነው፡፡ይህም የሰው ልጆች ሁሉ በአንድ ድንበር በተከለለ የፖለቲካ ማህበረሰብ ተወስነው የሚኖሩ ሳይሆን በየጊዜው እየተጠናከረ የሚሄድ ግንኙነት በተገነባ በአንድ ግሎባላዊ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ መሆናቸውን የሚገልጽ ቃል ነው፡፡

በመሆኑም፤ ኮስሞፖሊታኒዝም "ሐገሩ ለሐገሬው" (Nativism) የሚል አመለካከት ተቃራኒ ነው፡፡ ድንበር ዘግቶ መኖርን ሳይሆን ነጻ የሰዎች ዝውውርን የሚቀበል፤ ከተለያዩ ባህሎች የተውጣጣ የጋራ ባህላዊ እሴቶችን በማዳበር ላይ የተመሠረተ፤ የሰዎችን እና የአኗኗር ዘይቤ ብዝሃነትን የሚቀበል እና ሁሉን አቅፎ ለመያዝ ዝግጁ የሆነ አመለካከት ያለው ነው፡፡

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ፤ የተለያዩ ሐገራት ህዝቦች ትስስር እና ግንኙነት፤ በዘርፈ ብዙ መስተጋብር እየተቆራኘ እና ይበልጥ

☞

"ኮስሞፖሊታን" እየሆነ፤ ሰዎች አንድ ወጥ መልክ ባለው ሐገረ-መንግስት ሊኖሩ ይገባል የሚለውም ህዝበኛ አመለካከት፤ ከሌሎች ሐገራት በሚመጡ ሠራተኞች፣ቱሪስቶች፣ ተማሪዎች፣ ስደተኞች እና የዳያስፖራ ማህበረሰቦች የተነሳ የተዳከመበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡ ክፍት ድንበርን በመፍጠር እና ሌሎችን ተቀብሎ ለመኖር ዝግጁ በመሆን አስተሳሰብ ላይ የቆመው የ"ኮስሞፖሊታን" አመለካከት፤ ከሊበራል እሴቶች ጋር የተሳሰረ እና የህዝበኝነትን አምባገነናዊ ዝንባሌ ተቃራኒ ባህርይ ያለው ነው፡፡

ተቋማዊ በሆነ የውክልና ዴሞክራሲ ስርዓት ውስጥ ላለው የጎንዮሽ የቁጥጥር እና ሚዛን ስርዓት አጽንዖት የሚሰጥ፤ የአናሳዎችን መብት የሚያከብር እና የሚያስጠብቅ፣ በምርጫ እና በፖለቲካ ፓርቲዎች አባልነት የፖለቲካ ተሳትፎን የሚያበረታታ፣ የማህበራዊ፣ ምሁራዊ እና ፖለቲካዊ ብዝሃነትን የሚቀበል፤ መቻቻል እና መግባባትን የሚያጠናክር፣ ምክኑያዊ ውሳኔ በማሳለፍ ረገድ የሳይንሳዊ ዕውቀት ሚናን የሚቀበል እና ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የተደራጀው ግሎባላዊ የአስተዳደር ስርአት እና ዓለም አቀፋዊ ትብብሩ መጠናከሩ አስፈላጊ መሆኑን የሚቀበል አመለካከት ነው፡፡ ይሄ አመለካከት ብዙዎቹ ኬይኔዝያኒዝም እያሉ ይጠሩታል፡፡

ህዝበኝነት የዚህ አመለካከት ተቃራኒ ነው፡፡ ታዲያ በዚህ ምድብ የሚወድቁ የፖለቲካ ፓርቲዎችን እና ንቅናቄዎችን ለይቶ ለማስቀመጥም የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ ይህን ጽንሰ ሐሳብ በማብራራት ከፍተኛ ተጽዕኖ ያለውና ቀደም ሲል የጠቀስነው ካስ ሙዴ (Cas Mudde) የተባለው፤ የህዝበኝነት ፍልስፍና በወጉ የተደራጀ አይደለም ይላል፡፡ ፍልስፍናው ግጥምጥምነት የሌላቸው የተለያዩ ሐሳቦች ጥርቅም ቢሆንም፤ ከፍ ብሎ በተጠቀሱት ሦስት መሠረታዊ ጉዳዮች፤ ማለትም ፀንቶ የሚገኘውን ሥርዓት በመገዳደር (Anti-establishment)፣ በአምባገነንነት ዝንባሌ (Authoritarian-ism) እና "ሐገሩ ለባለሐገሩ" (Nativism) የሚል ገበያን ከሌላው የመከለል (Protectionism) ፖሊሲ እና አመለካከት በማራማድ ይታወቃሉ፡፡ ህዝበኞች፤ ‹‹ከተበላሸ›› መንግስታዊ ሥርዓት ይልቅ የተራው ህዝብ (የድምጽ አልባው ብዙሃን) ጥበብ እና ብቃት ይሻላል በሚል የሚታመን ፍልስፍና ነው፡፡

☞

ህዝበኞች የህዝቡን ፈቃድ ያንጸባርቃል ተብሎ በሚታሰብ ጠንካራ እና በሆነ ምክንያት የህዝብ ተቀባይነትን ለማግኘት በቻለ ግለሰብ አድራጊ ፈጣሪነት ወይም የውሳኔ ስልጣን ይታመናሉ፡፡ እንዲሁም ህዝበኞች፣ የህዝቡ ፈቃድ መገለጫ እንዲሆን የሚፈልጉት ቀጥተኛ የብዙሃን ዴሞክራሲ (Majoritarian Democracy) የሚባለውን የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ሲሆን፣ ይህም የህዝብ አስተያየትን በማሰባሰብ፣ በሪፈረንደም እና ሁሉም መራጭ ህዝብ ድምጽ በቀጥተኛ ተሳትፎ አድርጎ ውሳኔ በሚያሳልፍበት ስርዓት (Plebiscites) እንጂ ተቋማዊ የሆነ የቁጥጥር እና ሚዛን ስርዓት በሚኖርበት፣ የአናሳዎች መብት ጥበቃ በሚያገኝበት የውክልና ዴሞክራሲ ሂደት ጉዳዮች ውሳኔ እንዲያገኙ አይፈልጉም፡፡

በህዝበኞች ‹‹ተራው ህዝብ›› ሲሉ፣ ትኩረታቸው ‹‹የሐገሬው ሰው›› የሚሉትን የህዝብ ክፍል ብቻ መጥቀሳቸው ነው፡፡ ስለሆነም፣ አመለካከታቸው መጤ-ጠል ብሔርተኝነት የሚንጸባረቅበት እና ህዝብን አንድ ወጥ መልክ ያለው አድርጎ የሚመለከት በመሆኑ፣ ከሌላ ሐገር እና ባህል የተገኙትን ዜጎች ከህዝብ አይቆጥራቸውም፡፡ መንግስት ከሌላ ሐገር እና ባህል የተገኙት ዜጎች ጉዳይ አይመለከተውም ብለው የሚያስቡ ናቸው፡፡

ከሁለተኛው አለም ጦርነት ወዲህ ብሄራዊ ድንበርን ክፍት የማድረግና የተለያየ ባህል ያላቸው ህዝቦች በንግድም ሆነ በማህበራዊ ግብየት ከፍተኛ መስተጋብር ማድረግ የሚችሉበት አለማቀፋዊ ማህበረሰብ(Cosmopolitan) የመፍጠር ሁኔታ በስፋት የተስተዋለበት ዘመን ነው። ነጋዴዎች፣ ሰራተኞች፣ ተማሪዎች፣ ቱሪስቶች፣ ስደተኞችና ዳያስፖራዎች ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር በመንቀሳቀስ ትስስር ፈጥረው የሚኖሩበት ሁኔታ ነበር። ከሁለት አስርት አመታት ወዲህ እየገነገነ የመጣው የህዝበኛ አስተሳሰብ አራማጆች ግን ከአለም አቀፍ ማህበረሰብ ይልቅ ለከባቢያዊ ማህበረሰብ ትኩረት የሚሰጥ በመሆኑ በአመዛኙ ጠባብ አገራዊ ወገንተኛነትን ብቻ የሚያራምድ ነው።

አለም አቀፋዊ አስተሳሰብ ከህዝበኛ አስተሳሰብ በተቃራኒው ድንበርን ክፍት በማድረግ ሰዎች በነጻ አስተሳሰብ የህዝበኝነት አንባገነናዊ ገጽታዎችን መሞገት የሚችሉበትን፣ በውክልና ዴሞክራሲ ተቋማትን መቆጣጠርና

☞

ማስተካከል የሚችሉበትን፣ የአናሳዎች መብት የሚጠበቅበትን፣ በምርጫ የሚሳተፉበትንና በፈለጉት የፖለቲካ ፓርቲ መታቀፍ የሚችሉበትን፣ ማህበራዊ፣ ምሁራዊና ፖለቲካዊ ብዝሀነትን አቻችለው ማስቀጠል የሚችሉበትን፣ አለመግባባቶች በድርድርና በማስታረቅ የሚፈቱበትን፣ ለምክንያታዊ ፖሊሲዎች መቀረጽ አስተዋጽኦ የሚያደርጉበትን፣ በአለም አቀፍ መንግስታት መካከል ትብብር የሚጠናከርበትን ሁኔታ ለመፍጠር ሰፊ ዕድል ይሰጣል።

በተመሳሳይም ሶሻል ሊበራሊዝም አስተሳሰብም ከህዝበኛ አስተሳሰብ በተቃራኒው ለሴቶችና ለአናሳ ቡድኖች መብትና እኩልነት፣ ለአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች፣ ከሀይማኖታዊ ይልቅ ከሀይማኖት ገለልተኛ ለሆኑ እሴቶች ትኩረት ይሰጣል።

ቀደም ባለው አፈራረጅ ህዝበኝነት ከጽንፈኛ ቀኝ አክራሪነት ጋር ተያይዞ ይገለጽ ነበር። ይሁን እንጂ ዛሬ በአሜሪካ፣ በምስራቅ አውሮፓና በእስያ የሚንቀሳቀሱ ህዝበኛ የፖለቲካ መሪዎች ከኢኮኖሚ አንጻር የግራ ክንፍ ፖሊሲዎችን የሚቀበሉ በመሆናቸው ቀኝ አክራሪ የሚለው መጠሪያ በተሟላ መልኩ ሊገልፃቸው አይችልም። ለዚህም ግራ ዘመሙ የቬንዙዌላ የቀድሞ መሪ ሁጎ ቻቬዝ ተጠቃሽ ነው። በዩናይትድ ስቴትስ በ1891 የተፈጠረው ህዝበኛ ፓርቲ ጸረ ልሂቃን የገጠር እንቅስቃሴ በካፒታሊዝም በተለይም ደግሞ በባንኮች ላይ እምነት የሌለው ግራ ዘመም ነበር። በተመሳሳይም ለንግድ ከለላ ትኩረት የሚሰጠውና በቻይና ምርቶች ላይ ከፍ ያለ ቀረጥ መጣል እንዳለበት የሚሞግተው ወግ አጥባቂው ትራምፕም በግራ ዘመም የሚፈረጅ ህዝበኛ ነው።

Tramp, briexit, and the rise of populism: economic have-nots and cultural backlash በሚል ርዕስ በሮናልድ ኢግልሀርትና ፒፓ ኖሪሰ በ2016 በቀረበው የጥናት ሰነድ ላይ የተቀመጠው የሂዩሪስቲክ ሞዴል የኮሚኒስት፣ ሶሻሊስት፣ ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲዎች በኢኮኖሚው፣ በተሻሻለ የታክስ ስርአት ፍትሀዊ የኢኮኖሚ ስርጭት እንዲኖር፣ ጠንካራ የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት እንዲስፋፉ የመንግስትን የአመራር ሚና የሚከተሉ የኢኮኖሚ ግራ ዘመም መስመር የሚከተሉ ህዝበኞች እንደሆኑ ያመለክታል።

☞

በአንጻሩ ሊበራል፣ ወግ አጥባቂና ክርስቲያን ዲሞክራቲክ ፓርቲዎች የነጻ ገበያ ስርአትን፣ ፕራይቬታይዜሽንን፣ ከመንግስት ቁጥጥር ነጻነትን፣ የታክስ ቅነሳን ትኩረት የሚያደርጉ፣ የመንግስት ሚናም ውሱን መሆን አለበት የሚለውን አስተሳሰብ የሚያራምዱ የኢኮኖሚ ቀኝ አክራሪ ህዝበኞች ናቸው።

እንደ ጀርመኑ ሪፐብሊካነር፣ የዩናይትድ ኪንግደም ኢንዲፔንደንት ፓርቲ እና የስዊዙ ስዊዝ ፒፕልስ ፓርቲ ከመንግስት ይልቅ ገበያ ተኮር አካሄድን የሚከተሉ የኢኮኖሚ ቀኝ አክራሪ ህዝበኛ ፓርቲዎች ናቸው። በአንጻሩ ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍልንና የማህበራዊ ዋስትናን ፖሊሲ የሚያራምዱት የቡልጋሪያው አታካ እና የሀንጋሪው ጆቢክ ፓርቲዎች በኢኮኖሚ ግራ አክራሪነት የሚፈረጁ ናቸው።

ህዝበኝነት አንድ ወጥ ባህልን እንጂ ብዝሃ ባህልን የማይቀበል እና በድንበር የተከለለ ሐገራዊ ጥቅም ማራመድን እንጂ ዓለም አቀፍ ትብብር እና ልማታዊ ዕርዳታን የማይደግፍ ነጻ የህዝብ፣ የሐሳብ፣ የጉልበት እና የካፒታል ዝውውርን ሳይሆን ድንበር ዘግቶ መኖርን፤ ሊበራል እና ተራማጅ ማህበራዊ እሴትን ሳይሆን አድሃሪ ወግ አጥባቂነትን የሚያቀነቅን ነው፡፡ ህዝበኛ መሪዎች ራሳቸውን የህዝቡን ፍላጎት የመረዳት ብቃት ያላቸው ብቸኛ የህዝብ ወኪሎች አድረገው ይወስዳሉ፡፡

አንዳንድ ምሁራን፤ ህዝበኝነት “ደካማ አይዲዮሎጂ ነው”ይላሉ፡፡ታዲያ የራሱ የሆነ የፖለቲካ ርዕዮት ባይኖረውም፤ ስልጣን ለመያዝ የሚያስችለውን “ሳልባጅ አይዲዮሎጂ” ይይዛል፡፡ በሌላ አገላለጽ፤ ህዝበኝነት የፖለቲካ ንቅናቄ ሳይሆን፤ የሥልጣን መቆናጠጫ መሣሪያ ነው፡፡በመሆኑም፤ ህዝበኛ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከቀኝ ወይም ከግራ የፖለቲካ ጎራ ሊመጡ ይችላሉ፡፡ ለምሣሌ፤ በግሪክ የመንግስት ስልጣን የያዘው ሲሪዛ (Syriza) የተሰኘው ፓርቲ የአክራሪ የግራ ክንፍ ፓርቲዎች ቅንጅት ሲሆን፤ የፈረንሳዩ ‹‹ናሽናል ፍሮንት›› የተደላደለ የቀኝ ፓርቲ ነው፡፡ ታዲያ የህዝበኝነት አስተሳሰብ መልክ በሌለው የርዕዮተ ዓለም የሚመራ በመሆኑ አንዳንዶች ‹‹የተቃውሞ ፓርቲ›› ሲሉ ይጠሩታል፡፡ ከነዚህ ሀሳቦች ተነስተን አሁን ለምን ስለህዝብኝነት መነጋገር አስፈለገ የሚለውን ቀጥለን እንመልከት፡፡

☞

### 2.1.5. ህዝበኝነት አሁን ለምን ገነነ ?

የዚህ ጥያቄ መልስ የሚገኘው በተለያዩ ሐገራት ከሚታየው እና ለህዝበኞች መነቃቃት ሰበብ ከሚሆነው ነባራዊ ሁኔታ ነው፡፡ ከነባራዊ ሁኔታው በመነሳትም፣ የህዝበኝነት አመለካከት አሁን ለምን እየተጠናከረ እንደመጣ ለመረዳት እንችላለን፡፡

በቅርቡ የወጣው ‹‹የሙኒክ የደህንነት ሪፖርት›› (Munich Security Report 2017)፣ የምዕራቡ ዓለም በህዝበኛ ንቅናቄዎች እና ፀረ-ሊላዊ የሆነ አመለካከት ባላቸው ኃይሎች (Anti-Globalist) የተነሳ ፈተና ውስጥ መውደቁን ይገልጻል፡፡ በሙኒክ የደህንነት ሪፖርት እንደተጠቀሰው “ያለፉት አስራ ሁለት ወራት እስከ ዛሬ ፀንቶ የቆየውን የሊበራል ስርዓት የሚቃወሙ ኃይሎች ድምፅ ጎልቶ የተሰማባቸው ወራት ነበሩ፡፡” ፀንቶ የቆየው ይህ ሰርዓት በበርካታ ምርጫዎች እና የህዝበ ውሳኔ ክንውኖች ሲንገዳገድ እና በፖለቲካው ሂደት የጎላ ሚና ያልነበራቸው ኃይሎች አስገራሚ ስኬት ማግኘት የቻሉበት ሁኔታ ታይቷል፡፡

ደርዘን የሚሆኑ ምዕራባዊ ዴሞክራሲዎች ውስጥ ህዝበኛ የፖለቲካ ፓርቲዎች የመንግሥትን ስልጣን መጋራት የሚችሉበት ሁኔታ ሲከሰት ተመልክተናል፡፡ እነዚህ ህዝበኛ የፖለቲካ ቡድኖች ከመራጩ ህዝብ ከፍተኛውን ድምፅ ማግኘት ባልቻሉባቸው ሐገራት ጭምር፣ በአጠቃላይ የፖለቲካ ሂደቱ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ማሳደር የሚችሉ መሆናቸው ታይቷል፡፡ የሚያገኙት ድምፅ ዝቅተኛ ቢሆን እንኳን የፖለቲካ ውይይቱን አቅጣጫ ማሳት የሚችሉና በፖለቲካ መድረኩ አውራ ተደርገው በሚታዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውሳኔ ላይ ጫና ማሳደር ችለዋል፡፡ በህዝበኛ ፖለቲከኞች ተጽዕኖ ሳቢያ ቀድሞ የሚታወቁባቸውን የፖሊሲ አጀንዳዎች በመተው ሌላ አጀንዳ ማቀንቀን የጀመሩበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

ታዲያ እንዲህ ያለውን አዲስ ክስተት ስንመለከት ልናነሳ የሚገባን መሠረታዊ ጥያቄ፣ ህዝበኛ የፖለቲካ ኃይሎች እንዲህ ማንሰራራት እና ቀና ቀና ማለት የጀመሩት ለምንድነው? የሚል ጥያቄ ነው፡፡ ብሔርተኛ ህዝበኛ የፖለቲካ አስተሳሰብ በአሜሪካና በምዕራብ አውሮፓ ብቻ ተወስኖ

☞

ሊቀር የሚችል እንደማይሆን መገመትም ይቻላል፡፡ የኒዮ-ሊበራሊዝም አስተሳሰብ ከምዕራቡ ዓለም ማህፀን ተወልዶ ወደ ሌሎች ክፍለ ዓለማት እየተስፋፋ እንደሄደ ሁሉ የህዝበኛ የፖለቲካ አስተሳሰብም ወደ አፍሪካ ምድር የመስፋፋት ዕድል ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ ግልፅ ግንዛቤ መያዝ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በጉዳዩ ላይ የተለያዩ ጥናቶችን ያደረጉ ምሁራን ሥራዎችን ዋቢ በማድረግ የህዝበኛ አስተሳሰብ መገለጫዎችን እንዳየነው፤ አሁን በሰፊው እንዲያንሰራራ ያደረጉትን ጉዳዮችን በመፈተሽ ስለ ጉዳዩ በቂ ግንዛቤ መያዝ ያስፈልግ ይሆናል፡፡

ጀርመናዊው የፖለቲካ ፕሮፌሰር ቮን ቤይም ህዝበኝነት አዲስ አስተሳሰብ እንዳልሆነ ያም ሆኖ ግን በተለይም በ20ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ ከፍተኛ ተቀባይነትን እያገኘ መምጣቱን ይገልጻል። ህዝበኛ አስተሳሰብ አራማጅ የፖለቲካ ሰብዕናዎችና ፖለቲካ ፓርቲዎች ከፍተኛ የህዝብ ድምጽ እያገኙ የመጡበት ሁኔታ በፖለቲካ ተንታኞች ዘንድ ከሁለት ዓብይ ንድፈ ሐሳቦች አንጻር ተተንትኖ ይገለጻል። አንደኛው በድህረ ኢንዱስትሪው የተካሄደው ትራንስፎርሜሽን የፈጠረው ኢፍትሀዊ የኢኮኖሚ ክፍፍልና ብዝበዛ በህዝቡ ዘንድ የፈጠረው ቅራኔ ሲሆን፤ ሁለተኛው በባህላዊ እሴቶች ላይ የተፈጠረው ለውጥ የፈጠረው ቅሬታ የሚሉት ናቸው።

## ኢኮኖሚያዊ ንድፈ ሐሳብ

በዳበረ ህብረተሰብ ዘንድ ለህዝበኛ አስተሳሰብ ማንሰራራት አንዱ ምክንያት ሆኖ የተጠቀሰው የኢኮኖሚያዊ ንድፈ ሀሳብ መነሻ ቆየት ያለ ነው። የፖለቲካል ሶሲዮሎጂ ልሂቃን የሆኑት ሲመር ማርቲን ሊፕሴትና ዳንኤል ቤል በ1950 ዎቹና በ1960ዎቹ ባደረጉት ጥናት የብዙሀኑን ንዑስ ከበርቴ መደብ፣ የአነስተኛ ቢዝነስ ሰራተኞችን፣ የባለሱቅ ነጋዴዎችን፣ በግል ስራ የተሰማሩ ዜጎችንና የነጻ ገበሬዎችን ሰፊ ድጋፍ በማግኘት አምባ ገነናዊ በሆነ ገጽታ ዘመናዊነትን በመቃወም በጀርመን ፋሺዝም፣ በፈረንሳይ ፖጃዲዝም እንዲሁም በዩናይትድ ስቴትስ ማካርቲዝም እንቅስቃሴ ሊገነግን እንደቻለ ያስረዳሉ።

☞

ጽንፈኛ አስተሳሰቦች በተለይም ተስፋ የቆረጡ፣ ስነልቦናዊ መጠለያ ያጡ፣ በግል ስራቸው ያልተሳካላቸው፣ ከማህበረሰብ የተገለሉ፣ ኢኮኖሚያዊ ዋስትና የሌላቸው፣ ያልተማሩ፣ ቀላል አስተሳሰብ ያላቸውን አምባገነን ሰዎች ቀልብ የሚስበ አስተሳሰብ እንደሆነ  ሊፕሴትና ቤል ያስረዳሉ።

የህዝበኞች ፖለቲካ ዲስኩር በተለየም ዝቅተኛ ክህሎት ያላቸውን፣ የዝቅተኛ መደብ ወይም ዝቅተኛ ደሞዝ ባለው ስራ የተሰማሩ፣ የስራ ዋስትና የሌላቸውን፣ ለማህበራዊ ጥቅሞች ያልታደሉትን በአመዛኙ ያልተማሩትን የህብረተሰብ ክፍሎች ለመማረክና ድጋፋቸውን ለማግኘት አመቺ ስልት እንደሆነ ዴንማርካዊው ሶሲዮሎጂስት እስፒንግ አንደርሰንም በተመሳሳይ በጥናቱ አመልክቷል።

በሀብትና በገቢ ምጣኔ ላይ ጥናት ያደረገው ፈረንሳዊው ኢኮኖሚስት ቶማስ ፓይክቲ በተለይም ከተወሰኑ አስርት አመታት ወዲህ በተለይም ባደጉት ሀገራት ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት ቢመዘገብም ሀብት ከሞላ ጎደል በአብዛኛው ከአስር ከመቶ በማይበልጡት ይልቁንም አንድ ከመቶው በሆነው የህብረተሰቡ ክፍሎች ቁጥጥር ስር መሆኑ በዜጎች መካከል እጅግ ከፍተኛ የሆነ የገቢ ልዩነት መከሰቱን ገልጾ ይህም ከቴክኖዎሎጂ መራቀቅ፣ እያደገ ከመጣው የሰው ሀይልና ካፒታል ዝውውር፣ ከግሎባላይዜሽን መጠናከር፣ ከሰራተኛ ማህበራት መመናመን፣ ከኒዮ ሊበራል የአውስተሪቲ እርምጃዎች፣ ከእውቀት ተኮር ኢኮኖሚ መስፋፋት፣ ከዲሞክራሲያዊ መንግስታት የቁጥጥር እርምጃ ውሱንነት፣ ከስደተኛው ቁጥር መበራከት ጋር ተያይዞ ለህዝበኛ አስተሳሰብ አራማጆች ከፍተኛ ህዝባዊ ድጋፍ ለማግኘት ምቹ ሁኔታን እንደፈጠረ ያብራራል።

በጥቅሉ ኢፍትሀዊ የሆነ የኢኮኖሚ ስርጭትና የሀብት ክፍፍል ተጠቂው ህብረተሰብ በአንድ እንዲያብር፣ በቡድን ልማዳዊ ስርአቱ እንዲተሳሰርና መጤ የሚላቸውን እንዲያገል ምክንያት ይሆነዋል። እንደዚህ አይነት ስጋት ያደረባቸው የህብረተሰቡ ክፍሎች የስራ ዋስትናና ጥቅሞችን አሳጥተውናል ከሚሏቸው ቡድኖች ነጻ የሚያወጣቸው አምባገነን ህዝበኛ የፖለቲካ መሪ መሻታቸው አይቀሬ ይሆናል። በአሁኑ ወቅት በጀልባ እየታጨቀ ወደ አውሮፓ የሚሰደደው ህዝብ መብዛት፣ በፓሪስ፣ በቤልጂየምና ኢስታንቡል

☞

በተደጋጋሚ የደረሰው የሽብር ጥቃት፣ በአውሮፓ መንግስታት የሚወሰደው የአውስተሪቲ እርምጃ ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው መመናመንና ከገቢ እድገት መገታት ጋር ተያይዞ ለተስፋ ቆራጭነትና ለህዝበኛ ፖለቲከኞች ማንሰራራት ዋነኛ ኢኮኖሚያዊ ምክንያት እንደሆነ በርካታ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ተንታኞች ይስማሙበታል።

ይህ አዝማሚያ በተለይም በአውሮፓ ለተለያዩ ፓርቲዎች ህዝባዊ ድጋፍ ለማሰባሰብ እንደ መልካም ጸጋ ሆኗል። በመካከለኛ ቀኝ አክራሪዎች አንጻር ሲታይ እያደገ የመጣው አለማዊ አስተሳሰብና የቤተ ክርስቲያናት ወንበር ኦና እየሆነ መቅረት የክርስቲያን ዲሞክራቲክ ፓርቲዎች ከፍተኛ ድምጽ እያጡ እንዲመጡ ምክንያት ሆኗል። በግራ አክራሪዎችም በኩልም የግለኝነት አስተሳሰብ ስር መስደድና የሰራተኛውን መደብ በአንድ አደራጅቶ ለማንቀሳቀስ አይነተኛ መሳሪያ የነበሩት የህዝባዊ አደረጃጀቶችና የሰራተኛ ማህበራት እየተዳከሙ መምጣት የህዝቡን ፖለቲካዊ ተሳትፎ እያዳከመው መጥቷል። የሰራተኛው ህዝብ ቅሬታውን የሚገልጽባቸው የሰራተኛ አደረጃጀቶችና ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች በአለም አቀፉ ድንበር ዘለል ግብይትና በመልቲ ናሽናል ኮርፖሬሽኖች እንቅስቃሴው ተዳክሟል።

በዚህም ማህበራዊ አገልግሎት የተነፈጋቸው የህብረተሰቡ ክፍሎች ለስራ እድል መመናመን፣ ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ እየቀጨጨ መምጣትና ለማህበራዊ አገልግሎቶች እጦት መንስኤ ናቸው በማለት ጣታቸውን ወደ አናሳ ብሄረሰቦችና ስደተኞች መዘርጋት ጀመሩ።

ህዝበኛ የፖለቲካ መሪዎችም ለንግድ እንቅስቃሴና ለታሪፍ ነክ ጉዳዮች ጥበቃ ትኩረት የሚሰጡ እንደመሆናቸው መጠን አሁን በስልጣን ላይ ያሉ መንግስታትን በድህረ ጦርነት ወቅት የነበረውን የብልጽግና ዘመንና ማህበረሰባዊ የጋራ እሴት ማስቀጠል አልቻሉም በሚል ለመክሰስና በዚያም የተሻለ ህዝባዊ ድምጽ ለማግኘት መልካም እድል ፈጥሮላቸዋል። ጥቅማችን ተነክቷል የሚሉ የህብረተሰቡ ክፍሎችም ጆሯቸውን ከመካከለኛ ግራ አክራሪዎች ወደ "የድሮ ታላቅነታችሁንና ወርቃማ ዘመናችሁን እመልሳለሁ" ወደሚሉ ህዝበኛ ፖለቲከኞች ለማዞር ተገደዋል። "አሜሪካን ወደ ቀደምት ታላቅነቷ!" የሚለው የትራምፕ መፈክርም የዚሁ አካሄድ ማሳያ ነው።

☞

በዚህም አመክንዮ የኢኮኖሚ ዋስትና እጦት ንድፈ ሐሳብ ህዝበኝነት ሰፊ የገቢ ልዩነት በፈጠረው ዓለም አቀፋዊ ኢኮኖሚ ተሸናፊ የሆኑ የህብረተሰቡ ክፍሎች በዘልማዳዊው የፖለቲካ ስርዓት እምነት ማጣታቸውንና ተቃውሟቸውን ተከትሎ የተከሰተ የፖለቲካ አስተሳሰብ እንደሆነ ተብራርቷል።

ይህ ኢኮኖሚ ተኮር አመክንዮ ሙሉ በሙሉ እውነታነትና ተቀባይነት ካለው ለህዝበኛ ፖለቲከኞች ከፍተኛ ድጋፍ የሚሰጥ መራጭ ሊኖር የሚችለው የስራ አጡ ቁጥር ከፍተኛ በሆነባቸው፣ በአለም አቀፍ ድንበር ዘለል ግብይት፣ በቴክኖዎሎጂ መምጠቅና በእውቀት መር ኢኮኖሚ ተጎጂ በሆኑ አገራት ህዝቦች ዘንድ መሆን ይጠበቅበታል።

አንዳንድ ጥናቶች ግን ይህ ኢኮኖሚ ተኮር ትንታኔ ከፍተኛ የስራ አጥ ቁጥር ባላቸው አንዳንድ አገራት ነባራዊ ሁኔታ ሙሉ ተቀባይነት እንደሌለው ያመላክታሉ። በአውስትሪያው ኤፍ ፒ ኦ፣ በጀርመን ሪፐብሊካንስና በዳኒሽ ፕሮግረስ ፓርቲ ምርጫ ድምጽ አሰጣጥ በዝቅተኛው መደብና፣ የተሻለ ገቢ በሚያስገኝ ስራ የተሰማራው ባለሙያ ድምጽ ላይ የጎላ ልዩነት ያላሳየበት ሁኔታ ተስተውሏል።

በርግጥ ካስ ሙዴ ለህዝበኛ አስተሳሰብ ማንሰራራት ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው በሚለው እሳቤ ላይ ጥርጣሬ አለው። ለዚህም ደግሞ ህዝበኛ ፓርቲዎች ከትውልድ እስከ ሞት ማህበራዊ ዋስትና ባረጋገጡ፣ የተሻለ ትምህርትና የተሻለ የኑሮ ዋስትና ለዜጎቻቸው ባጎናጸፉ፣ ለዜጎች መብትና እኩልነት ትልቅ ትኩረት በሚሰጡ እንደ ስዊድንና ዴንማርክ ባሉ ማህበራዊ ደህንነትን በአንጻራዊነት ባረጋገጡ አገራት ዘንድ ከፍተኛ ህዝባዊ ድምጽ እያገኙ የመጡበት ሁኔታ መስተዋሉን እንደ ማሳያ ይጠቅሳል። ይህ ጥናትም ለህዝበኛ አስተሳሰብ ማንሰራራት አንዱ ዓብይ ምክንያት ተደርጎ ለሚጠቀሰው የባህል ተኮር ንድፈ ሐሳብ መነሻ ሆኗል።

## የባህል ተቆርቋሪነት ንድፈ ሐሳብ

ይህ የሶሻል ስነ ልቦና አስተሳሰብ ለህዝበኛ አስተሳሰብ ማንሰራራት ዋነኛው ምክንያት ቀደምት ባህላችን እየተበረዘ፣ በ21ኛው ክፍለ ዘመን የዝምታ አብዮት ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶቻችን እየተዋጡ ስለመጡ የባህል

☞

ጥበቃ ያስፈልገናል ብለው በሚያምኑ የቀደመ ባህልና ወግ ተቆርቋሪ ወግ አጥባቂዎች ድጋፍ እንደሆነ ያመለክታል።

የዚህ አስተሳሰብ አቀንቃኞች በአመዛኙ የቀደመ ወግና ልማድን አጥብቆ ማስቀጠል በሚፈልጉ፣ በፍጥነት እየተቀየረ በመጣው የባህል ማዕበል ተገፍተን ተረስተናል በሚሉ በእድሜ የገፉና በትምህርታቸውም እምብዛም ባልገፉ የህብረተሰቡ ክፍሎች ናቸው።

ባለፈው ግማሽ ክፍለ ዘመን የምዕራቡ አለም ህብረተሰብ በአዳዲስ ባህላዊ አስተሳሰቦች፣ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችና አዳዲስ ፖለቲካዊ አስተሳሰቦች እየተለወጡ ነባር ባህላዊ እሴቶች በድህረ ቁሳዊ ባህል እየተዋጡ መምጣታቸው በተለያዩ ጥናቶች ተመልክቷል።

በወጣቱና የኮሌጅ ትምህርት በቀሰመው ትውልድ ዘንድ ለተለያዩ ጾታ ተኮር ጉዳዮችና መብቶች ብዝሀዊ አስተሳሰብን የማስተናገድ፣ ከሀይማኖት ውጪ የሆኑ እሴቶችንና ልማዶችንና ስነ ምግባሮችን የማራመድ፣ ለስደተኞች፣ ለጥገኞች፣ ለውጭ ዜጎች አዕምሮን ክፍት በማድረግ የመቀበለን፣ የባህላዊ አናኗርና አመጋገብ የመሳሰሉ ባህላዊ ልማዶች ብዝሀነትንና ስብጥረትን የማስተናገድ፣ ለአለም አቀፍ ትብብር፣ ለሰብአዊ እርዳታ እንደ የተባበሩት መንግስታትና አውሮፓ ህብረት ለመሳሰሉ የጥምር መንግስታት ተቋማትን መቋቋም መደገፍን የመሳሰሉ ዘመናዊ ባህሎችን ትውልድ በተተካ ቁጥር ይበልጥ እየተላበሰ መጥቷል።

ከ1970 እስከ 2008 ድረስ የተደረጉ በርካታ ጥናቶች የድህረ ሁለተኛው አለም ጦርነት ትውልዱ ከቁሳዊነት አልፎ በተራማጅ ድህረ ቁሳዊ እሴቶች ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተካ የአረጋዊውን ትውልድ ባህላዊ እሴቶች ቀስ በቀስ እየቀየረ መምጣቱን ያመለክታሉ።

የባህል ለውጡም ከአረንጓዴ ልማት አቀንቃኝ ፓርቲዎች መበራከት፣ ከተራማጅ የሰብአዊ መብት ተቆርቋሪ ቡድኖችና የአካባቢ ጥበቃ ተሟጋቾች መበራከት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው።

የድህረ ቁሳዊነት አስተሳሰብ አራማጆች ቁጥር እጅግ እየተበራከተ መምጣት የማህበራዊ መደብና የኢኮኖሚ ፍትሀዊ ስርጭት ጉዳይን እያሳሳው

☞

በመምጣቱ በባህል ነክ ጉዳዮችና በማህበራዊ ማንነት ጉዳይ ላይ ትኩረትን ያደረገ የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንዲያቆጠቁጥ ምክንያት ሆነ። በምዕራቡ አለም እየተበራከቱ የመጡት እነዚህ የድህረ ቁሳዊ አስተሳሰብ አራማጆች በአመዛኙ ከተማረው የህብረተሰብ ክፍል የወጡና ለተራማጅ ማህበራዊ ለውጥና ለሰብአዊ ጉዳዮች ቀዳሚ ትኩረትን የሚሰጡ ናቸው።

ይህ እንዳለ ሆኖ ይህ የድህረ ቁሳዊ አስተሳሰብ አሉታዊ ውጤትን አስከትሏል። ይኸውም የቀደመው ባህላዊ እሴቶቻችን እየተሸረሸሩ መጥተዋል የሚል ጠንካራ ስጋት በአሮጌው ትውልድ ዘንድ በጉልህ መንጸባረቁ ነው። ይህ አስተሳሰብ ዞሮ ዞሮ እድሜው እየገፋ በኀልማሳ የእድሜ ክልል ደረጃ ላይ በደረሰው የቀደመ ወጣት ትውልድም የሚንጸባረቅ እውነታ ነው። የባህል መሸርሸር ስጋቱንም የሚወልደው የኢኮኖሚ ስርጭቱ ኢፍትሀዊነት ነው።

እንደዚህም ሆኖ ግን በአንድ ወቅት ወንድ ተኮር የነበረው የበላይነት በድህረ ቁሳዊ ዘመን በሴቶች እኩልነትና በተለይም በእውቀት ተኮር ኢኮኖሚውና በፖለቲካው መስክ ሴቶች ልዩ ተጠቃሚ እየሆኑ መምጣታቸው ባልተማረውና በአብዛኛው በጾታ ወንድ በሆነው አሮጌው የአገር ተወላጅ ላይ ትልቅ ስጋት በማሳደሩ በተለያዩ የምዕራቡ አለም አገራት ወግ አጥባቂ ህዝበኛ ፖለቲከኞች ከፍተኛ የህዝብ ድምጽ እንዲያገኙ አስችሏቸዋል።

በስደተኞች፣ በአናሳ ዘሮችና ብሄረሰቦች፣ በጥገኝነት ፈላጊዎች፣ በእንግዳ ሰራተኞችና በሙስሊሞች ላይ የከፋ ጥላቻ ማንጸባረቅ ዋነኛ የነዚህ ወግ አጥባቂ ህብረተሰብ ክፍሎች ተቃውሞ መግለጫዎች ናቸው።

በስልጣን ላይ ያሉ ነባር ፓርቲዎች በአውሮፓ ከዕለት ዕለት በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ የመጣውን የስደተኞች ቁጥር ለመግታትና የስደተኞችን እንቅስቃሴ ለመግታት የሚያስችል ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረግ አለመቻላቸው ለቀኝ አክራሪ ህዝበኛ ፖለቲከኞች መገንገን ዋነኛ ምክንያት እንደሚሆን፣ ከዚህም ጋር ተያይዞ በበርካታ የአውሮፓ አገራት መጤዎችን በከፋ ሁኔታ የመጥላትንና አደገኛ የዘረኛነት አስተሳሰብን የማራገብ አካሄድ የህዝበኛ ፖለቲከኞች ድምጽ ማሰባሰቢያ ስልት ሊሆን እንደሚችል ቤትዝ ያስቀምጣል።

☞

ከዚሁ ባህል ተኮር ትንታኔ ጋር ተያይዞም የአውሮፓ ህብረት አባል አገር መሆን ነባር ባህልን በራስ ፈቃድ እንደማጥፋት አድርገው የሚቆጥሩ ህዝቦችም አሉ። ያልተጠበቀው የእንግሊዝ ከአውሮፓ ህብረት የመነጠል ህዝበ ውሳኔ ውጤትም ከኢኮኖሚያዊ ይልቅ ባህላዊ አንድምታ እንዳለው አንዳንድ ተንታኞች ይስማሙበታል። በርካታ እንግሊዛውያን እንግሊዝ የአውሮፓ ህብረት አባል መሆኗ ከኢኮኖሚ አንጻር ጥቅም እንዳለው የሚያምኑ ቢሆንም፤ ሥጋታቸው ከባህል መበረዝ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ከርቲስ የተባለው የፖለቲካ ተንታኝ ያደረገው ጥናት ያመለክታል።

ከላይ የተገለጸው ከፍላጎት አንጻር ያለው እውነታ እንዳለ ሆኖ ከአቅርቦት አንጻር ሲታይ ‹‹አሜሪካን ዳግም ታላቅ እናድርግ›› የሚለው የዶናልድ ትራምፕ መፈክርና የፖለቲካ እርምትን አልቀበልም ማለቱ የቀድሞውን ወርቃማ ዘመን ለሚናፍቁ የአሮጌው ትውልድ የህብረተሰብ ክፍሎች ትልቅ ተስፋ በመሆኑ ለህዝበኛው ትራምፕ በምርጫ አሸናፊ ሆኖ መውጣት ዋነኛ ግብአት እንደሆነ ተንታኞች ይስማሙበታል።

በጥቅሉ ሲታይ ህዝበኛ መሪዎች ከፍተኛ ድምጽ የሚያገኙት ከአሮጌው ትውልድ፣ ከወንዶች፣ የኮሌጅ ትምህርት ካልቀሰሙት፣ ተራማጅ አስተሳሰብን ከማይሹ፣ ጾታ ተኮር ጉዳዮችን፣ ሀይማኖትና ብዝሀነት ከማይቀበሉ፣ አለም አቀፋዊ ማህበረሰብን ከማይወዱ፣ የውጭ አገር ዜጎችን በክፉ ከሚጠሉ ወግ አጥባቂ የህብረተሰቡ ክፍሎች እንደሆነ፣ ይህ የባህል መበረዝ ስጋት ከኢኮኖሚ ችግር ጋር ተሳስሮ በአሁኑ ወቅት ህዝበኛ መሪዎች የፖለቲካ ስልጣን መሰላሉን በቀላሉ ለመውጣት እንዳስቻላቸው በርካታ ጥናቶች አመልክተዋል።

በሌላ በኩል፤ የህዝበኝነት አመለካከት እንዲጠናከር ያደረጉ ሦስት ሰፋፊ እና ተደራራቢ (overlapping) የሆኑ ገፊ ምክንያቶች መሆናቸውን የሚጠቅሱ እና እነዚህም ኢኮኖሚያዊ ስጋት፣ ማህበራዊ ስጋት እና የፖለቲካዊ ብቃት ችግር በሚል የሚተነትኑ ምሁራን አሉ፡፡

☞

ኢኮኖሚያዊ ስጋቱ፤ በየጊዜው እጨመረ ሲሄድ ከሚታየው የገቢ አለመመጠን እና የአማካይ እውን ገቢ (Real Income) ዕድገት ከመገታት ጋር የሚያያዝ ችግር ነው፡፡ በአብዛኛው ይህ ችግር በ1980ዎቹ በአጠቃላይ በምዕራቡ ዓለም፤ በተለይም በማርጋሪት ታቸር ትመራ በነበረችው እንግሊዝ እና በፕሬዚዳንት ሮናልድ ሬጋን ትተዳደር በነበረችው አሜሪካ ከተከሰተ የፖለቲካ አመለካከት ለውጥ ጋር ተያይዞ የመጣ ችግር ነው፡፡

ከሃያኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አካባቢ አንስቶ፤ በዓለም የተካሄዱት ሁለት ታላላቅ ጦርነቶች በፈጠሩት ጫና፣ ‹‹ታላቅ የኢኮኖሚ ቀውስ›› (The Great Depression) ተብሎ ከሚጠቀሰው የኢኮኖሚ ቀውስ፣ ከድህረ ጦርነቱ የመልሶ ግንባታ ጥረት እና ከዌል ፌር ስቴት መፈጠር ጋር ተያይዞ፤ የገቢ አለመመጣጠን ችግር በእጅጉ ቀንሶ ነበር፡፡ በወቅቱ የነበረው ለውጥ በተለይ በአሜሪካ እጅግ ጎልቶ የሚታይ ነበር፡፡

በአሜሪካ ከ1946 እስከ 1980 ባሉት ዓመታት፤ በሐብት መሰላሉ ግርጌ የሚገኙት ሰዎች 50 በመቶ የሚሆኑት አሜሪካውያን እውን ገቢ በ102 በመቶ ጭማሪ ሲያሳይ፤ በሐብት መሰላሉ አናት የሚገኙት የ0 ነጥብ 1 በመቶው የሚሆኑት አሜሪካውያን እውን ገቢ ደግሞ በ54 በመቶ በመጨመሩ፤ የገቢ አለመመጣን ችግሩ እጅግ ወርዶ ነበር፡፡ ነገር ግን ከ1980 እስከ 2014 ባሉት ዓመታት ተቃራኒ ሁኔታ የታየበት ሆነ፡፡

ከ1980 እስከ 2014 ያሉት ዓመታት፤ የታቸር እና የሬጋን መንግስታት አክራሪ የነጻ ገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ተግባራዊ መሆን የጀመሩበት እና ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ቀውስ የተከሰተበት ዘመን ሲሆን፤ በተጠቀሱት ዓመታት ውስጥ በሐብት መሰላሉ ግርጌ የሚገኙት 50 በመቶ የሚሆኑት አሜሪካውያን እውን ገቢ አንድ በመቶ ብቻ ዕድገት ሲያሳይ፤ በሐብት መሰላሉ አናት የሚገኙት የ0 ነጥብ 1 በመቶው የሚሆኑት አሜሪካውያን እውን ገቢ ግን በ321 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡ ይህ ነገር በአሜሪካ በጣም ጎልቶ ከመታየቱ በቀር በሌሎች ሐገሮችም ያለው ሁኔታ ተመሳሳይ ነው፡፡

☞

ሆኖም የህዝበኝነት መስፋፋት ከገቢ አለመመጣጠን ጋር ብቻ ተያይዞ የሚታይ ችግር አይደለም፡፡ ለምሣሌ፤ በፈረንሳይ እንደ አሜሪካ የተጋነነ የገቢ አለመመጣጠን ችግር አይታይም፡፡ ነገር ግን በቅርቡ በተካሄደው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ከፈረንሳይ መራጭ ህዝብ ግማሹ፤ በመጀመሪያው ዙር ምርጫ ዋና ተደርገው ለማይታዩ እጩዎች ድምጽ የሰጠበት ሁኔታ ታይቷል፡፡ ስለዚህ ጉዳዩ ከኢኮኖሚ ጋር ብቻ የሚያያዝ አይደለም፡፡

በሌላ በኩል፤ በበለፀጉት ሐገራት የገቢ አለመመጣጠን ከፍ ብሎ ሲታይ፤ ግሎባላዊ የገቢ አለመመጣጠኑ ዝቅ ማለቱ ይታያል፡፡ ይህም የዳበሩት እና የዕድገት ጎዳና መከተል የጀመሩት ኢኮኖሚዎች የግሎባላይዜሽን ክስተት ባመጣው በጎ ዕድል ተጠቃሚ በመሆናቸው ነው፡፡ ስለሆነም፤ ከ1988 እስከ 2008 ዓ.ም ባሉት ዓመታት በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው የእውን ገቢ መጠን ስርጭት ተለውጧል፡፡ የቻይናን ጨምሮ፤ በገቢ ስርጭቱ መካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ፤ የበርካታ አዳጊ ኢኮኖሚ ሐገራት ሠራተኞች ባለፉት 20 ዓመታት በጣም ከፍተኛ የገቢ ዕድገት ለማግኘት ችለዋል፡፡ በከፍተኛው የገቢ እርከን ላይ የሚገኙት የበለፀገ ኢኮኖሚ ሐገራት ሠራተኞች ጉዳይም ተመሳሳይ ነው፡፡ ሆኖም ከዝቅተኛው እስከ መካከለኛው አርከን መነሻ ያሉት ሠራተኞች የገቢ መጠን (የአሜሪካን ጨምሮ) በአብዛኛው መሻሻል ሳያሳይ ባለበት ሲረግጥ ቆይቷል፡፡ ይህ ሁኔታም በተጠቀሰው የገቢ እርከን የሚገኙት ሠራተኞች በራሳቸው ሐገር በሚገኙ ባለከፍተኛ ገቢ ሰዎች ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሐገራት ባሉ ሰዎች ገቢያቸው እንደተወሰደባቸው አድርገው እንዲያስቡ አድርጓቸዋል፡፡ ይህ የገቢ ስርጭት ለውጥ ማህበራዊ ስጋት ፈጥሯል፡፡ ዜጎች በስደተኞች፣ በንግድ፣ በግሎባላይዜሽን እና በቴክኖሎጂ ጉዳዮች ግፊት በተፈጠሩ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ለውጦች ሳቢያ ችግር ላይ ወድቀዋል፡፡

በዚህ ስጋት ውስጥ ወሳኙ ነገር እውነታው ሳይሆን በሰዎች ዘንድ ያለው አስተሳሰብ (Perception) ነው፡፡ ዜጎች ለህዝበኛ ፓርቲዎች በሚሰጡት ድምጽ እና በስደተኞች ቁጥር መጨመር መካከል ዝምድና ማግኘቱ አስቸጋሪ ቢሆንም፤ የስደተኞች ቁጥር መጨመር ጉዳይ በእንግሊዝ ከአውሮፓ ህብረት የመነጠል የውሳኔ እና አሁን ባለው በፈረንሳይ የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ ወሳኝ ሚና ያለው መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም፡፡

☞

በፖለቲካ ሂደት የህዝብ ግምት እና አስተሳሰብ ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ፣ ህዝበኞቹም ሆነ ሌሎች ፓርቲዎች የህዝብ ግምት እና አስተሳሰብ ይጠቀሙበታል፡፡ ይሁንና ለህዝበኛ ፖለቲከኞች ስኬት ወሳኙ ጉዳይ የፖለቲካ ስርዓቱ ብቃት ማጣት ነው፡፡ ስርዓቱ ችግራችንን ሊፈታ አይችልም ወይም ‹‹ለግሎባል ልሂቃን›› አገልጋይ የሆነ ስርዓት እንጂ ለእኛ የሚፈይደው ነገር የለም በሚል አስተሳሰብ በተራው ህዝብ ዘንድ ህዝበኛ ፖለቲካኞች ምቹ መደላድል ያገኛሉ፡፡ ስለሆነም ይህን አስተሳሰብ ለመቀየር የሚያስችል ሁኔታ ካልተፈጠረ በቀር፣ አዲስ የፖለቲካ ክስተት ሆኖ ብቅ ያለው ህዝበኝነት የመጨመር እንጂ የመቀነስ አዝማሚያ ሊይዝ አይችልም፡፡ ችግሩን ዓይናችንን በመዝጋት፣ እጃችንን አጣጥፈን በመቀመጥ እና ‹‹እንዳመጣጡ ይመለሳል›› የሚል ስትራተጂ የሚበጅ አይሆንም፡፡ ይልቅስ፣ መለስ ብለን በታሪክ ሂደት የተከሰቱትን የህዝበኛ እንቅስቃሴዎች በመመርመር እና ትምህርት በመቅሰም ችግሩን ለመከላከል መጣጣር ይኖርብናል፡፡

## 3. እየተለወጠ ባለ ዓለም ውስጥ የሚደረግ የአለም አቀፍ ግንኙነት

አሁን በብዙዎቹ ሃገራት ዘንድ እየተከሰተ ያለው አዝማሚያ ከዓለም አቀፍ ግንኙነት አንጻር ሊኖረው የሚችለውን ተጽዕኖ ቢያንስ በሁለት ከፍሎ ማየት ተገቢ ይሆናል።

በመጀመርያ በእንደዚህ አይነቱ ሁኔታ ወቅት እየተጋጋለ ከሚመጣው አክራሪ ሃገራዊነት ጋር ተያይዞ የሚከሰተውን ምስቅልቅል ማጤን ያስፈልጋል። የህዝበኝነት እንቅስቃሴ በስፋት በሚታይባቸው ሀገራት ዘንድ የሚገኙ በርካታ ዜጎች ለገጠማቸው ችግር ተጠያቂ ከሚያደርጓቸው ወገኖች ከላይ ለመጥቀስ የተሞከረው እንደተጠበቀ ሆኖ የግሎባላይዜሽንን ያክል ለውግዘትና ለእርግማን የተመቸ ይኖራል ተብሎ አይወሰድም። ግሎባላይዜሽን ለሰፊ የስራ መታጣትም ሆነ ለሀገራዊ ኢኮኖሚው ተወዳዳሪነት መቀነስ፣ እንዲሁም ላልተገራ የስደተኞች ፍልሰት ተጠያቂ ከመሆን አልፎ ለሀገራዊ ኩራትና ክብር መቀመቅ መግባት ተጠያቂ ይሆናል። ወትሮውኑም በጥንቃቄ ካልተያዘ በስተቀር ግሎባላይዜሽን እንደ ስርአት የሚያስከትላቸው የፍትሃዊ ተጠቃሚነት ጥያቄዎች ታክለውበት ሀገራቱ ሁሉ ከዚህ ማዕቀፍ በመውጣት ወደለየለት የኢኮኖሚም ሆነ የፖለቲካ አርበኝነት የሚሸሹበት

☞

ሁኔታ ይፈጠራል። በዚህ ጊዜ ከምዕተ ዓመት በኋላ ጊዜ ያለፈባቸው ተብለው ይታመኑ የነበሩ እንደ ፕሮቴክሽኒዝም፣ ታሪፍ የመሳሰሉ ውድድር ገዳይ እርምጃዎች የሚኗቸው ብቅብቅ ማለታቸው አይቀርም። እነዚህና መሰል እርምጃዎች ከአጭር ጊዜ አንፃር ጠቀሜታ ያላቸው መስለው ቢታዩም ለችግሩ መከሰት የአንበሳውን ድርሻ የሚይዘውን ግልብ ሊበራልና ኒዮ ሊበራል ካፒታሊዝም በአሁኑ ወቅት የደረሱበትን ከባድ መዋቅራዊ ቀውስ መፍታት እስካልተቻለ ድረስ እንደ ዘላቂ መፍትሄ ያለው ፋይዳ እዚህ ግባ የሚባል ሊሆን አይችልም።

ይልቁንም እነዚህ ኣካሄዶች በሃገራት መካከል ለረዥም ጊዜ የቆዩ ትብብሮችም ሆነ ይነስም ይብዛም በጋራ ተጠቃሚነት መንፈስ ይደረጉ የነበሩ የንግድ ግንኙነቶች ተዳክመው ወደ ለየለት ፍጥጫ የሚያመሩበት ሁኔታን ይፈጥራሉ። አሁን ባለንበት ወቅታዊ ሁኔታ የንግድ ጦርነቶች ወደ ጦር መሳሪያ ግብግብ የሚያድጉበት ዕድል ትርጉም ያለው ነው ባይባልም ፍጹም አርበኝነት የወለዳቸው ኢኮኖሚያዊ ፍጥጫዎች ግን እዚህም እዚያም መከሰት መጀመራቸውን መካድ አይቻልም።

ለዚህም በአሁኑ ሰዓት በዩናይትድ ስቴትስ እየተከሰተ ያለውን ማየት ብቻውን የጉዳዩን አደገኝነት ለማየት ያግዘናል። የፕሬዝዳንት ትራምፕ አስተዳደር ስልጣን በያዘ በሁለተኛው ቀን ያደረገው ነገር ቢኖር በምርጫ ዘመቻ ወቅት ቃል በገቡት መሰረት ከትራንስ ፓስፊክ የንግድ ትብብር ማዕቀፍ መውጣት ነበር። ይህ በፕሬዚዳንት ኦባማ አስተዳደር በኤሽያ፣ በላቲን አሜሪካና በሰሜን አሜሪካ መካከል ጠንካራ የንግድ ግንኙነት በመገንባት የግጭትና የአውዳሚ ንትርክ ቀዳዳዎችን ይደፍናል የተባለለት ትራንስ ፓስፊክ ትብብር ለአሜሪካውያን ያለው ፋይዳ ምንም ይሁን ምን ፕሬዝዳንት ትራምፕ ከሚያራምዱት የአሜሪካ ትቅደም ፖለቲካ ጋር አብሮ መሄድ ስላልቻለ ዋነኛዋ ዘዋሪ ሀገር ይሁንታዋን ነፍጋው ተቀባይነት ሊያጣ በቅቷል። እርግጥ በአሜሪካ ማፈግፈግ ሳቢያ የተፈጠረውን ክፍተት ቻይና እንደ ትልቅ ዕድል ቆጥራ ልትጠቀምበት እየተንቀሳቀሰች ቢሆንም ሌሎች መሰል ስምምነቶች ለወደፊትም አደጋ ላይ ስላለመውደቃቸው ዋስትና የለም። በዚህ ረገድ የሰሜን አሜሪካ ከታሪፍ ነፃ የንግድ ቀጠና

☞

ወይም ናፍታ አደጋ ላይ እንደወደቀ ሁሉም የሚመለከታቸው ወገኖች የሚስማሙበት ጉዳይ ነው።

ከትብብር ማዕቀፎች በተጨማሪ በሀገራት መካከል የሚደረጉ የንግድ ልውውጦችም ቢሆኑ ከዚህ ፈተና ነፃ ናቸው ብሎ መውሰድ አይቻልም። የሌሎችን ሀገራት ጉዳይ ለጊዜው ትተን በሁለቱ ታላላቅ ልዕለ ኃያላን በዩናይትድ ስቴትስና በቻይና መካከል ከፕሬዝዳንት ትራምፕ መመረጥ ወዲህ እየታዩ ያሉ ሁኔታዎችን ባጭሩ መቃኘት ስለ ጉዳዩ የተሻለ አረዳድ እንዲኖር የሚያግዝ ይመስለናል። በአሜሪካ ምርጫ ዘመቻ ወቅት በተደጋጋሚ ከሰማናቸው ጉዳዮች አንዱ የቻይናውያን ዕድገት ምን ያክል በአሜሪካውያን ጫንቃ ላይ እንደተመሰረተና ይህንንም በፍጥነት የማስተካከል አስፈላጊነት ነው። በርግጥ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው የንግድ ግንኙነት አሁን ደርሶበት ያለው ደረጃ በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት አሜሪካና የቀድሞዋ ሶቪየት ህብረት በኑክሌር አረር ቁጥር ደርሰውበት ወደ ነበረው በጋራ የመጠፋፋት ወይም ሚችዋሊ አሹርድ ዲስትራክሽን ጫፍ ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ይታመናል። ይህም ማለት በሁለቱ ዘንድ የሚደረግ መጠቃቃት ዞሮ ዞሮ ሁለቱንም ከማጥፋት አይመለስም እንደማለት ነው።

ይሁንና አሜሪካ በአሁኑ ወቅት በተለይም በፕሬዚዳንት ትራምፕ አክራሪ ብሄርተኛ አማካሪዎችና ደጋፊዎች ዘንድ የአሜሪካን ታላቅነት ለማስመለስ እስከ ጦርነት ድረስ ልንሄድ ይገባል የሚል ፉከራ ማድመጥ አዲስ ነገር መሆኑ አብቅቶለታል ማለት ይቻላል። እንዲያውም ግርሃም አሊሰን የተባለ ፖለቲካል ሳይንቲስት Destined for war; Can America and China Escape Thucydides's Trap? በሚለው መፅሀፉ እንደሚሞግተው በሁለቱ ሃያላን መካከል በስተመጨረሻ አካባቢ ግጭት ሊፈጠር የሚችልበት ዕድል ሰፊ ነው። ሁለቱ ሀገራት አሁን ባላቸው ተነፃፃሪ ወታደራዊ አቅም ብቻ ሳይሆን በንግድ ልውውጥ፣ በቴክኖሎጂ መደጋገፍ፣ እንዲሁም አንዱ ለሌላው ካለው ከሞላጎደል የማይተካ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አንፃር ወደለየለት ግጭት የመገባት ዕድሉ በጣም አነስተኛ እንደሆነ በርግጠኝነት መናገር ይቻላል። ነገር ግን ጦርነት ሙሉ በሙሉ ዝግ ነው ብሎ መደምደም ያስቸግራል፡፡

☞

ያም ሆኖ እያደገ የመጣው ወደየራስ አምባ የሚደረግ ሽሽት አሁን እየተፈጠረ ላለው ምስቅልቅል ያለ ሁኔታ አሉታዊነቱ ያመዘነ ተፅዕኖው ቀላል እንዳልሆነ መገንዘብ ያሻል።

ከዓለም አቀፍ ግንኙነት አንፃር በምዕራቡ ዓለም እየታዩ ያሉ ክስተቶች ተፅዕኖ የሚያሳርፍበት ሁለተኛው ዓቢይ ጉዳይ የባለብዙ ወገን መድረኮችን የሚመለከት ነው። ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርነው በተለይም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ በስራ ላይ ያለው በህግ ላይ የተመሰረተ (Rule Based) ሥርዓት ከሞላጎደል ተገማችነት (Forecasted) ያለውና በሀገራት መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶችን እየገዛ የመጣ መሆኑ ይታወቃል። የተባበሩት መንግስታት፣ የአውሮፓ/አፍሪካ ህብረት፣ የዓለም የንግድ ድርጅት፣ ኔቶ ወዘተ የመሳሰሉት ተቋማት ከነብዙ ችግሮቻቸውም ቢሆን ለአህጉራዊም ሆነ ለከባቢያዊ ሰላም ያደረጉት አስተዋፅኦ ቀላል አይደለም። ሌላውን ትተን በተባበሩት መንግስታት ማዕቀፍ ውስጥ ከኮሌክቲቭ ሴኩሪቲ፣ ከሰብዓዊ ቀውስ አፈታት፣ ብሎም ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ እየተሰሩ የመጡ ሥራዎች አሁን በመከሰት ላይ ባሉ እድገቶች ባንድ ወይም በሌላ መልኩ አጣብቂኝ ውስጥ መግባት መጀመራቸውን ማየት ችለናል። የተመድን ይሁንታ ሳይጠይቁ የሃይል እርምጃ የመውሰድ አባዜ ሃያላኑን መጠናወት ከጀመረ ውሎ ያደረ ቢሆንም አሁን ባለንበት ወቅት ከመቼውም በተለየ መልኩ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል መገመት ይቻላል። የዩናይትድ ስቴትስ ከፓሪሱ የአየር ንብረት ስምምነት መውጣት፣ ለኔቶም ሆነ ለተመድ ያላትን ግዴታና ቁርጠኝነት እንደገና እንደምታጤነው ይፋ ማድረጓ ወዘተ መልቲ ላተራል መድረኮች እየገቡበት ያለውን ፈታኝ ወቅት የሚጠቁም ይመስለናል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ከፀረ ሽብር ትግል፣ ከሰላም ማስከበር፣ ከዓለምአቀፍ ፀረ ወንጀል እንቅስቃሴም ሆነ ሌሎች ባለብዙ መድረኮችን የሚሹ ሥራዎች መንገራገጭ የበዛባቸው ሊሆኑ የሚችሉበት ዕድል እየሰፋ ሊሄድ እንደሚችል ታሳቢ ማድረጉ ተገቢ ነው። በርግጥ አሁን ባለንበት ሁኔታ እያጋጠሙ ያሉ ፈተናዎች ለአዳዲስ መፍትሄዎችና ለአዳዲስ አደረጃጀቶች በር የሚከፍቱበት እድል ዝግ አይደለም። የዩናይትድ ስቴትስን ከፓሪሱ

☞

ስምምነት መውጣት ተከትሎ ቻይናና አውሮፓ፣ እንዲሁም የአሜሪካ ከትራንስ ፓስፊክ ለመውጣት መወሰን ተከትሎ በቻይናና በሌሎቹ የአጋርነቱ አባላት በኩል የታየው ተነሳሽነት መልካም አጋጣሚዎች ጨርሰው እንዳልጠፉ አመላካች ነው። ይሁንና ከተሳታፊው ብዛትና ከሁከቱ መበርከት አንፃር በዚህ ውጥንቅጡ በወጣ ዓለም ውስጥ ሆነን ወደ እውነት የተጠጋ ተገማችነት ሊኖር እንደማይችል መገንዘቡ ተገቢ ይሆናል።

## 3.1. ህዝበኛ አመለካከትን መከላከል

የ20ኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ታሪክ የኬይነሲያን ሶሻል ዲሞክራሲና የኒዮ ሊበራሊዝም ተረክ ዘመን ተብሎ ሊገለጽ ይችላል ይላል፤ እንግሊዛዊው የፖለቲካ ተንታኝና የአረንጓዴ ፖለቲካ አስተሳሰብ አራማጅ ጆርጅ ሞኒቦት። ለዘመናት እየሰማን የመጣነው አስተሳሰቡ በአሁኑ ወቅት ከጨዋታ ውጭ እየሆነ የመጣውን የኬይነሲያን ፖለቲካል ኢኮኖሚ አስተሳሰብና ተጨባጭ ትርጓሜ የሌለውን ነገር ግን ያለ ግልጽ ማንነቱ ዓለምን በተሳሳተ አቅጣጫ እየነዳ ያለውን የኒዮ ሊበራሊዝም ተረክን ነው።

የኬኔሲያን አስተሳሰብ ኢኮኖሚ ተኮር ብቻ በመሆኑ ለኢኮኖሚ እድገት መሰረታዊ ለሆኑት ለሰው ሀብት ደህንነትና ለኢኮኖሚ ምንጭ ለሆነችው ዓለማችን አካባቢያዊ ደህንነት ደንታ ቢስነቱን ሲያሳይ መኖር የሚችለው ተፎካክሮ ያሸነፈ ብቻ ነው በሚል አካሄድ ከሰብአዊ አስተሳሰብ ያፈነገጠውና ፉክክርንና አሸናፊው ተሸናፊውን ጨፍልቆ የመግዛት ገበያዊ መብት አለው የሚለው የኒዮ ሊበራሊዝም አስተሳሰብ ለአለም አቀፍ የፖለቲካና አካባቢያዊ ቀውሶች ዋነኛ ምክንያት እንደሆነ ሞኒቦት how do we get out of this mess? በሚል ርዕስ ባሰፈረው ጽሁፍ ትንታኔውን ያስቀምጣል።

ኒዮ ሊበራሊዝም ሰዎችን ሸማች በሚል እንደ እቃ የመቁጠር አስተሳሰብን የሚያራምድ፣ በንግድ እንቅስቃሴው ቁጥጥር ማድረግ አያስፈልግም፣ ማህበራዊ ግልጋሎት መስጫ ተቋማት በግል ይዞታ ሥር መሆን አለባቸው የሚል፣ የተለያዩ የሰራተኛ አደረጃጀቶች መኖር፤ የአሸናፊው መኖርና የተሸናፊው መጥፋት ተፈጥሯዊ ስርአትን መቃረን ☞

አድርጎ የሚያይ፣ በሰዎች መካከል እኩል የሆነ ፍትሐዊ የሐብት ክፍፍልን እንደ ሞራል ዝቅጠትና ጸረ ዕድገት አድርጎ የሚመለከት፣ ለእያንዳንዱ የእጁን የሚሰጠው ገበያው ነው የሚል ሰብአዊ ያልሆነ እጅግ ጥቂት ለሆኑት ከብሮ መኖር እና ለብዙሃኑ ደግሞ መጥፋት ጥብቅና የሚቆም የማይጨበጥ አስተሳሰብ ነው ሲል የኒዮሊበራሊዝም አስተሳሰብን ይኮንናል።

የኒዮ ሊበራሊዝም አስተሳሰብ በዜጎች መካከል ከፍተኛ የገቢ ልዩነት በመፍጠርና ስራ አጥነትን በማስፋፋት እንደ ፋሺዝምና ስታሊኒዝም የመሳሰሉ አክራሪ ህዝበኛ ፖለቲከኞች እንዲያንሰራሩና የኒዮሊበራሊዝም አስተሳሰብ መልኩን ቀይሮ ይበልጥ በከፋ መልኩ እንዲስፋፋ ምክንያት መሆኑንም ያብራራል።

የተበላሹና የማይሰሩ አስተሳሰቦች ሊተኩ የሚችሉት በምርጥና ለውጥን በሚቀሰቅሱ አስተሳሰቦች ነው። ስለዚህ ለዘመናት ስንሰማው የነበረውን የኬኔሲያን እና የኒዮሊበራሊዝም የተሳሳተ ትርክት በሌላ ምርጥና በጋራ ሊያሳድገን በሚችል ትርክት መቀየር የመጀመሪያው የመፍትሄ እርምጃ እንደሆነ ሞንቢየት አስቀምጧል።

ይህንንም ወደ ተግባር ለመቀየር እና ሁለቱን የማያስኬዱ የፖለቲካል ኢኮኖሚ አስተሳሰቦችን በተሻለ የጋራ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ አካሄድ ለመተካት በአንድነት ማበር እንደሚያስፈልግም ይገልጻል። ጆርጅ ሞንቢዮት መፍትሄውን የሚያስቀምጠው ከሰዎች የመተሳሰብ ተፈጥሮአዊ ባህርይ በመነሳት ነው። የተለያዩ ሰብአዊ የጤናና ቁሳዊ ችግሮቻችንን ለመፍታት በሳይንሳዊ ምርምር በርካታ መፍትሔዎችን ለሰው ልጆች አበርክቶልናል። ይህም ሰዎች ማህበራዊ ፍጡራን እንደመሆናችን መጠን ለሌሎች የማሰብ ደመ ነፍሳዊ ዝንባሌና ፍላጎት እንዳለን የሚያሳይ ነው። በብዙ ሚሊየን ዓመታት አዝጋሚ ለውጥ እንደ ዳይኖሰር ያሉ ግዙፍ ፍጡራን መኖር አቅቷቸው ሲጠፉ፤ ሰዎች ግን በጋራ በመተባበር ብዙ ተፈጥሯዊ ፈተናዎችን በህብረት ተቋቁመን ማለፍ ችለናል።

ለዘመናት ያካበትናቸው ማህበራዊ እሴቶች ሁሉንም ዓይነት ማህበራዊና ባህላዊ ብዝሃነት አቻችሎ የማስተናገድ፣ እኛ ከምንኖርበት

☞

አገር ውጪ የመጡ ሰዎችን የማንፈራ፣ ሰብአዊ ፍጡር እንደመሆናችን መጠን፤ ለሌላው የማሰብ ተፈጥሮአዊ ስብእናችንን የማውጣት፣ በእርሱ አገላለጽ የእኔነት ፖለቲካን ተግባራዊ ማድረግ ብቻ ነው የሚጠበቅብን ሲል በአጽዕኖት ይገልጻል።

ታዲያ ህዝበኝነት በብቃት መከላከል የሚቻለው የኒዮሊበራል አስተሳሰብ የፈጠረው ቀውስ መሆኑን በመረዳት፤ አስተሳቡን በአዲስ ሁሉም ወገኖች በሚጠቅም፤ የልማታዊ መንግስት አስተሳሰብን በማስፈን ነው፡፡

የኒዮ ሊበራል አስተሳሰብ በምዕራቡ ዓለም ሰማይ ምድር በሰፊው የተንሰራፋ በመሆኑ፤ አንዳንዴ የርዕዮት ዓለም ጓዝ የተሸከመ አስተሳሰብ መሆኑም ይዘነጋል የሚለው ሞንቢዮት፤ የኒዮሊበራል አስተሳሰብ በስርዓቱ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ጭምር ግራ አጋቢ መሆኑን ይጠቅሳል፡፡ ህዝቡ የስርዓቱን ችግሮች እንዳይገነዘብ፤ ኮርፖሬት ፕሬሶች እና በእነዚሁ ኮርፖሬቶች የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ‹‹ቲንክ-ታንኮች›› አሁን ፀንቶ በሚገኘው የኒዮ-ሊበራል ስርዓት ላይ የሚሰነዘሩ ትችቶች ከህዝብ ጆሮ እንዳይደርሱ መንገድ በመዝጋት፤ በስርዓቱ ላይ የሚሰነዘሩ ማናቸውንም ሂሶች በማድበስበስ እንደሚሸፍጡ ያስረዳል፡፡

የአክራሪ ገበያ መርህ አቀንቃኝ የሆኑ ቲንክ-ታንኮች ብዙ ጊዜ የሚሰጡት ምክረ-ሃሳብ፤ የኮርፖሬት ኃይል እንዲጠናከር እና የትልልቅ የንግድ ድርጅቶችና የበዛ ሐብት ያላቸው ግለሰቦች ፍላጎት በፖሊሲ ቀረፃ ሂደት ትኩረት እንዲያገኙ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ አሁን ዓለምን ወጥሮ የያዛት ቀውስም የተፈጠረው በዚህ ነው፡፡

የምዕራቡ ዓለም ሚዲያዎች የሚሰሩትን የዜና ዘገባ፤ ኮርፖሬቶቹ ከሚያወጧቸው የዜና መግለጫዎች ለይቶ ማየት የሚያስቸግር ሆኗል፡፡ የኢኮኖሚያዊ ምርምሮችን ይዘው የሚወጡ ጆርናሎች ዋጋም የማይቀመስ የሆነው የኪራይ ሰብሳቢ ካፒታሊዝም (Rentier Capitalism) ተግባር ሲሆን፤ ይህም የህዝብ አእምሮ እንዲመክን (Stifling of the Public Mind) አድርጓል፡፡ይህም የገኘው መደብ የርዕዮት ዓለም ማስረጫ ዘዴ ሆኖ እያገለገለ መሆኑን ፀሐፊው ያስረዳል፡፡

☞

የሞንቢዮት ድምፅ በስርዓቱ ላይ የተሰነዘረ የቁጣ ድምፅ ነው፡፡ ፀሐፊው፤ የምዕራቡን ዓለም የግለኝነት አስተሳሰብ (Individualism) አምርሮ ይተቻል፡፡ "ብቸኝነት ገደብ የለሽ ውፍረት ከሚያስከትለው ሞት በእጥፍ የሚልቅ ሞት የሚያስከትል ነው፡፡ (Loneliness is twice as deadly as obesity)" ይላል፡፡

አጥንት ዘልቆ የሚሰማ ስድብ ተደርጎ የሚታሰበው እንደ ስድብ ‹‹ሉዘር›› የሚል ስድብ ነው፡፡ ለምን እንደሚያደርገው ሳያውቅ በደመ-ነፍስ የውድድር መንፈስ ውስጥ በመግባት እና ‹‹የአይጦች እሽቅድድም›› (Rat-racing) በመሰለ ሁኔታ ሊገለጥ ከሚችለው የምዕራቡ ማህበረሰብ አስተሳሰብ የተነሳ ‹‹ሉዘር›› (በውድድር ተሸናፊ) ተብሎ መነቀፍ ከሞት የሚቆጠር ስድብ ሆኖ ይታያል፡፡

በዚህ የተነሳ ሃብት ሞልቶ የተረፋቸው ባለፀጎች እንኳን ደስታ የራቃቸው ናቸው፡፡ ደስታ በራቀው የደስታ መሻት ጥረት ተዘፍቀን ሁሉንም ገንዘብ ሊገዛው የሚችለውን የፍጆታ ሸቀጥ ፈጅተን፤ አሁን ራሳችንን እንደ አውሬ መብላት ጀምረናል›› ይላል፡፡ የምዕራቡ ዓለም ዜጎች፤ መዛነፍ በሌለው እኩል ዕድል፤ ብቃት ያላቸውን ሰዎች ሊሸልም በሚችል ፍፁም የሆነ ስርዓት (Meritocracy) የሚኖሩ አድርገው ስለሚቆጥሩ ‹‹ለውድቀቶቻቸው ተጠያቂ የሚያደርጉት ራሳቸውን ነው›› በማለት ስርዓቱን ይተቻል፡፡

"ተገቢውን ወይም አስፈላጊውን ጥረት ካደረግን ከልሂቃኑ ሰልፍ መግባት እንችላለን የሚል እምነት እንድንይዝ ተደርገናል፡፡ ገና ከዕድሜያችን ማለዳ ጀምሮ በውድድርና በአሃዛዊ ሚዛን ሰፍሮ በማነፃፀር ሥራ እንጠመዳለን፡፡ ግለኝነት የህይወትን ገፅታዎች ሁሉ እንደቅጠል አርግፎታል፡፡ ሰዎች አላፊ ጠፊ የፍጆታ ሸቀጥ በመሸመት ደስታን አሳድዶ የመያዝ ጥረት ውስጥ እንዲገቡ አድርጓቸዋል፡፡ ተፈጥሮአዊውን ዓለም የማውደም ስራ ውስጥ አስገብቶናል›› ይላል፡፡ የኒዮ-ሊበራሊዝም አስተሳሰብ በአግባቡ ተፈትሾ መፍትሔ ካልተቀመጠ፤ ከአንዱ ድቀት ወደ ሌላው ድቀት እየተሸጋገርን መቀጠላችን የማይቀር መሆኑን በመግለጽ ሥጋቱን ያንጸባርቃል፡፡

☞

ከ2007 እስከ 2017 ባሉት ዓመታት በበለፀጉ ሀገራት የሚኖረው የአብዛኛው ዜጋ ዓመታዊ ገቢ ባለበት ሲረግጥ ቆይቷል ወይም አሽቆልቁሏል፡፡ይህም ለህዝበኛ ፓርቲዎች መነቃቃት ምክንያት ሆኗል፡፡የቀኝ አክራሪ ህዝበኛ ፓርቲዎችም በፖለቲካ ምህዳሩ ሥፍራ እያገኙ፣ ድንበር ተሻጋሪ የሆነ ህብረት እየፈጠሩና እየተጠናከሩ መጥተዋል፡፡ አሁን በምዕራቡ ዓለም የሚካሄደው ትግል ወይም ፖለቲከኞችን ማዶ ለማዶ ያሰለፈው እና በመካከላቸው አጥር ሆኖ የቆመው ጉዳይ አይዲዮሎጂ አይደለም፡፡ ስለዚህ የፖለቲካ ጎራው የተከፈለው የግራ እና የቀኝ ፖለቲከኞች በሚል ሳይሆን፤ ዓለም አቀፍ አመለካከትን በሚደግፉ ሊበራሎች (Liberal Cosmo-politans) እና በህዝበኛ ፖለቲከኞች (አንዳንዴም መጤ-ጠል በሆኑ ጥብቅ የአስተዳደር ዘይቤ ደጋፊዎች) መካከል የተከፈለ ጎራ ሆኗል፡፡

ህዝበኛ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምዕራቡ ማህበረሰብ የሚታየውን የባህል መዘመን ወይም ለውጥን አይቀበሉም፡፡ ሉላዊነት ‹‹ሀገራችንን ለሥጋት ዳርጓታል›› ብለው የሚያስቡትን ነገር ሁሉ ይቃወማሉ፡፡ ይህም ከስደተኞች እና ዓለም አቀፍ አመለካከት ካላቸው ልሂቃን ጀምሮ የዓለም አቀፍ ተቋማትን የሚመለከት ተቃውሞ ነው፡፡ እነዚህ ፖለቲከኞች የሊበራል ዴሞክራሲ አላባውያን የሆኑትን የአመለካከት ወይም የባህል ብዝሃነትን እና ሊበራሊዝምን የሚያጣጥሉ ናቸው፡፡

ህዝበኛ ፖለቲከኞች የህዝብን ስሜት በመኮርኮር የቅስቀሳ ፖለቲካ የተካኑ ናቸው፡፡ የመራጩን ህዝብ የሥጋት ስሜቶች እና ቅሬታዎች በመጠቀም፤ በአብዛኛው ተጨባጭ ሐቆችን አጣምሞ በማቅረብ እና የደጋፊዎቻቸውን የተዛባ አመለካከት የሚመግብ ነጭ ውሸት በማዛመት የምዕራቡን ዓለም የሚያካትት ‹‹የፍርሃት ዕድር›› (axis of fear) በመፍጠር ላይ ናቸው፡፡ ለሚጠቅሱት ችግር መፍትሔ ባለማቅረባቸው ከመራጮች በካርድ የሚገለጽ ቅጣት ሳያገኛቸው፤ መቀስቀስ የሚችሉበት ዕድል ተፈጥሮላቸዋል፡፡

የጀርመኑ ፕሬዚዳንት ጂዋችም ጋውክ (Goachim Gauck) በስልጣን ዘመናቸው ማብቂያ ላይ ባደረጉት የመሰናበቻ ንግግር በምዕራብ ዴሞክራሲዎች ላይ ያንዣበበውን አደጋ ሲገልፁ፤ ‹‹አስቀድመን የያዝነውን

☞

የተዛባ አመለካከት ተጨባጭ ሐቅ አድርገን የምንወስድ ከሆነ፤ ከፊል እውነቶችን፣ ትርጓሜዎችን፣ የሴራ ንድፈ ሐሳቦችን እና አሉቧልታዎችን እንደ እውነት የምንቀበል ከሆነ፤ የፖለቲካ ጎዳናውን ለሐሳዊ መሢህዎች (Demagogues) እና ኦቶክራቶች የተመቸ የምናደርግላቸው መሆኑን መዘንጋት የለብንም›› ሲሉ አስጠንቅቀዋል፡፡ የኦክስፎርድ መዝገበ ቃላት አርታኢዎች፤ የ2016 ዓ.ም ምርጥ ቃል ‹‹ድህረ- እውነት›› (Post-truth) የሚለው ቃል መሆኑን ያወጁት ከዚህ የተነሳ ነው፡፡

አሁን የሚታየው ሁኔታ በዴሞክራሲ ላይ አደጋ ከመደቀን ባሻገር ግልጽ የሆነ የደህንነት ችግርን የሚጋብዝ ነው፡፡ ‹‹የድህረ እውነት›› ባህል ሌሎች የውጭ አካላት የተዛባ መረጃ የማቅረብ ዘመቻ ለማካሄድ ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡ ይህም የሊበራል ዴሞክራሲዎች መሠረት የሆነውን በሳል ክርክር የማድረግ ባህልን ይሸረሽረዋል፡፡

አሁን የሊበራል ዓለም አቀፋዊ ስርዓቱ ተሰነጣጥቋል፡፡ የህዝበኛ ፖለቲከኞች መነሳሳት፤ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጀምሮ የሊበራል መርህ የሚከተለው የምዕራቡ ዓለም ሲገነባው እና ሲጠብቀው በቆየው ሊበራላዊ የዓለም ስርዓት ላይ አደጋ ደቅኖበታል፡፡ ስርዓቱን አደጋ ላይ የሚጥል እና በፈጣን ሁኔታ እየተጠናከረ ያለ መዋቅራዊ ተግዳሮት ተጋርጦበታል፡፡ ህዝበኛ ፖለቲከኞች አንዱ ከአንዱ ልምድ እየቀሰመ እና ከድንበር ባሻገር ካሉ ብጤዎቻቸው ጋር ህብረታቸውን እያጠናከሩ ነው፡፡አንዳንድ ተንታኞች ይህን ሁኔታ "ፀረ-ሊበራል ዓለም አቀፋዊነት"፣ "ህዝበኛ ዓለም አቀፋዊነት›› ወይም ‹‹ዓለም አቀፍ ብሔርተኝነት" የሚል ስያሜ ሰጥተውታል፡፡

የሀገር ቤት ህዝበኞች እና በውጭ የሚገኙ ፀረ- ሊበራል አገዛዞች የሊበራል ዓለም አቀፋዊ ስርዓቱ መሠረቶች በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተቀናጀ ጠንካራ አደጋ ፈጥረዋል፡፡ የሊበራል ዴሞክራሲ መስፋፋት፣ በነጻ የንግድ ስርዓት ላይ የተመሠረተውን የኢኮኖሚ ትስስር እና ጠንካራ የሥራ ግንኙነት መፍጠር የቻሉ የዓለም አቀፍ ተቋማት አሰራርን የሚያደናቅፍ ችግር ሆኖ ታይቷል፡፡

"ፍሪደም ሀውስ›› የተሰኘው ተቋም ባለፉት አስር ዓመታት የነጻነት ሁኔታ እየተዳከመ መምጣቱን በ2015 ባወጣው ሪፖርት አስታውቋል፡፡ ☞

የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ ሥልጣን በተረከቡ ጊዜ ባደረጉት ንግግር ውስጥ ዴሞክራሲ፣ ነጻነት እና ሰብዓዊ መብት የሚሉ ቃላት አልተሰሙም፡፡ ይህ ከሳቸው በፊት ሆኖ የማያውቅ እንግዳ ክስተት ነው፡፡ይህም ለሊበራሉ የዓለም ስርዓት መልካም ዜና አይደለም፡፡

“ሂዩማን ራይትስ ዎች››ን የሚመራው ኬኔት ሮት (Kenneth Roth)፤ “በርካታ የምዕራቡ ዓለም ፖለቲከኞች በሰብዓዊ መብቶች እሴቶች ላይ ያላቸውን እምነት ያጡ ይመስላሉ፡፡ ስለሰብዓዊ መብት የሚናገሩት ከአንገት በላይ በሆነ ስሜት ነው” በማለት የተናገረው፤ ቢያንስ የተለወጠ ዓለማዊ ሁኔታ መኖሩን ያሳያል፡፡

ነጻ ዓለም አቀፋዊ የኢኮኖሚ ስርዓትም እየፈራረሰ ይመስላል፡፡ ዓለም አቀፉ የንግድ ድርጅት (WTO) የሚያካሂዳቸው ስምምነቶችም ለዓመታት እንደተወዘፉ ቀርተዋል፡፡ ለብዙ ዓመታት የነጻ ገበያ ሻምፒዮን ሆና የቆየችው አሜሪካ፤ አሁን የምትከተለው ጎዳና ይበልጡን ወደ ኢኮኖሚ ከለላ ያዘነበለ ሆኗል፡፡

የዶናልድ ትራምፕ የሰርክ መፈክር “አሜሪካ ትቅደም” ሆኗል፡፡ፕሬዚዳንት ትራምፕ ስልጣን ሲረከቡ ያደረጉት ንግግር ነገሮች ሌላ አቅጣጫ መከተል መጀመራቸውን አመላካች ነው፡፡ ‹‹አሜሪካ የምትከተለው ፖሊሲ በአሜሪካ ኢንዱስትሪዎች ኪሳራ የሌሎች አገሮችን ኢንዱስትሪ የሚያሳድግ ፖሊሲ ነበር፡፡ ...ከእኛ የመካከለኛ መደብ ህብረተሰብ ሐብት እየተነጠቀ ለመላው ዓለም ሲታደል ቆይቷል፡፡ የእኛ የጦር ኃይል እየተዳከመ ሌሎችን ስንደጉም ኖረናል፡፡ የእኛን ሀገር ከጥቃት መከላከል ትተን ሌሎችን ስንጠብቅ ከርመናል፡፡ የአሜሪካ የመሠረተ ልማት በአሳዛኝ ሁኔታ አርጅቶ እና ወድቆ ሳለ፤ በባህር ማዶ በትሪሊየን የሚቆጠር ዶላር ስንረጭ ሰንበተናል፡፡ የእኛ ሐብት፣ ጥንካሬ እና በራስ የመተማመን ስሜት እየተዳከመ ሲሄድ ሌሎች ሀገሮችን ባለፀጋ አድርገናል፡፡ ሆኖም ይህ የትናንት ታሪክ ሆኖ ይቀራል፡፡አሁን የምንመለከተው ወደፊት ብቻ ነው፡፡ ከዛሬ ጀምሮ መፈክራችን አሜሪካ ትቅደም ይሆናል፡፡ ...ለኢኮኖሚያችን የምናደርገውም ከለላ ወደ ታላቅ ብልጽግና እና ጥንካሬ ያመራናል›› ሲሉ ተናግረዋል፡፡

☞

ሆኖም ይህ የትራምፕ አቋም ተጎጂ የሚያደርገው እደግፈዋለሁ የሚሉትን የአሜሪካ ሠራተኛ ህዝብ መሆኑን በርካታ ኢኮኖሚስቶች ተናግረዋል፡፡ ነገር ግን ችግሩ በአሜሪካ ተወስኖ የሚቀር አይደለም፡፡ በሌላ በኩል፤ የዓለም አቀፍ ስርዓቱን ደግፈው ያቆሙ የባለ ብዙ ወገን ተቋማት አደጋ ላይ ናቸው፡፡ ዛሬ እንደ ዓለም አቀፉ የወንጀል ፍርድ ቤት (ICC) ያሉ ተቋማት ድጋፍ እያጡ ነው፡፡ እንዲሁም ለምዕራብ መራሹ የዓለም ሥርዓት ምሰሶ ሆኖ የቆየው፤ የሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን ድርጅት (Nato) አስፈላጊነት በራሳቸው በምዕራባውያኑ ጥያቄ ውስጥ ወድቋል፡፡ ዶናልድ ትራምፕ በአንድ አጋጣሚ ‹‹Nato በጣም ጠቃሚ ተቋም ነው›› ሲሉ መናገራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ቀደም ብለው Nato ያረጀና ያፈጀ ተቋም ነው ሲሉ አጣጥለውታል፡፡ የትራምፕ የውጭ እና የደህንነት ፖሊሲ ግራ አጋቢ ሆኗል፡፡

በሊበራሉ ዓለም አቀፋዊ ስርዓት ላይ ራሳቸው የስርዓቱ አዋላጆች ፊታቸውን እያዞሩበት ነው፡፡ በአጠቃላይ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም በኋላ የመጣው ዘመን፤ ዓለምን ፀረ-ሊበራል አቋም በስፋት ወደምታይበት አዲስ የታሪክ ምዕራፍ እየገፋት ነው፡፡ አሁን የምንገኝበት ዘመን ውጥረት የበዛበት፣ ኃያላን ሐገራት ወደ ግጭት እንዳይገቡ የሚል ስጋት ያንዣበበበት ዘመን ነው፡፡ ሊበራላዊው የዓለም ስርዓትም ጠበቃ አጥቶ የመፈራረስ አደጋ ተጋርጦበት ይገኛል፡፡

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ቀስ በቀስ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች እየተጠናከረ የመጣ እና ከአስር ዓመታት በፊት በተከሰተው የፋይናንስ ቀውስ ወደ ከፋ ደረጃ የተሸጋገረ የህዝበኝነት ንቅናቄ አለ፡፡ በዚሁ መጠን ግሎባላዊው የፖለቲካ ምህዳር እየተለወጠ ነው፡፡ ማዕከላዊው ፖለቲካ እየተሸረሸረ ነው፡፡ ከ1980ዎቹ መጀመሪያ አንስቶ ማዕከላይ-ግራ (Center-left) እና ማዕከላይ-ቀኝ (Center-right) በሚል የሚፈረጁት የተለመዱት የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያገኙት የመራጮች ድምጽ እያሽቆለቆለ መጥቷል፡፡ ሆኖም ከ2008ቱ የፋይናንስ ቀውስ ወዲህ ይህ የማሽቆልቆል ጉዞ ይበልጥ እየተጠናከረ ሄዷል፡፡ የህዝበኝነት ጉዳይ አሳሳቢ አጀንዳ ሆኖ የማይታባቸው ወይም የመቀዝቀዝ አዝማሚያን ይዟል ብሎ ለመናገር የሚቻል ሁኔታ ያላቸው ሐገሮች በጣት የሚቆጠሩ ናቸው፡፡

☞

ህዝቡ ፀንቶ ለሚገኘው ስርዓት ያለው ቅሬታ በ2016 ዓ.ም ያልተገመተ ፖለቲካው ውጤትን አስከተለ፡፡ ይህም በምዕራቡ ዓለም በእንግሊዝ ከአውሮፓ ህብረት ለመውጣት ባደረገችው ውሳኔ፤ በአሜሪካም በዶናልድ ትራምፕ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሆኖ መመረጥ፤ በጣሊያን ማቲዮ ሬንዚ ያቀረቡት የህገ መንግስት ማሻሻያ በመራጩ ህዝብ ተቀባይነት በማጣቱ ይበልጥ ግልጽ ሆኖ ወጣ፡፡ የእነዚህ ክስተቶች አንድምታ ሰፊ እና ጥልቅ ነው፡፡ ስለዚህ አንዳንድ ሰዎች የምዕራቡ ከአንድ ምዕራፍ ጫፍ ደርሷል፡፡ ምናልባት ወደ የግሎባላይዜሽን ትስስሩ መቀነት ወደሚፈታበት ወቅት ሊሸጋገር ይሆን የሚል ጥያቄ እንዲያነሱ አስገድዷቸዋል፡፡ ሆኖም በ2016 ዓ.ም ጎልቶ የታየው ያለመረጋጋት እና እርግጠኝነት የማጣት ስሜት መገንገን ምዕራባዊውን የዓለም ክፍል ብቻ የሚመለከት ክስተት አይደለም፡፡የዚሁ ክስተት አምሳያ የሆኑ ጉዳዮችን ብራዚል፣ ፊሊፒንስ እና ቱርክን ጨምሮ በመላው ዓለም ተመልክተናል፡፡

በርግጥ ይህ ሁኔታ ከፋይናንስ ቀውሱ መከሰት ወዲህ የተፈጠረ ችግር አይደለም፡፡ ለምሣሌ፤ ሩሰል ዳልተን የተባለ ፀሐፊ በ2004 ዓ.ም በኢንዱስትሪ በገፉት ዴሞክራሲዎች ህዝቡ ለፖለቲካ ስርዓቱ ያለው ድጋፍ እየተሸረሸረ ነው›› ሲል ጽፎ ነበር፡፡ ‹‹የምዕራቡ ዓለም ዴሞክራሲ እየተራቆተ መሄድ›› በተመለከተ በሚቀርቡ ክርክሮች፤ ከ1990ዎቹ ጀምሮ ያሉት አስርት ዓመታት የህዝብ የፖለቲካ ተሳትፎ እየተዳከመ የሄደባቸው ወሳኝ ዓመታት መሆናቸው ይገለጽ ነበር፡፡

በመሆኑም፤ አሁን የታየው ለውጥ ድንገተኛ ደራሽ ነገር ሆኖ ሊያስገርመን የሚገባ አይደለም፡፡ ‹‹ግሎባል ሪስክ ሪፖርት›› በየዓመቱ በሚያወጣቸው ሪፖርቶች ችግሮችን ሲያመለክተን ቆይቷል፡፡ በ2007 እና በ2008 ዓ.ም ባወጣው ሪፖርት የዳበረ ኢኮኖሚ ባላቸው ሀገራት ከግሎባል መቀነቱ የመውጣት ሁኔታ መታየቱን እና ይህም ከፍተኛ ችግር ሊያስከትል የሚችል መሆኑን ጠቁሞ ነበር፡፡ በ2011 ደግሞ ‹‹በኢኮኖሚያዊ ተለያይነት (Economic disparity) ችግር እና በግሎባል አስተዳደር መውደቅ›› ያተኮረ ሪፖርት አውጥቶ ነበር፡፡ በተመሳሳይ በ2014 ያወጣው ሪፖርት፤ ‹‹የማህበራዊ መዋቅር መፈራረስን ጨምሮ ሌሎች አሳሳቢ የማህበራዊ

☞

ችግሮች መኖራቸውን፤ ህዝብ በተቋማት ላይ ያለው እምነት መሸርሸሩን፣ የተሟላ የአመራር ሁኔታ ያለመኖሩን እና ያልተቀረፈ የፆታ እኩልነት ችግር›› መኖሩን አስታውቆ ነበር፡፡ እንዲሁም በ2015 ‹‹የማህበረሰቦች አቅም ይበልጥ እየተዳከመ መምጣቱ ይበልጥ አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱን›› በመጥቀስ፤ ያልተገባ የኢኮኖሚ ተስፈኝነት ስሜት ከማስተላለፍ መቆጠብ አስፈላጊ መሆኑን አስታውሶ፤ እንዲህ ያለ መልዕክት ‹‹ታሪክ እንደሚጠቁመው የሌለ የቁጥጥር አቅም የመኖር ስሜት ፈጥሮ ህዝቦችን ላልጠበቁት ችግር ሊያጋልጣቸው›› እንደሚችል አመልክቶ ነበር፡፡

አሁን ፀንቶ ባለው ስርዓት ቅሬታን መግለጽ በምርጫ አሸናፊ የሚያደርግ አስተያየት ሆኖ መታየቱ፤ ያለውን ግሎባላዊ ችግር እና አደጋ በወጉ መረዳት እና ተገቢ ምላሽ የመስጠትን ጉዳይ አጣዳፊነት አጉልቶ ያወጣዋል፡፡ የዓለም የኢኮኖሚ ፎረም ከፍተኛ ግሎባላዊ ትኩረት እና የተግባር እንቅስቃሴን የሚጠይቁ አምስት ቁልፍ ተግዳሮቶችን ለይቶ አስቀምጧል፡፡ እነሱም፤

1. ጠንካራ ትብብርን እና በገበያ ካፒታሊዝም ውስጥ የረጅም ዘመን ምልከታን ማጠናከር፤
2. የግሎባል ኢኮኖሚያዊ ዕድገቱ አዲስ ህይወት እና ጉልበት እንዲያገኝ ማድረግ፤
3. የማንነት ጉዳዮች ወሳኝ መሆናቸውን መረዳት እና አካታች የሆነ ጤናማ የፖለቲካ ማህበረሰብ መፍጠር፤
4. አራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ያመጣውን አደጋ መቀነስ እና መልካም ዕድሎቹን በአግባቡ መጠቀም፤ እና
5. የግሎባል የትብብር ስርዓታችንን ማጠናከር፤ ናቸው፡፡ የቀኝ አክራሪ ህዝበኛ ንቅናቄን መከላከል የሚቻለውም እንዲህ ያሉ እርምጃዎችን በመውሰድ ነው፡፡

## 3.2. ዓለም አቀፋዊ ተፅዕኖው

የቀኝ አክራሪ ህዝበኝነት ከጅማሬው ፅንፍ የነካ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ርዕዮተ ዓለም አስተሳሰብ ይዞ የተነሳ ሲሆን ህገ መንግስታዊ መሰረት ያላቸው እንደ ብዙሃነትና የአናሳ መብቶች የመሳሰሉ ☞

የሊበራል ዲሞክራሲ ፅንሰ ሃሳቦች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ዲሞክራሲያዊ የሆኑ ፓለቲካዊ ሂደቶች ስለማይቀበል ነው፡፡

እነዚህ አቀንቃኞች ሲጀመር ፀረ ዲሞክራሲያዊ ተቋማት ስላልሆኑ ተከታዮቻቸው በተለይ ታችኛው የማህበረሰብ ክፍል በነዚህ ዲሞክራሲያዊ ተቋማት ላይ እምነት እንዳይኖራቸው በኪሳራ ይሰራሉ፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ቀደምትና አንጋፋ የፓለቲካ ፓርቲዎች የነበራቸው ድጋፍ እየመነመነ ይመጣል፡፡ በሌላ አባባል የቀኝ አክራሪ ህዝበኝነት አስተሳሰብ እየተንሰራፋ ይመጣል ማለት ነው፡፡ የቀኝ አክራሪ ህዝበኝነት ማጠንጠኛ ደግሞ ፀረ ሉላዊነት አቋም ማራመድና  አለም አቀፋዊ የሆኑ የጋራ ህግጋትን አጥብቆ መንቀፍ ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ በዲሞክራሲ መንገድ የተመረጡ የቀኝ አክራሪ ህዝበኝነት አመራሮች የመረጣቸውን ህዝብ ፍላጐት ለማርካት በሚል የውጭ ፓሊሲያቸውን የመቅረፅ ሙሉ መብት ስለአላቸው አለም አቀፋዊ ተፅዕኖ ማስከተሉ አይቀርም፡፡

ብሄርተኝነት አንዱ የቀኝ አክራሪ ህዝበኝነት መገለጫ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ አገር ቅድሚያ ለተወላጅ የሚል አዲስ አስተሳሰብ እያንሰራራ መጥቶ ሌላውን ወይም ( መጤውን ) ማግለል ይጀምራል፡፡ በተለያዩ አገራት የሚገኙ የቀኝ አክራሪ ህዝበኝነት አቀንቃኞች በአገራቸው ጠንከር ያለ ፀረ ስደተኞች ህግ እንዲደነገግ ሌት ተቀን እየወተወቱ ይገኛሉ፡፡ ምንም እንኳን ስደተኝነት አላስፈላጊ ቢሆንም ቅሉ የሰው ልጅ የመንቀሳቀስ ተፈጥሯዊ ዝንባሌ አለው፡፡ ከዚህ ዝንባሌው ደግሞ ብዙ ነገሮችን አትርፏል፡፡ የቀኝ አክራሪ ህዝበኝነት ከዚሁ የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ዝንባሌ ጋር ፀብ ውስጥ የሚገባ እንቅስቃሴን የመገደብ አስተሳሰብን ያቀነቅናል፡፡ በመሆኑም ፀቡ ከሰብአዊነት ጋር ስለሚሆን መዘዙ የትየለሌ ነው፡፡

ይህ ፀረ ስደተኞች ህግ ወጣ ማለት ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለው ሰብኣዊ የመብት ጥሰት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በዚህ መሰረት አብዛኞቹ የህዝበኝነት አቀንቃኞች ስደተኛን መጥላትና ማግለል የሚል አሰተሳሰብ አራማጆች ስለሆኑ ለያሉበት አካባቢ ዜኖፎብያ (Xenophobia) የመፍጠር ዕድሉ በጣም ሰፊ ነው፡፡ አሳሳቢ የሚሆነው ደግሞ ዜኖፎቢያ በባህሪው ማህበራዊና ሰብኣዊ ቀውስ ማስከተሉ አይቀርም፡፡

☞

ሌላኛው የህዝበኝነት አቀንቃኞች እንደ አቋም ይዘው የሚያራምዱት የበላይነት አስተሳሰብ ሲሆን ይህ ማለት እነሱ ብቻ የተመረጡ ዘሮች ሌላው አናሳ እንደሆነ አምነው ደጋፊ ህዝባቸውን አስተሳሰቡን እንዲቀበል ያደርጉታል፡፡ ይህ ደግሞ በውጤቱ በተለያዩ ማህበረሰብ ክፍል ላይ የዘረኝነት አስተሳሰብን ይቀሰቅሳል፡፡ የቀኝ አክራሪ ህዝበኝነት አራማጆች ደግሞ የዘረኝነት አባዜ የተጠናወታቸው ስለሆኑ ውጤቱ የከፋ ሊሆን ይችላል፡፡ በሁለተኛው ዓለም ጦርነት በሂትለር መሪነት እኛ የአርያን ምርጥ ዘሮች ነን በሚል የተሳሳተ አመለካከት በጆውሽ ( አይሁድ ) ዘሮች ላይ የፈፀሙት ግፍ የዚህ የበላይነት ስሌት የፈጠረው ቀውስ ነበር፡፡ በዚህ ዘመንም ተገቢ ጥንቃቄ ካልተደረገ በስተቀር ተመሳሳይ ድርጊት የማይፈፀምበት አንዳችም ምክንያት የለም፡፡

በዚህ ዘመን ዓለም በቴክኖሎጂ ምክንያት የመንደር ያህል ቅርብ እየሆነች ባለችበት ሰዓት የቀኝ አክራሪ ህዝበኝነት አራማጆች ፀረ ግሎባላይዜሽንና በአገሮች መካከል የጠነከረ ዘርፈ ብዙ ግንኙነት እንዳይኖር በመፈለግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ይሄ ማለት ደግሞ ለዘመናት አገራት በጋራ ሆነው የገነቡትን የርስበርስ የመተባበር መንፈስ ቀስ በቀስ ወደ መሸርሸሩ እንዲያመራ መስራት ማለት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት አገሮች በተናጠል መንቀሳቀስ ከጀመሩ የዓለም ደህንነት አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል፡፡ በተለይ በሃገራት መካከል ይታይ የነበረውን የጋራ የንግድና የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግር ሊመነምን እንደሚችል ግልፅ ነው፡፡ለምሳሌ እንግሊዝ ከአውሮፓ ህብረት መውጣትን ተከትሎ /ምንምእንኳ እንግሊዝ ከሁሉም አገራት የነፃ ገበያና ግብይት ስርዓት ጠንካራ አራማጅ ብትሆንም/ አገሪቷ ከተለያዩ አገራት ጋር ልታደርጋቸው በይደር ላይ የነበሩ የንግድ ግንኙነትና ስምምነቶች ልትሰርዛቸው እንደምትችል ተንታኞች አስቀምጠዋል፡፡

የህዝበኝነት ማበብ ለዓለም የደህንነት ስጋት መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡ ይህም ሊሆን የሚችልበት ምክንያት የቀኝ አክራሪ ህዝበኝነት ስደትና ሰደተኞች ላይ ጠንካራ የተቃውሞ አቋም ሰለአላቸው ነው፡፡ ይህ አቋማቸው በርከት ያሉ ስደተኞች ባለባቸው አገሮች ብዙ ደጋፊና ተከታይ እንዲኖራቸው

☞

አስችሏቸዋል፡፡ ይህን ጠንካራ ፀረ ስደተኞች ህግ ተከትሎ አለም አቀፍ አሸባሪዎች አይሲስና ( ISIS ) መሰሎቹ እንደ ዕድል ነው ያዩት፡፡ ስለዚህ ዕድሉን ከመጠቀም ወደኋላ አይሉም ( አያቅማሙም ) ምክንያቱ ደግሞ ፀረ ሰደተኛ አቋም ራሱ ተወስዶ መጤውን የማግለል ስሜት ስለሚኖር መጤው ላይ የመገለል ስሜት ይፈጥራል ( በተለይ ሙስሊሞችን)፡፡ በዚህ ምክንያት በሁለቱም ቁርሾ እየዳበረ የመጣና ሰፊና የማይቀለበስ ማህበራዊ ክፍተት ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ ይህ ስደተኛ በመሆኑ ብቻ መገለል የደረሰበትን ግለሰብ የአሸባሪዎች ትልቅ መሳሪያ መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ምክንያቱም ማህበራዊና ስነ አእምሯዊ ቀውስ ስለሚያስከትል የአሸባሪዎች መሳሪያ ለመሆን አያቅማማም፡፡ እንደውም ISIS የተባለው አለም ዓቀፍ አሸባሪ እንግሊዝ ከአውሮፓ ህብረት መውጣቷን ተከትሎ ደስታውን በአደባባይ ገልጿል፡፡ ይህን ያደረገበት ምክንያትም በተለያዩ አገራት ስደተኛና መሰረታቸው ስደት የሆኑ በርከት ያሉ ወጣቶች ለሽብሩ ዓላማ መጠቀሚያ ስለሚያደርጋቸው ነው፡፡

### 3.3. ለታዳጊ አገሮች ተፅዕኖው ምንድን ነው ?

ታዳጊ አገራት ካለባቸው ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለመላቀቅ ደፋቀና በሚሉበት ሰዓት ከበለፀጉ አገራት ያላሰለሰ ድጋፍ ይፈልጋሉ፡፡፡ የበለፀጉ አገሮች ለታዳጊ አገሮች የሚያደርጉት ዘርፈ ብዙ ድጋፍ ከቴክኒክ እስከ ጂኦፓለቲካዊ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ በዓለም አቀፍ ንግድ ግንኙነት ታዳጊ አገሮች ወደ በለፀጉ አገሮች የሚልኳቸውን ጥሬ እቃዎች ከቀረጥና ኮታ ነፃ በሆነ መልኩ መላክ እንደሚችሉ በሁለቱም በኩል ስምምነት ላይ ደርሰዋል፡፡ በዚህ በተዘረጋው አለምአቀፍ የንግድ ስርዓት ተጠቃሚ የሚሆኑት ታዳጊ አገሮች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የቀኝ አክራሪ ህዝበኝነት አስተሳሰብ ይህንን የንግድ ስርዓት የሚቃወም ስለሆነ ታዳጊ አገሮች ተጐጂ ይሆናሉ፡፡

ሌላው እንደሚታወቀው ከዚህ በፊት በተለያየ ምክንያት ከተለያዩ ታዳጊ አገሮች ግለሰቦች በትምህርት ይሁን በስደት መልክ ወደ ተለያዩ የበለፀጉ አገራት ህጋዊ ጦርነትና አለመረጋጋትን ወይም ፓለቲካን ሽሽት ህጋዊ ባልሆነ መልኩ ይገቡ ነበር፡፡ ከገቡ በኋላም በተለያዩ የስራ መስክ

☞

ተሰማርተው ከቋጠሩት ትንሽዬ ሐብትና ንብረት ወደ ቤተሰብ ይልካሉ፡ ፡ይህ የሚላከው ብር ህጋዊ አላላክ ከተከተለ በመጠኑም ቢሆን ለታዳጊ አገርና ህብረተሰብ ይጠቅማል፡፡ እንዲሁም በትምህርት ምክንያት ወደ በለፀጉ አገሮች የተላኩ ተማሪዎች ትምህርታቸውን አጠናቀው በመመለስ ለአገራቸው የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራ ይሰራሉ፡፡ አስተሳሰቡ እንዲያድግ ከተፈቀደለት ይህንኑ ትንሽ እድልንም ማጨለሙ አይቀሬ ነው፡፡ ዕናም አስተሳሰቡ ጠንካራ ፀረ ስደተኛ አቋም ያለው ስለሆነ ለታዳጊ አገሮች በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ነው የሚሆንባቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሌላው ጉዳይ መዋዕለ ንዋይ ፍሰትን በተመለከተ ሲሆን ይህም ከተለያዩ የበለፀገ አገሮች ሀብታም ግለሰቦች ወደ ታዳጊ አገሮች እየመጡ በተለያዩ የንግድ እንቅስቃሴ ተሰማርተው ይገኛሉ፡፡ በዚህም የታዳጊ አገሮች ለተወሰኑ ዜጎች የስራ ዕድል ፈጥሮ የስራ አጥነትን ከመቀነስ አንፃር የውጭ ባለሃብቶች ትልቅ ሚና እየተጫወቱ እንዲሁም አምርተው ከሚልኩት እቃ የውጭ ምንዛሬ እያገኙ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማረጋገጥ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፡፡ይሁን እንጂ የቀኝ አክራሪ ህዝበኝነት አቀንቃኞች ዕድሉ ሁሉ ለአገሬው በሚል ስግብግብ እሳቤ ስሌት ምክንያት የአገሮቻቸው ባለሃብቶች በታዳጊ አገር ላይ መዋዕለ ንዋያቸውን እንዳያፈሱ በመወተወት ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ ደግሞ ታዳጊ አገራትን እጅግ አድርጎ የሚጎዳ ነው፡፡

ሌላኛው ጦስ ሊሆን የሚችለው ጉዳይ በታዳጊ አገራት ተመሳሳይ እሳቤዎች እንዲያቆጠቁጡ ምክንያት ሊሆን መቻሉ ነው፡፡ እንኳን ዘንቦብሽ ድሮም ጤዛነሽ እንዲሉ በመጠኑም ቢሆን በታዳጊ አገራት እየታየ ያለው ሰፊ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ጥረት ጨርሶ ሊያከስመው ይችላል፡፡ የቀኝ አክራሪ ህዝበኝነት ትልቁ አደጋም ይሄው ክስተት ነው፡፡ በተለይ በታዳጊ አገራት ያለው ማህበረሰብ ገና በዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የተገነባ ስላልሆነ ሚዛናዊ የሆነና አመክንዮ ላይ የተመሠረተ አስተሳሰብ ስር የሰደደ አይደለም፡፡ በመሆኑም ይህ ሁኔታ በአገራቱ ለዘረኝነት ማቆጥቆጥ በር ይከፍታል፡፡ የቀኝ አክራሪ ህዝበኝነት የግለሰብና የማህበረሰብ እኩልነት አይቀበልምና ለአለም አቀፍ ሰላም አስከባሪ ማህበረሰብ ፈታኝ የሆነ ዘረኝነት መሰረት ያደረገ የእርስ በርስ ጦርነት ሊከሰት ይችላል፡፡

☞

የምዕራባዊ ሀገራት መሪዎች፣ በውስጣቸው ጉዳይ ተውጠው ‹‹ሀገሬ ትቅደም›› በሚል መፈክር ከተመሩ፣ በንግድም ሆነ በእርዳታ ለታዳጊ ሀገራት አስተማማኝ አጋር ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ይህም በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ያለባቸው ችግር የሚባባስበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

የቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም አሜሪካ የዓለም ሰላም እና ደህንነትን እንዳሻት የመወሰን ሰፊ ዕድል እንድትይዝ አድርጓታል፡፡ ይህም ከወታደራዊ ጉዳዮች አንጻር ብቻ ሳይሆን ከፖለቲካ እና ከኢኮኖሚው ዘርፍ አኳያም ነው፡፡ ከወታደራዊ ጉዳዮች አንጻር እንደ ‹‹ሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን ድርጅት›› (NATO) ያሉትን ነባር የወታደራዊ ትብብር ተቋማት ለማስፋፋት እና መልሶ ለማደራጀት የሚያስችል ተቀናቃኝ የሌለው ዕድል አግኝታለች፡፡ አዳዲስ ተግዳሮቶችን ለመከላከልም አዳዲስ የትብብር እና የአጋርነት መድረኮችን አመቻችታለች፡፡ ሆኖም እንደ ዶናልድ ትራምፕ ያሉ ህዝበኛ መሪዎች የሚከተሉት ‹‹አሜሪካ ትቅደም›› በሚል መፈክር የሚገዛ አቅጣጫ የሐገሪቱ፣ በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካው እና በወታደራዊው ዘርፍ፣ ለዓለም ሰላም፣ ልማት እና ዴሞክራሲ የምታበረክተውን አስተዋጽዖ በማዳከም የህዝበኝነት እንቅስቃሴው ይበልጥ እንዲጠናከር ሊያደርገው ይችላል፡፡

አሁን በአውሮፓ እና በደቡብ አሜሪካ የሚታየው የህዝበኝነት ማዕበል እንዲጠናከር በማድረግ፣ የአሜሪካ የደህንነት መሠረቷ አድርጋ የምትመለከተውን የዴሞክራሲ ስርዓት መስፋፋት በመግታት እና በማዳከም ራሷንም የደህንነት ሥጋት ውስጥ ይጥላታል፡፡ ትራምፕ የሚያቀነቅኑት ህዝበኛ አመለካከት፣ ለሐገሪቱ ዕድገት እና ሥልጣኔ መሠረት የሆነውና በውክልና ዴሞክራሲ ላይ የቆመውን የአሜሪካ የፖለቲካ መዋቅር በማዳከም፣ ቁሳዊ አቅም እና ሞራላዊ ተቀባይነት ያተረፈላትን እሴት በማጥፋት፣ ከውስጥ የሚፈጠርባትን የደህንነት አደጋ ጭምር ለመከላከል የማትችል ሀገር ያደርጋታል፡፡ በዚሁ መጠን የዓለም ሰላም እና ደህንነትን የሚያናጋ ከፍተኛ አደጋ መደቀኑ የማይቀር ይሆናል፡፡ የህዝበኛ ፖለቲካ እንቅስቃሴ ደካማ የዴሞክራሲ ስርዓት መዋቅር ባላቸው ሀገራት ተጠናክሮ ከወጣ መንግስት አልባ ሀገራት ከመሆን ሊያደርሳቸው ይችላል፡፡

☞

በመሆኑም አሜሪካም ሆነች ሌሎች የዓለም ሀገራት፣ የህዝበኛ ንቅናቄዎችን ታሪክ እና የንቅናቄውን ወቅታዊ ባህርይ በውል በመመርመር፣ በተለይም ለኃላፊነት ቀጣናቸው ትኩረት በመስጠት ራሳቸውን ለስራው ብቁ ማድረግ እና ስትራተጂያዊ ዕቅድ ሊነድፉ ይገባል፡፡

ሀገራት ቀዳሚ ትኩረት ሊሰጡት የሚገባው፣ በየአካባቢ ሊነሱ የሚችሉ ቀኝ አክራሪ ህዝበኛ የፖለቲካ ኃይሎች የመንግስት ሥልጣን ለመያዝ ከመቻላቸው በፊት እርምጃቸውን መግታት የሚያስችል ፖሊሲ የመደንፍ እና ፈጥኖ ወደ ተግባር የመሄድ ጉዳይን ነው፡፡ ህዝበኞች የውክልና ዴሞክራሲ በፀናባቸው ሀገራት ከሥልጣን ኮርቻ ለመውጣት ከህገ መንግስታዊ ስርዓት ያፈነገጠ (Direct political action) የመጠቀም ዝንባሌ ይኖራቸዋል፡፡ ስልጣን ከያዙም በኋላ በተመሳሳይ መንገድ የመሄድ ዝንባሌ ይኖራቸዋል፡፡ ምንም እንኳን የህዝበኛ ፖለቲከኞችን አካሄድ በዲፕሎማሲያዊ ዘይቤ ማስቀየሩ ቀላል እና ውጤታማ መሆኑ አጠራጣሪ ቢሆንም በዚሁ መስመር ጥረት ማድረግ ይገባል፡፡

በዚህ ረገድ የዳበረ ዴሞክራሲ ያላቸው አገሮች፣ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ በጀመሩ ሀገራት የሚነሱ ህዝበኛ ፖለቲከኞች ወደ መስመር እንዲገቡ ተጽዕኖ በማድረግ እገዛ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ እንዲሁም ከህዝበኛ ኃይሎች ጋር በጊዜያዊ ጥቅም ተስበው ህብረት ከመፍጠር መቆጠብ ይኖርባቸዋል፡፡ አሁን በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚታየው የህዝበኛ ፖለቲከኞች ማንሰራራት ዓለምን ወዴት ሊያመራት ይችላል የሚለው ጥያቄ አስቸጋሪ ጥያቄ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በጉዳዩ ላይ ውይይት ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

አሁን የሚታየው የቀኝ አክራሪ ህዝበኛ ንቅናቄ ወዴት ሊያመራ ይችላል የሚለው ጉዳይ በውል ሊታይ የሚገባው ነጥብ ነው፡፡ አንዳንዶች ይህ ንቅናቄ ወደ ፋሽዝም ሊያመራ የሚችል መሆኑን ሲጠቅሱ፣ ሌሎች ወደ ፋሽዝም ሊያመራ አይችልም በሚል ይከራከራሉ፡፡ ሆኖም ችግሩን ከራሳችን አንጻር በማየት እና አደጋውን ለመካላከል የሚያስችል ቁመና ለመገንባት ጥረት ማድረግ ይኖርብናል፡፡

አሁን በበርካታ የዓለም ሀገራት የሚታየው ለህዝበኛ ፖለቲከኞች መነቃቃት መንገድ የጠረገው ሁኔታ፣ በ1920ዎቹ ለፋሽዝም መነሳት ምቹ

☞

መደላድል ከሆነው ሁኔታ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡ ከአንዳንድ ምሁራን ‹‹ራሳቸው የምዕራቡ ዓለም መንግሥታት በዓለም ሰላም ላይ ስጋት የደቀኑ ችግሮችን በአግባቡ ለመመከት እና ለመቋቋም አቅም የሌላቸው እና ፈቃደኛነቱም የሚጎድላቸው ሆነው ታይተዋል›› ይላሉ - የሶሪያን ጉዳይ በምሳሌነት እየጠቀሱ፡፡ በተመሳሳይ፤ ፋሽዝም በ1920ዎቹ ለመስፋፋት የቻለው፤ ሊበራሎች እና ዋና ዋናዎቹ የወግ አጥባቂ ፖለቲከኞች፤ እንቅስቃሴውን ከምር ወስደው ተገቢውን ጥረት ማድረግ ባለመቻላቸው ነበር፡፡ እንቅስቃሴውን ለመግታት ጥረት ከማድረግ ይልቅ በዝምታ በማስተናገድ ለፋሽዝም መስፋፋት እና መጠናከር እገዛ አድርገዋል፡፡

ዛሬም ተመሳሳይ ሁኔታ ይታያል፡፡ በምዕራቡ ዓለም የፖለቲካ ቀስተ ደመና የሚታዩ ፖለቲከኞች፤ በግራ መጋባት፣ የተከሰተውን ነገር ባለማመን እና በተቃውሞ ስሜት ተከብበው፤ የዛሬው ህብረተሰባዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ጂኦፖለቲካዊ ሁኔታ፣ በ1920ዎቹ ከነበረው ሁኔታ የተለየ በመሆኑ፤ የዘመናችን ቀኝ አክራሪ ህዝበኞች መነቃቃት የፋሽዝም ዳግም ማንሰራራት ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም እያሉ ነው፡፡ በርግጥ በ2017 ዩኒፎርም ለብሰው የጎዳና ጦርነት የከፈቱ የፓርቲ ሠራዊቶች እየተመለከትን ባለመሆኑ እና የቦልሸቪክ አብዮት ስጋት የሚያስጨንቀው ንጉሳዊ አገዛዝ ባለመኖሩ የተለየ ሁኔታ ያለ ቢሆንም፤ ዝምታ እና መፋዘዙ በ1920ዎቹ እና 1930 ከነበረው ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ አሁን በቀኝ አክራሪ ህዝበኛ ፖለቲከኞች የሚቀነቀኑት አጀንዳዎች፤ በፋሽስት ይቀነቀኑ ከነበሩ መሠረታዊ አጀንዳዎች ጋር አንድ እና ያው በመሆናቸው መመሳሰል አለ፡፡ ዛሬ የፋሽስት ዘይቤ ያለው ፖለቲካ በአውሮፓ፣ በአሜሪካ፣ በሩሲያ እና በሌሎች ክፍለ ዓለማት ይታያል፡፡

የህዝብ አለኝታነት ምስል፣ ሆን ተብሎ ቁጣ ቀስቃሽ ንግግር ማድረግ፣ ከምክንያታዊነት የራቀ ዴማጎጂያዊ መፈክር የፋሽስት ዘይቤ ፖለቲካ ገጽታዎች ናቸው፡፡ መጤ ጠል ብሔርተኝነት፣ ህዝብን አስቀድማለሁ እያሉ ህዝብን ከህዝብ ማቃቃር፣‹‹አሜሪካ ትቅደም›› ማለት እና ግሎባላዊ ካፒታሊዝምን መቃወም የባህርይ አንድነት ይሰጣቸዋል፡፡ይህ አዲስ የፋሽዝም መንገድ መያዙን የሚያመላክት ነው፡፡ ፋሽዝም ዳግም የመነሳት ዕድል አለው ከማለት አልፈን እኛም መቼ ሊሆን ይችላል ☞

የሚለውን ከአሁኑኑ መተንበይ አንችልም፡፡ የሆኖ ሆኖ ግን ግስጋሴውን የሚገታ ስራ መሰራት እንዳለበት ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

ጉዳዩን ከአገራችን ጋር አያይዘን ስንመለከት፤የእኛ ሐገር የቀኝ አክራሪ እንቅስቃሴዎች፤ በሌሎች ሐገሮች የታየውን ሁኔታ ምሣሌ በማድረግ፤ ከሁኔታው ሞራላዊ ኃይል በማግኘት፤እንቅስቃሴ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ እኛን አይመለከተንም በሚል የምንተወው ሳይሆን፤ ሁኔታው በአንክሮ በመከታተል፤ ለሀገራችን ልማት፣ ሰላም እና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ እንቅፋት እንዳይሆኑ እና ችግር እንዳይፈጥሩ በወትሮ ዝግጁነት መንፈስ መጠበቅ ይኖርብናል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ክፍል ከራሳችን አኳያ ያለውን ሁኔታ ወደ መመልከት እናመራለን፡፡

## 4. ውጥንቅጡ በወጣ ዓለም ውስጥ የሀገራችን ዕጣ ፈንታ

ድርጅታችን አገራችን ለረጅም ጊዜ ተጣብቶ ወደ መፍረስ ቋፍ የገፋትን የትምክህትና የጠባብ አክራሪ ብሔርተኝነትን ከፍተኛ መስዋእትነት ከፍሎ የታገለና የማታ ማታም ከስልጣን አስወገዶ በምትኩ የቡድንና የግል መብቶች የተከበሩባት ፌዴራላዊና ዴሞክራሲያዊ ሀገር መገንባት የቻለ ድርጅት ነው፡፡ ይህን ስናደርግ ከሞላ ጐደል ዓለማዊ ሁኔታው ለቀኝ አክራሪ አስተሳሰብ ያልተመቸ ነበር ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡ ሆኖም ከላይ እንዳየነው አሁን ያለው ዓለማዊ ሁኔታ ለህዝበኛ የቀኝ አክራሪ ኃይሎች የተመቸ ሆኗል፡፡ እዚህ ላይ ቆም ብሎ ለመሆኑ ይህ ዓለማአቀፋዊ ክስተት አገራዊ እንድምታው ምን ይሆን ? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይሆናል፡፡

የቀኝ አክራሪነት በአንድ አገር ላይ ብቻ ያለ ክስተት አይደለም፡፡ ይልቁንም እንደ ወረርሽኝ ከአንዱ አገር ወደ ሌላው አገር እየተዛመተ አብዛኛውን የበለፀጉት ምዕራብ አገራትን በመቆጣጠር ላይ ያለ አደገኛ ክስተት ነው፡፡ በእርግጥ ክስተቱና በዋነኛነት እንደዚህ አይነቱ ቀውስ ያደገ የካፒታሊስት አገር ችግር ስለሆነ በበለፀጉት ሃገራት በዋነኛ መስተዋሉ አይቀርም፡፡ ሆኖም አገራችን ቀላል የማይባል የቀኝ አክራሪ አስተሳሰብ ተሸካሚ የሆኑ የፓለቲካ ኃይሎች የሚገኙባት አገር ነች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ☞

ገና ፌዴራላዊ ስርዓታችን በሁለት እግሩ ያልቆመ በመሆኑ ከቀኝ አክራሪ ኃይሎች ጋር የምናደርገው የፓለቲካ ፍልሚያ ተጀመረ እንጂ ገና አልተገባደደም፡፡ በመሆኑም በዚህ ሁኔታ የቀኝ አክራሪ ኃይሎች አለም አቀፋዊነት የበላይነትን ካገኙ ከሁሉም በላይ የአገር ውስጥ የቀኝ አክራሪ ኃይሎች የሞራል መነሳሳት ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም የቀኝ አክራሪው ኃይል ዓለም አቀፋዊ የበላይነትን መቀዳጀት ስለሚፈልግ ለእንደኛዎቹ የቀኝ አክራሪ ኃይሎች የገንዘብ ፣የሞራል፣ የቴክኒክ እና መሰል ድጋፎችን ሊያደርግ ይችላል፡፡ ስለሆነም የአገራችን የቀኝ አክራሪ ኃይል ከመቸውም ጊዜ በላይ ምቹ በሆነ ዓለማቀፋዊ ሁኔታ ወደ ሚንቀሳቀስ ኃይልነት ተሸጋግሯል ማለት ነው፡፡ ዞሮ ዞሮ በዋነኛነት በአገር ውስጥ የሚደረገው ትግል ውጤት የሚወሰነው አገር ውስጥ ባለው ሁኔታ ነውና ጥርሳችንን ነክሰን በመረባረብ ፌዴራላዊ ስርዓታችን ከቀኝ አክራሪ ኃይሎች ጋር የሚያደርገውን ፍልሚያ በእኛ ድል አድራጊነት እንዲጠናቀቅ በማድረግ የዓለም አቀፋዊ ሁኔታ ተፅዕኖ እንዲቀንስ ማድረግ ይቻላል፡፡

ግሎባላይዝድ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ሆነን በትልልቆቹ ሀገራት ውስጥ ከሚከሰቱት እድገቶች ተፅዕኖ ነፃ መሆን አይቻልም። የውጭ ግንኙነትና ብሄራዊ ደህንነት ፖሊሲያችን በትክክል እንደሚያስቀምጠው ዋናው ሥራችን ድህነትና ኋላ ቀርነትን ማስወገድና ብዙህነትን በወጉ የሚያስተናግድ ሥርዓት መገንባት መሆኑና እዚህ ላይ መረባረባችን እጅግ ተገቢ ነው። ይሁንና ከዚህ ጎን ለጎን በአካባቢያችንም ሆነ በመላው ዓለም በየጊዜው የሚታዩ ለውጦችን እየተከታተሉ ተጋላጭነትን መቀነስ ላፍታም ቢሆን ልንዘነጋው የማይገባ የዕለት ተዕለት ሥራችን ነው። የውጭ ግንኙነትና ብሄራዊ ደህንነት ፖሊሲያችን ያስቀመጣቸው መሰረታዊ መርሆዎች እንደተጠበቁ ሆነው በየጊዜው የሚያጋጥሙ ዓለም አቀፋዊም ሆነ ከባቢያዊ ዕድገቶችን በንቃት እየተከታተሉ አስፈላጊ ማስተካከያዎችን ለማድረግ የሚያስችሉ ጥናቶችን ማድረግ ሊታለፍ የማይችል ሥራችን እንደሆነ መገንዘብ ያሻል። በዚህ መስክ በተደጋጋሚ የተፃፉ ፅሁፎቻችን በግልፅ እንደሚያስቀምጡት ማንኛውንም ጉዳይ ሆነ ክስተት ልናየውና ልናጠናው የሚገባን ለሃገራዊ ህዳሴያችን ካለው ፋይዳ አንፃር መሆኑን ልብ ልንለው ይገባል።

☞

ከላይ በዝርዝር ለማየት እንደሞከርነው አሁን እየተፈጠረ ባለው ዓለማዊ ሁኔታ ከዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፣ ከፀረ ድህነት ትግልም ሆነ ከሰላምና ከፀጥታ እንዲሁም ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ በርካታ ፈተናዎች ማጋጠማቸው የሚቀር አይመስልም። የጀመርነውን የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሥራችን የማሳካትም ሆነ የመላው ህዝባችን ፍትሀዊ ተጠቃሚ የሚያደርግ ልማት የማረጋገጥ ትግል ከማሳካት በላይ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚችል ጉዳይ ሊኖር አይችልም። በሚቀጥሉት ጥቂት ገፆች ይህንን ጉዳይ በተመለከተ የተወሰኑ ነጥቦችን ለማየት እንሞክራለን።

ከሁሉ በፊት በአገራችን የቀኝ አክራሪ /ትምክህት/ ህዝበኝነት አስተሳሰብ አራማጆች እነማን ናቸው? የሚለውን ጥያቄ አንስቶ መልስ መስጠት ተገቢ ነው፡፡ አገራችን በአፄ ምንልክ ንግስና ግዜ አሁን ያሉትን ቅርፅ እንድትይዝ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ሰፊ የሆነ የቀኝ አክራሪ ዝንባሌ የሚስተዋልባት አገር ነች፡፡ ከዛም በኃላ በተከታታይነት በትረ ስልጣኑን የጨበጡት ንጉሳውያንም ሆነ ደርግ የዚሁ አስተሳሰብ አቀንቃኞች ነበሩ፡፡ ሆኖም አገራችን ሰፊ የሆነ ብዙህነት የሚስተዋልባት አገር ነችና ብዙህነት መከበር አለበት የሚለውና የጠቅላይ ናዛዥ አስተሳሰብን ክፉኛ የሚቃወም ሌላው አካል ፀረ የዚሁ አስተሳሰብ መታገሉ አልቀረም፡፡ ከበርካታ አሰርት ዓመታት ደም አፋሳሽ ጦርነት በኃላ የማታ ማታ ይሄው የቀኝ አክራሪ ህዝበኝነት ከበትረ ስልጣኑ ተወግዶ በምትኩ የግለሰብና የቡድን መብትን የሚያከብር ፌዴራላዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ “ሀ” ብሎ ተጀምሯል፡፡ነገር ግን በተፈጠረው በነፃነት የመደራጀት መብትን በመጠቀም የአስተሳሰቡ ርዝራዦች የሞት የሽረት ትግል ማድረጋቸው አልቀረም፡፡ ግንቦት 7 ወዘተ… እየተባሉ መልክ፣ ስምና አደረጃጀት እየቀያየሩ ነገር ግን ያረጀውንና ያፈጀውን ተመሳሳይ አስተሳሰብን ተሸክመው በመታገል ላይ ይገኛሉ፡፡ ምንም እንኳን ትግሉ አሁንም በእኛ ድል አድራጊነት ባይጠናቀቅም ቅሉ አጠቃላዩ የአገራችን ፓለቲካል ኢኮኖሚ ግን በመሠረቱ ለእነሱ የማይመች እየሆነ በመምጣት ላይ ይገኛል፡፡

መነሳት ያለበት የመጀመሪያው ጉዳይ ሃገራችን ኢትዮጵያ በኢህአዴግ አመራር በማካሄድ ላይ የምትገኘው የነፃ ገበያ መር ካፒታሊስት ሥርዓት ግንባታን የሚመለከት ይሆናል፡፡ ከላይ ለማየት እንደተሞከረው ካፒታሊዝም በተፈጥሮው ( Inherently ) ራሱን በራሱ አደጋ ላይ የሚጥሉ ☞

ቀውሶችን የመፍጠር አዝማሚያ እንዳለው ለማየት ችለናል፡፡ ይሁንና በየወቅቱ የተጋረጡበትን ፈተናዎች በተለያዩ መንገዶች እየተጋፈጠ በተለይ ደግሞ የገበያ አክራሪ ወገኖችን መረን የለቀቀ የገበያ አምልኮ ለመቋቋም የሚያስችሉና መንግስት የገበያ ውድቀትን በመፍታትና ወደ ለየለት ቀውስ ላለመግባት የሚያስችሉ የተመረጡ ጣልቃ ገብነቶችን በማከናወን ካፒታሊዝም ከአጠቃላይ ውድቀት መታደግ የተቻለበት ሁኔታ እየፈጠረ እስካሁን ድረስ መጥቷል፡፡

ይሁንና በአሁኑ ዘመን ገበያ አክራሪው የኒዮ ሊበራሊዝም ሥርዓት በተደጋጋሚ እየተከተላቸው በመጣቸው የተሳሳቱ መንገዶች አማካኝነት ሊበራሊዝም በከፍተኛ አጣብቂኝ ውስጥ የገባበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡ ፡ድርጅታችን ኢህአዴግ ከጅምሩ ይህንን በሚገባ በመገንዘብ የሃገራችን የካፒታሊዝም ግንባታ ጥረት ይህንን አዝማሚያ ግምት ውስጥ ያስገባና የመንግስት ተገቢ ሚና በትክክል የተገነዘበ እንዲሆን ያደረገው ጥረት መልካም ፍሬን እያፈራ እንደመጣ ለሁላችንም ግልፅ ነው፡፡

ከኒዮ ሊበራሊዝም ይገጥመን የነበረው ተከታታይነት ያለው ዓለም አቀፍ ተፅዕኖ ተቋቁመን በተነፃፃሪነት ነፃ ሃገራዊ ኢኮኖሚ ለመገንባት ያደረግነው ጥረት ከሞላ ጎደል የተሳካ ሆኖ አሁን በተከታታይ ባለ ድርብ አኃዝ እድገት እያስመዘገብን የመጣንበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ይህ ሂደት በአንድ በኩል መሪ ድርጅታችንና ልማታዊ መንግስታችን ሲከተሉት የቆዩትን የካፒታሊስት ሥርዓት ግንባታ አቅጣጫ ትክክለኛነት በሚገባ ያረጋገጠ ሃቅ ሆኗል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አሁን ባለንበት ውጥንቅጡ የወጣ ዓለም ውስጥ የቱንም ያክል የማያዋጣ መሆኑ ይረጋገጥ ኒዮ ሊበራሊዝም አሁንም ቢሆን የማይሰራ አማራጩን እኛን በመሳሰሉ ታዳጊ ሃገራት ላይ ለመጫን ያለው ፍላጎት ለከት ተበጅቶለታል ተብሎ አይታሰብም፡፡

ስለዚህ እነዚህ ተፅዕኖዎችን ለመቋቋም የሚያስችለንን ቀጣይ ዝግጅት ማድረግና ተገማችነት ባጣ ዓላማዊ እውነት ውስጥ ሆነንም ቢሆን የህዝባችንን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥራዎችን አጠናክረን መቀጠል ይጠበቅብናል፡፡

☞

እስካሁን የመጣንበትን ጉዞ ትክክለኝነት በወጉ መገንዘብ የታዩብንን ድክመቶች አርመንና በተጎናፀፍናቸው ድሎች ላይ አክለን ለበለጠ ድል ለመብቃት ተጨማሪ ጉልበት ይሆነናል ተብሎ ይታመናል፡፡ በአሁኑ ሰአት ያለው ዓላማዊ ሁኔታ ምንም ይሁን ምን የገበያ አክራሪነትም ሆነ የመንግስትን ሚና እጅግ አንኳሶ የሚያይ የካፒታሊዝም ግንባታ አካሄድ ተቀባይነት እንደማይኖረው በሚገባ የተረጋገጠበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ጉዳዩ መንግስት የሌለበት ካፒታሊዝም መገንባት የመቻል ያለመቻል መሆኑ ቀርቶ መንግስት ምን ያክል ከዘራፊነትና ከኪራይ ሰብሳቢነት አዝማሚያ ድርጊት መራቅ ይችላል የሚለው መሆኑ ገሃድ ወጥቷል፡፡ ስለዚህ በዚህ ረገድ ልማታዊነትን ለማጎልበትና አደገኛና ፀረ-ልማት የሆነውን የመንግስትን ስልጣን ለራስ ብልጽግና የመጠቀም አዝማሚያዎችን ለመዋጋት የጀመርነውን ጥረት አጠናክረን መቀጠል ይጠበቅብናል፡፡

ከምንከተለው የካፒታሊስት ሥርዓት ግንባታ ጉዳይ ሳንወጣ ልናነሳው የሚገባው ሌላ ጉዳይም አለ፡፡ ይኸውም አሁን ባለው ዓለማዊ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ልማታችንን የሚያግዝ ዓለምአቀፍ ትብብርና ግንኙነት ከማሳለጥ አንፃር ምን ምን ፈተናዎች ይገጥመናል የሚለው አንዱ ጉዳይ ነው፡፡ በተለይም ደግሞ ከልማት እርዳታ፣ ከብድር አቅርቦትና ከኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲሁም ገበያ ከማግኘት አንፃር ምን ዓይነት ፈተናዎች ሊገጥመን ይችላል የሚለው ጥያቄ በሚገባ መታየት ይኖርበታል፡፡

በሌሎች ፅሑፎች ላይ በተደጋጋሚ እንደተገለፀው አሁን እየተፈጠረ ያለው ባለብዙ ዋልታ የሚመስል ዓለም የሚያመጣቸው የተለያዩ ፈተናዎች እንደተጠበቁ ሆነው ለልማታችን አጋዥ የሆኑ አጋጣሚዎችን በመፍጠር ረገድ ቀላል የማይባሉ መልካም ዕድሎችን እንደሚያመጣ ለማየት ተሞክሯል፡፡ አሁን እየተፈጠረ ባለው ዓለማዊ ሁኔታ ውስጥ ሃገራት ከዓለም አቀፍ ትብብር ማዕቀፎችና ከግሎባሊይዜሽን ምህዋር እየወጡ ወደለየለት አክራሪ ብሔርተኛ አሰላለፍ የሚመጡበት ሁኔታ ያመዝናል፡፡

ሁሉም የራሱን ጥቅም ማሳደድ ላይ በተጠመደበት ሁኔታ በጋራ ጥረትና በጋራ ተጠቃሚነት መርህ ላይ ተመስርተን ስናሳካቸው የነበሩት ጉዳዮች ተንጠባጥበው የሚቀሩበት ዕድል ይሰፋል። በእንደዚህ ዓይነቱ ☞

ከባቢያዊ ሁኔታ (Envioroment) በተለይም ከምዕራቡ ዓለም በኩል በዘልማድ ይጠበቁ የነበሩ የልማት እርዳታም ሆነ መሠል ትብብሮች ምንጫቸው እየደረቀ ቢመጣ የሚገርም አይሆንም። ይህንንም በቅርቡ በገጠመን የድርቅ አደጋና በተከታታይ እየተነገረንም ያለው የዚህ ዓይነቱ የእርዳታ አሰጣጥ ሂደት በእጅጉ እየቀነሰ እንደሚሄድ መገመት ይቻላል፡፡

ለወትሮውም ቢሆን ከልማት ዕርዳታ ጋር በተያያዘ ስማቸው ብዙም ከማይጠሩ ሃገራት መካከል ዩናይትድ ስቴትስ ግንባር ቀደሟ ነች ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ዩናይትድ ስቴትስ ከሰብዓዊ ዕርዳታ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከሌሎች በማደግ ላይ ካሉ ሃገራት ጋር ያላት የበጎ አድራጊነት ግንኙነት በተለይም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጠናቀቅ ወዲህ ብዙ ሲነገርለት ቆይቷል፡፡ በተለይም ከጆርጅ ደብሊዩ ቡሽ የሥልጣን ዘመን በኋላ ደግሞ ከኤድስና ከመሰል ተላላፊ በሽታዎች መከላከል ጋር በተያያዘ አሜሪካ የምትሰጠው እርዳታ በርካታ በጎ ውጤቶችን ማምጣት መቻሉ ይታመናል፡፡ በፕሬዝዳንት ኦባማ ዘመንም ቢሆን ከምግብ ዋስትና ጋር በተያያዘ ከሃገራችን ጋር የተጀመሩ በመጠናቸው እጅግ ትልቅ ያልሆኑ የልማት ትብብሮች አሉ፡፡ በአሁኑ ሰዓት በዩስኤ አይ ዲ እዚህም እዚያም የሚከናወኑ የተወሰኑ የልማት ፕሮጀክቶች አሉ፡፡

ፕሬዚዳንት ትራምፕ የያዙት “የአሜሪካ ትቅደም” ፖሊሲ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ቢደረግ በሃገራችንና በዩኤስኤ መካከል ባለው የትብብር ማዕቀፍ ላይ ምን ተፅዕኖ እንደሚኖረው መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፊ ማብራሪያ ለማቅረብ ሳይሆን ለልማታችን ካለው ፋይዳ አንፃር በእኛ በኩል መደረግ ስለሚገባው ዝግጅት አንዳንድ ጠቋሚ ጉዳዮችን ለማመላከት በማሰብ ነው ርዕሱን ማንሳት የተፈለገው፡፡ ከሰብዓዊ እርዳታም ሆነ ከፀረ-ኤድስ ዘመቻ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የትብብር ግንኙነቶች ይነስም ይብዛም ለአሜሪካም ቢሆን የሚያመጡት ቢያንስ ፖለቲካዊ ጠቀሜታ ከመኖሩ ጋር ተያይዞ እዚህ ግባ በሚባል ደረጃ የሚቀንስበት ምክንያት ይኖራል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ከዩስኤ አይ ዲ ጋር ያሉን የትብብር ማዕቀፎች በይዘታቸው የልማት ትብብር ብለን በምንጠራው ማዕቀፍ ውስጥ የሚጠቃለሉ ስለሆኑ በዚህ ረገድ ሊኖር የሚችለው ለውጥ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ተፅዕኖ መፍጠሩ አይቀርም፡፡ ይሁንና በዚህ መልክም ቢሆን እስካሁን ባደረግናቸው እንቅስቃሴዎች የልማት ፋይናንስን ☞

በሚገባ ከመጠቀም ጋር በተያያዘ ሃገራችን ያላት አፈፃፀም በሁሉም ወገን ዘንድ በአጥጋቢነቱ የሚታወቅ ስለሆነ እዚህ ግባ የሚባል ችግር ሳይገጥመው ሊቀጥል የሚችልበት ዕድል ዝግ ይሆናል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ የአፍሪካ ሃገራት ወደ አሜሪካ ገበያ የጨርቃ ጨርቅና ሌሎች በታዳጊ አገሮች የሚመረቱ ምርቶችን ከታሪፍ ነፃ ለማስገባት የሚያስችላቸው የአጎዋ ፖሊሲም እንዳለ ስለመቀጠሉ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ የሆነ ሆኖ የአሜሪካ ኩባንያዎች በስፋት የሚሳተፉበትን እድል በመፍጠር ግን ይህንን ችሮታ ለመጠቀም መትጋት ከኛ የሚጠበቅ ተግባር ይሆናል፡፡

ከልማት ዕርዳታ ጋር በተያያዘ እየተለወጠ ያለ የሃገራት እውነታ በሃገራችን ላይ ተፅዕኖ ሊያመጣ የሚችልበት እውነታን ስንገመግም በተለየ ትኩረት ልናየው የሚገባው ጉዳይ ቢኖር ከብሪግዚት እውን መሆን ጋር ተያይዞ በዩናይትድ ኪንግደም በኩል ሊከሰት የሚችለው የአቅጣጫ ለውጥ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ሁሉ ከልማት እርዳታ ጋር በተያያዘ በጥራትም ይሁን በብዛት በልማት ሥራዎች ላይ ትርጉም ያለው ተፅዕኖ ካመጡ ትብብሮች ከዩናይትድ ኪንግደም ጋር ያለንን ግንኙነት የሚያክል የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ከእንግሊዝ ጋር በዚህ ረገድ እስካሁን የነበረን ግንኙነት በሌበርም ይሁን በወግ አጥባቂ መንግስታት ወቅት አንዳችም እክል ሳይገጥመው እስካሁን ሊዘልቅ ችሏል፡፡ ይኸም የሆነበት ምክንያት በዋናነት የሃገሪቱ መንግስት የOECD አባላት ሃገራት ከአጠቃላይ ሃገራዊ ምርታቸው ቢያንስ 0.7 በመቶ ያህሉን ለድሃ ሃገራት ዕርዳታ ለማዋል የገቡት ቃል እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይሁንና የዩናይትድ ኪንግደም መንግስታት በዚህ ረገድ የሚያሳዩት የትብብር ዝግጁነት ቀጣይነት የሚወሰነው የዕርዳታ ተቀባይ ሃገራት የሚቀበሉትን የእርዳታ መጠን የድሆችን ህይወት በተሻለ ለመለወጥ በሚያስችሉ ፕሮጀክቶች ላይ ምን ያክል በተሳካ መልኩ አውለዋል በሚለው ግምገማ መሰረት ነው፡፡ በእንግሊዞቹ ቋንቋ “Value for money” ተብሎ በሚጠራው የግምገማ ስሌት ሃገራችን ኢትዮጵያ የዕርዳታ ገንዘብ ከመጠቀም ጋር ተያይዞ የዩናይትድ ኪንግደምን ትብብር ከሚቀበሉ ሃገራት ሁሉ ህንድን ብቻ ከርቀት አስከትላ በአንደኛ ደረጃ የምትጠራ ሃገር ነች፡፡

ልማታዊ መንግስታችን የልማትን ዕርዳታ ያለብዙ ብክነት ለታለመለት ግብ እያዋለ ከመምጣቱና የሚታይ ድሃ ተኮር ውጤት ከማስመዝገቡ አንፃር ☞

ከብሪግዚት በኋላ ባሉት ጥቂት ዓመታት ውስጥም ቢሆን አጠቃላይ የልማት አቅጣጫችንን ትኩረት በሚያዛባ ደረጃ እንቅፋት ላይገጥመው ይችላል፡ ፡ይሁንና ለብሪግዚት መከሰት ምክንያት የሆኑት "ተጎድተናል" የሚሉ የዜጎች ስሌቶች በእንደዚህ ዓይነቶቹ የእንግሊዝ መንግስት ወጪዎችን ላይ የራሳቸውን ጥላ ማጥላታቸው የሚቀር አይሆንም፡፡ ኒዮሊበራሊዝም ባስከተለው መዋቅራዊ ቀውስ ህይወታቸው ባንድ ወይም በሌላ መልኩ የተመሰቃቀለባቸው በሚሊዮን የሚቆጠሩ የተቆጡ ዜጎች ባሉበት ሃገር ውስጥ የእያንዳንዱን ቤሳቤስቲን መድረሻ በተለየ ትኩረት መጠየቁ በፍፁም አይቀርም፡፡ ምንም እንኳ ልማታዊ መንግስታችን እስካሁን ያሳየው ትጋት በሁሉም ወገኖች ዘንድ ሞገስን ያስገኘለት ቢሆንም ከዩናይትድ ኪንግደም የሚገኘው የልማት ዕርዳታ እስካሁን በነበረው ጥራትና መጠን ለወደፊት ስለመቀጠሉ ግን እርግጠኛ መሆን አይቻልምም፣ አያስፈልግምም፡፡ እዚህ ላይ ቀድሞ በእርዳታ መልክ የሚሰጠውን ሃብት አሁን አሁን አክራሪው ሃይል እንዲለዝብ ከስደተኞች እንቅስቃሴ ( Migration ) ጋር በማያያዝ ይህንኑ በየአገሩ ለማስቀረት ሥራ ፈጠራ ላይ ያተኮረ እንደ "Jobs Compact" የመሳሰሉትን በመቅረጽ ለመጠቀም ፈጠራ የታከለበት ጉዞ መቀጠል ያለብን ይሆናል፡፡

እየተለወጠ ካለው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ አንፃር የሁለቱን ሃገራት ጉዳይ እንደ አብነት ማንሳት አስፈለገ እንጂ በምዕራቡ ዓለም በስፋት እየታየ ያለው ዘርፈ ብዙ ለውጥና እየፈጠረው ያለው ውጥንቅጡ የወጣ ሁኔታ ከሀገራችን ጋር በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ትብብርና ግንኙነት ካላቸው ከሌሎች ሃገራት ጋር ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ገፅታ እየያዘ መምጣቱ የሚቀር አይመስልም፡፡ በተለይም ደግሞ የአውሮፓ ህብረት ፣ ጀርመን እና ሌሎች የስካንዲኒቪያን አገሮች ለአየር ንብረት ለውጥ በሰጡት ትኩረት ምክንያት ከታዳሽ ሃይል ኤሌክትሪክ የማመንጨት ሥራ ላይ ከፍተኛ ድጋፍ ልናገኝ ስለምንችል የነርሱንም ኢንቬስተሮች በማሳተፍ አጋጣሚውን በላቀ ሁኔታ መጠቀም ይገባናል፡፡ የአሜሪካ ከፓሪሱ ስምምነት መውጣት በነዚህ አገሮች ላይ የፈጠረውን እልህ ለራሳችን እና ለመላው ዓለም የሚያስገኘውን ጥቅም አሚጠን ተግባር ላይ ለማዋል መጣር አለብን፡፡

☞

እዚህ ላይ ነገ ምን ይመጣል? ለሚለው ጥያቄ በእርግጠኝነት የምንሰጠው መልስ ኖረም አልኖረም ልማታችን ፍጥነቱንና ግለቱን ጠብቆ እንዲቀጥል ከማድረግ አንፃር ከእኛ ምን ይጠበቃል ብሎ መጠየቅ ግን ተገቢ ይሆናል፡፡ የመጀመሪያውና ዋነኛው ተግባር የጀመርነውን ልማት እስካሁን ከታየውም በተሻለ ፍጥነት በማስቀጠል ተጨማሪ ሚሊዮኖችን ከድህነት አረንቋ የማውጣትና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ ሃገራዊ ኢኮኖሚ የመገንባት ሥራችንን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ማሸጋገር መሆን ይኖርበታል፡፡ ሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በግብርና ልማትም ሆነ በሌሎች አምራች ዘርፎች ላይ በተለይም ደግሞ በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ በቆዳና ቆዳ ውጤቶችና በአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች በማተኮርና ያልተዘጋውን የዓለም ገበያ በተነፃፀረ ተወዳዳሪ ዋጋ በማቅረብ ንጽጽራዊና ተወዳዳሪ ጠቀሜታ ባላቸው ዘርፎች ላይ ዕድገት ለማስመዝገብ የያዛቸውን ዕቅዶች በጊዜ የለንም መንፈስ ለማሳካት መረባረብ ይኖርብናል፡፡

የቁጠባና የወጪ ገቢ ግኝት (Export) ግቦቻችንን ከመቼውም በበለጠ ትጋት በማከናወን የውጭ እርዳታ ከሃገራችን የልማት ወጪ ጋር በንፅፅር ያለውን ድርሻ ደረጃ በደረጃ በመቀነስ በዋናነት በራስ አቅም ላይ የተመሰረተ ዕድገት ማረጋገጥ እንደምንችል በተግባር ማሳየትም ይጠበቅብናል፡፡ ከዚህ አኳያ ከአውሮፓ ሕብረት ጋር የተፈራረምነውን የስትራቴጂክ አጋርነት በማጎልበት ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ከእርዳታ ባሻገር ሄደን በንግድና ኢንቨስትመንት እንዲሁም በቱሪዝም ዘርፍ ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር መረባረብ የሚገባን ይሆናል፡፡ የኢንቨስትመንት ከባቢያዊ ሁኔታችን የአውሮፓ ኩባንያዎችንም በስፋት የሚስብ በማድረግ የለውጥና የማሻሻያ ስራዎችን በጥራት ማከናወን አለብን፡፡ በተለይም ከውጪ ንግድ እንቅስቃሴያችን አንፃር የታየውን እጅግ ከፍተኛ መቀዛቀዝ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በመፍታት አስተማማኝ የሆነ የክፍያና የንግድ ሚዛን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥራ መሥራት ይጠበቅብናል፡፡ የልማት እርዳታ በሃገራችን የልማት እንቅስቃሴ ላይ ያለው ከፍተኛ ፋይዳ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መስክ ያለንን ጥገኝነት ከጊዜ ወደ ጊዜ በመቀነስ የደጋፊ ሚና ከመጫወት አልፎ የሞት የሽረት ጉዳይ የማይሆንበትን ዕድል ለመፍጠር

☞

መረባረብ አለብን፡፡ ተጨማሪ ብድር የማግኘት (Debt sustainability) ዕድላችን የሚወሰነው ተጨማሪ የኤክስፖርት ገቢ በማግኘት አቅማችን ላይ እንደሆነ ልብ ልንለው ይገባል፡፡ ስለሆነም አሁንም የመሠረተ-ልማት ክፍተታችንን በራስ አቅም ለመፍታት በምናደርገው ጥረትም ሆነ ተጨማሪ ብድር ለማግኘት የኤክስፖርት ግኝታችንን የማሳደግ ጉዳይ የሞት የሽረት ጉዳይ አድርገን መረባረብ ይገባናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ቻይናን ጨምሮ የሰሜን ምስራቅ እሲያ አገሮች ከሆኑ የዓለማችን ከፍተኛ የልማት ኢንቨስትመንትና ብድር አመንጪ ሃገራት ጋር ያለንን በመርህ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ማጠናከር ይኖርብናል፡፡ እንደሚታወቀው ቻይና የዩናይትድ ስቴትስን ከዓለም መድረክ ማፈግፈግ ምክንያት አድርጎ በመፈጠር ያለውን ክፍተት ለመሙላት ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ዝግጁ መሆኗን በተግባር በማሳየት ላይ ትገኛለች፡፡ ግራሃም አሊስን እንደሚለው ቻይና ሃገራችንን ጨምሮ  ከ130 የዓለም ሃገራት ጋር በየጊዜው እያደገ ያለ የንግድ ሚዛን ማስመዝገብ የቻለ ግንኙነት አላት፡፡ አገሪቱ ያላትን ዓለማቀፋዊ ተጽእኖ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያሳድግላት የታመነበትንና በብዙዎች የክፍለ ዘመናችን ትልቁ የልማት ትብብር ተብሎ የሚሞካሸውን ዋን ቤልት ዋን ሮድ ወይም ቤልት ኤንድ ሮድ የትብብር ማዕቀፍ ባሳለፍነው ግንቦት ወር ይፋ አድርጋለች፡፡  ይህ የልማት ትብብር ማዕቀፍ  አገራችንን ጨምሮ ከ60 በላይ የሚደርሱ አገራትን እንደሚያቅፍ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እነዚህ አገራት በአጠቃላይ ወደ 4.4 ቢሊዮን ወይም 63% የአለምን የህዝብ ቁጥር እንደሚሸፍኑ ይገመታል፡፡ በዚህ ኮሪደር የሚገኙ አገራት በአጠቃላይ ኢኮኖሚያቸው ወደ 21 ትሪሊዮን የአሜሪካን ዶላር መድረሱን የቻይና መንግስት ይፋ ያደረጋቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ቻይና ከነዚህ አገሮች ጋር ያላት የንግድ መጠን እ.ኤ.አ በ2014 ዓ.ም 1.12 ትሪሊዬን የአሜሪካን ዶላር መድረሱ ተገልጿል፡፡

የአለም ባንክና የአለም የንግድ ድርጅት በሌሎች ሃገራት ላይ ያላቸውን የአድራጊ ፈጣሪነት ሚና እንዲሁም ዩናይትድ ስቴትስ በነዚህ ተቋማት ላይ የመጨረሻውን ድምጽን በድምጽ የመሻር ስልጣን እንዳላት ይታወቃል፡፡ግራሃም አሊሰን እንደሚለው ቻይና "ችሮታም፣ ለጋስነትም

☞

፣ማባበልም፣ ማስፈራራትም” አክላበት በምታደርገው እንቅስቃሴ የነዚህን ተቋማት ተፅእኖ ለመቋቋም የሚያስችሉ ሙከራዎች በማድረግ ላይ ትገኛለች፡፡ ለዚህም በ30 ቢሊዮን መነሻ ካፒታል የተቋቋመውና ሃገራችንም አባል የሆነችበት የእስያ መሰረተ ልማት ኢንቨስትመንት ባንክ አንዱ ማሳያ ነው፡፡ በአምስቱ አገራት የሚመራው የብሪክስ ባንክም ሌላኛው ነው፡፡አሁንም ግራሃም አሊሰን እንደሚለው ቻይናን ለአለም አቀፍ ልማት ፋይናንስ አቅርቦት ያዘጋጀቻቸው ባንኮች ከስድስቱ ትልልቅ የምዕራብ አለም ተመሳሳይ ተቋማት ጋር ሲነፃፀር የመቶ ሰላሳ ቢሊዮን ዶላር ብልጫ አላቸው፡፡ የዩናይትድ ስቴትስም ሆነ የሌሎች ምዕራባውያን ሃገራት ማፈግፈግ ቀጣይ ሆነም አልሆነም የቻይና እያደገ ያለ ተሳትፎ ክፍተቱን በማካካስ ረገዱ የራሱ የሆኑ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ምንም እንኳ ከቴክኖሎጂ ፈጠራ ጋር በተያያዘ ምዕራባውያን ረዘም ላሉ ዓመታት ዋነኞቹ አመንጪዎች ሆነው መቀጠላቸው የሚያጠራጥር ባይሆንም ቻይና የመረጋጋት ምንጭ ሆና የምትቀጥልበት ዕድል ግን አሁንም ቢሆን ሰፊ ሆኖ እንደሚቀጥል ይታመናል፡፡ በልማታዊ መንግስታችን በኩል የልማት ፋይናንስን በብቃትና በውጤታማነት በመጠቀም በኩል ያስመዘገብናቸውን በጎ ልምዶች በማዳበር ያሉብንን ድክመቶች ደግሞ በቀጣይነት በማሻሻል ያለውን ዕድል በሙሉ አሟጠን ለመጠቀም ርብርባችንን ማሳደግ ግድ ይለናል፡፡ በምዕራባውያን አገራት ያለው ሁኔታም አንድና ወጥ ባለመሆኑ እንደየሀገሩ ሁኔታ የተዘረዘረ እቅድ ኖሮን ተለዋዋጭ ሁኔታውን ለራሳችን ጥቅም ለማዋል መረባረብ ይገባናል፡፡

አሁን እየተፈጠረ ባለው ውጥንቅጡ የወጣ ዓለም ከሃገራችን አንፃር ሊኖር የሚችለው ሌላው ተፅዕኖ ከዴሞክራሲ ግንባታ ሥራችን ጋር የተያያዘ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ሁሉ ሃገራችን ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ሃገር እንደመሆኗ መጠን ብዙሀነቷን በወጉ የሚያስተናግድ ሥርዓት ባላረጋገጠችበት ሁኔታ ከትርምስና ከቀጣይ ሁከት የምትድንበት ዕድል እንደማይኖር ሳይታለም የተፈታ ሃቅ ነው፡፡ በቅርብም ሆነ በሩቅ ያለው ውጫዊ ሁኔታ ከዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባችን አንፃር ያለውን ተፅዕኖ በትክክል መገንዘብ መቻላችን የጀመርነውን ጉዞ በተሳካ መልኩ ለማጠናቀቅ እንድንችል እጅግ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

በዚህ ረገድ መነሳት ያለበት የመጀመሪያው ነጥብ የጀመርነው የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እስከ ምን ድረስ የዴሞክራሲ ተቋማትን

☞

ማጠናከር ችሏል የሚል ነው፡፡ እንደሚታወቀው ሁሉ ወዳጆቻችንም ሆኑ ሌሎች የምዕራብ ሃገራት የዴሞክራሲ ግንባታን ለእነሱ ብለን የምንሰራው የታይታ ሥራ (Window dressing) እንደሆነ ያምናሉ፡፡ የአፍሪካ መንግስታት በአጠቃላይም ሆነ የኢትዮጵያ መንግስት ዴሞክራቲክ ባህሪይ እንደሌላቸውና ህዝባቸውን በማስተዳደር ረገድ ምዕራባዊ ሃይባይ እንደሚያስፈልጋቸው አስረግጠው ሲናገሩም ለረጅም ጊዜ ሰምተናል፡፡ በሰብዓዊ መብትና በዴሞክራሲ ግንባታ እንዲሁም በሲቪል ማህበራት ሽፋን የሃገራችንን የዴሞክራሲ ግንባታ ከሩቅ ለመዘወር ያልተፈነቀለ ድንጋይ አልነበረም፡ ፡ከዚህ አንፃር በምዕራቡ ዓለም ዘንድ እየታየ ያለው ከግሎባላይዜሽን ማዕቀፍም ሆነ ከዓለምዓቀፍ የትብብር ማዕቀፍ የመሸሽ አዝማሚያ ቢያንስ ቢያንስ በመንግስታት ደረጃ በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ጥረታችን ላይ ይደረግ የነበረውን ጣልቃ ገብነት በተወሰነም መልኩም ቢሆን ሊያለዝበው ይችላል ተብሎ ይገመታል፡፡

ኘሬዝዳንት ዶናልድ ትራምኘ “አሜሪካን ለማስቀደም” ካላቸው ፍላጎት የተነሳ በሌሎች አገሮች ላይ ጣልቃ እንደማይገቡ፤ “የአሜሪካ ትቅደምን” አጀንዳ እስካገዘ ድረስ ከማንም ሃገር ጋር በትብብር ለመስራት ዝግጁ መሆናቸውን በተደጋጋሚ መግለፃቸው ይታወቃል፡፡ ምናልባትም እንደዚህ መሆኑ የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታችንን ለህዝባችን ቃል በገባነውና የህልውናችንን ቀጣይነት በሚያረጋግጥልን አኳኋን ለማከናወን በተወሰነም መልኩ ቢሆን ካላስፈላጊ ጣልቃ ገብነት ይገላግለናል ተብሎ ሊገመት ይችላል፡፡

ይሁን እና የኘሬዚዳንቱ ቃል ተከበረም አልተከበረም እኛን በመሰሉ ሃገራት የዲሞክራሲ ግንባታ የቤት ስራ ላይ ለራሳቸው “የማይተካ” ሚናን የሚሰጡ መንግስታዊም ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ የምዕራብ አለም ተቋማት እንጀራችን ብለው የያዙትን የሰብአዊ መብት ይከበር የይስሙላ ጬኸት በቀላሉ ያቆማሉ ተብሎ አይታሰብም፡፡ ተወደደም ተጠላም በዚህ ረገድ ይደርስብን የነበረውና ወደፊትም ሊቀጥል እንደሚችል ታሳቢ ልናደርገው የሚገባን ተፅእኖ መነሻው የምዕራባውያኑ የዲሞክራሲያዊና የሰብአዊ መብት ጥብቅና ሳይሆን የሃገራችንና የመሪ ድርጅታችን በተነፃፃሪ ከምዕራባውያን

☞

ነፃ የሆነ አካሄድ በመሆኑ ይሄ እስካልተቀየረ ድረስ ተፅእኖው ይቀራል ተብሎ አይወሰድም፡፡ ተፅእኖውን ተቋቁመን የህዝባችንን የዴሞክራሲ፣ የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄ ከመመለስ የምንቦዝንበት ምክንያት ደግሞ በፍፁም ሊኖር አይችልም አይገባም፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ሌላ ሊነሳ የሚገባ መሰረታዊ ቁም ነገርም አለ፡፡ ይኸውም የዴምክራሲ ተቋሞቻችንን በሚፈለገው ደረጃና ፍጥነት ማጠናከር አቅቶን የህዝባችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት፣ የዴሞክራሲና የራስን በራስ በተሟላ መልኩ የማስተዳደር ጥያቄ እንዲቀለበስ የፈቀድን እንደሆነ የሚገጥመን ሃገራዊ የህልውና ፈተና ነው፡፡ ከላይ በፅሑፉ ላይ ለማሳየት እንደተሞከረው የዲሞክራሲ ተቋማት ጥንካሬ አስተማማኝ ባልሆነበት፤ የሕዝቦች ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ዝግጁነት ባነሰበትና፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ቀውሶች የየዕለት ገጠመኞች በሚሆኑበት ሁኔታ ለወትሮው የህዝብን ጥያቄ የመመለስ ሥራ ሲሰሩ የኖሩ ፖለቲከኞች ሳይቀር ጭልጥ ወዳለ የህዝበኝነት ምሕዋር ውስጥ ገብተው ሃገርን ለቀጣይ ትርምስ የሚዳርጉበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

አሁን በሃገራችን ያለው እውነታም ከዚህ ሃቅ ብዙም የራቀ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባውም፡፡ የጅምር ዴሞክራሲያችንን ድክመቶችን በማጉላትና፣ መረጋገጥ የጀመረው ፍትሐዊ ልማት በሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ በተገቢ ፍጥነት አለመዳረሱን በማጉላት የፌዴራል ሥርዓታችን ልዩ መገለጫ የሆነውን የፍትሐዊ ተጠቃሚነት ጉዳይ በማንኳሰስ የህዝባችንን ስሜት ለመቀስቀስ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን እዚህም እዚያም በመታየት ላይ እንደሆኑ ለማወቅ ነብይነትን አይጠይቅም፡፡ የዓለም አቀፉ አዝማሚያ የሚያሳየውም ይህንኑ ነው፡፡ በመርህና በትግል ላይ ተመስርቶ ልማትንና በእሱ በኩል ብቻ ሊረጋገጥ የሚችለውን የህዝቦች ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ከማምጣት ይልቅ የህዝበኝነትን ፈረስ እየጋለቡ አንዱ ሌላውን በጥርጣሬ የሚያይበትና ሃገር እንደ ሃገር ባልተረጋጋ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ምሕዋር ውስጥ የምትዋዥቅበትን ሁኔታ እንዳንፈጥር ከመቼውም ጊዜ በላይ መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡ በአሁኑ ሰዓት በየቦታው ብቅ ብቅ እያሉ የምናያቸው ወደየራስ አምባ ተመልሶ የመመሸግ አደገኛ አዝማሚያ ከአለምአቀፋዊ የሕዝበኝነት መስፋፋት አዝማሚያ ጋር ተዳብሎ ወደለየለት ሁከት እንዳያደርሰን ከመቼውም የበለጠ ትኩረት ሰጥተን ልንታገለው ይገባል፡፡ ድርጅታችን ኢህአዴግ የውስጠ ድርጅት ዲሞክራሲውን የበለጠ አዳብሮ፤ በውስጡ ☞

የሚታዩ የሌብነት ወኪል የሆኑ የጠባብነት፣ የትምክህትና የከባቢያዊነት አዝማሚያዎችን ታግሎ በሰፈር ልጅነትና በመወለድ ቅርበት ወይም በደምና አጥንት ትስስር ሳይሆን በመደብ ተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተ መርህ ተኮር እንቅስቃሴውን ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ማጧጧፍ ይኖርበታል፡፡

የየአካባቢውን ሕዝብ ስሜት የሚቀሰቅሱ መፈክሮችን እያሰሙ ወደለየለት የሕዝበኝነት ስካር መግባት ለተወሰነ ወቅት የይምሰል ሕብረት ከመፍጠር አልፎ የዲሞክራሲ ተቋማትን በማጠናከር፣ ልማታችንን በማፋጠንና በማጎልበት እንዲሁም በህዝቦች ዙሪያ መለስ ጥያቄዎች በመርህ ላይ የተመሰረተ ምላሽ በመስጠት ብቻ ሊፈቱ የሚችሉ ችግሮችን ለአፍታም ቢሆን ሊፈታልን አይችልም፡፡ መታገልና መርህን ጨብጦ ችግሮችን ለመፍታት መንቀሳቀስ አድካሚ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡አማራጩ ግን በተራ የህዝበኝነት መፈክር ነገ ተነገወዲያ ወደ ትርምስ እና መከፋፈል የሚያስገባንን የጥፋት መንገድ መከተል እንዳልሆነ ልብ ማለት ይኖርብናል፡ ፡አሁን በምዕራቡ ዓለም እየታየ ያለው ህዝበኝነት መነሻውን እንዳየነው መሠረታዊ መዋቅራዊ ለውጥ በማምጣትና ፖለቲካ ኢኮኖሚውን በመቀየር መፈታት ያለባቸውን ችግሮች ሌሎች እንደፈጠሩት በማስመሰል አቅጣጫ ማሳት ጊዜያዊ ስሜት በመኮርኮር ወደ ስልጣን ርካብ መውጫ እንጂ መቼውንም ቢሆን የዘላቂ ውጤት ምንጭ እንደማይሆን ሁሉ በህዝባችን ሁሉን አቀፍ የተደራጀ እንቅስቃሴና በድርጅታችን መሪነት ፖለቲካ ኢኮኖሚውን በመቀየር ሊፈቱ የሚገባቸውን ችግሮች ሌላ መልክ ማስያዝና ወደ ውስጥ ከመመልከት ይልቅ ውጫዊ ማድረግ ለበለጠ ቀውስ ይዳርገን እንደሆነ እንጂ መሠረታዊ መፍትሄ አይሆነንም፡፡

ደረጃው ይለያይ እንጂ በሁሉም ክልሎች እየታየ ያለው የህዝበኝነት አዝማሚያ በጠንካራ ትግል ልንመክተው ይገባል፡፡ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ መርህ ላይ ተመስርቶ ህዝቦችን ለትግልና ለድል ማብቃት የሚጠበቅባቸው አመራሮች ራሳቸውን ወደሰፈር የጎበዝ አለቅነት ማውረድ የጀመሩበት አዝማሚያ በእንጭጩ እንዲቀር ሊደረግ ይገባል፡፡ አንዱ መንደር ከሌላው ተለይቶ የሚያድግበት አንዱ ክልል ከሌላው ተነጥሎ ባለፀጋ የሚሆንበት መንገድ የጥፋትና የመበታተን እንጂ የአንድነት እና የልማት መንገድ እንዳልሆነ ታውቆ በጊዜ ወደ ቀልብ መመለስ አማራጭ የሌለው ጉዳይ እንደሆነ ተገንዝቦ ርብርብ ማድረግ ይገባል፡፡

☞

በዚህ ረገድ ዋናው ስራችን አሁንም የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ስራችንን አጠናክሮ መቀጠል ነው፡፡ መድረኮቻችን ሕዝባችን የሚሆነውን የሚመርጥባቸው መድረኮች እንጂ የሕዝብን የፍትህና የተጠቃሚነት ጥያቄ ለመመለስ ፍላጎቱም ዝግጅቱም የሌላቸው ሰዎች በስልጣን እርካብ ላይ የሚፈናጠጡባቸው መሆን የለባቸውም፡፡ የሃገራዊ ህልውናችን መረጋገጥም ሆነ ልማታችን ወደ የማይቀለበስ ደረጃ መድረስ የዲሞክራሲ ተቋሞቻችን መጎልበት የማይተካ ሚና እንዳላቸው አውቀን በዚህ ረገድ ያሉብንን ክፍተቶች ለመድፈን መረባረብ ይኖርብናል፡፡ የህዝብ ምክር ቤቶች፣ የተለያዩ የሲቪል ማህበረሰቦች፣ የሚዲያና የፖለቲካ ተቋማት ይበልጥ መጠናከር ያለባቸው ይሆናል፡፡

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ባለፉት ጥቂት ገፆች ለማየት የሞከርናቸው ጉዳዮች በዋናነት ለውጭ አደጋ ተጋላጭ የሚያደርጉን የውስጥ ጉዳዮችን የሚመለከቱት ናቸው፡፡ አሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተፈጠሩ ያሉት ለውጦች በባህሪያቸው የቱን ያክል ተገማችነት ቢኖራቸው ወይም ባይኖራቸው በውስጥ ያለውን ሁኔታ በተሻለ ደረጃ ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥራ እስከተሰራ ድረስ ውጤቱ እጅግም የከፋ እንዳይሆን ለማድረግ እንደሚቻል ይታመናል፡፡ ይሁንና የውስጥ ሥራችን የቱንም ያክል ያማረ ቢሆን ከእኛ ቀጥተኛ ቁጥጥር ውጪ ያለውን ውጫዊ ሁኔታ በትክክል መገንዘብ ግድ ይላል፡፡ በተፈጠሩት ክስተቶች ልክ አዎንታዊ አጋጣሚዎችን በሚገባው ለመጠቀም፤ ሥጋቶችን በተቻለ መጠን ለመቀነስ እንዲሁም ከጎረቤቶችም ጋር ሆነ በቅርብም በሩቅም ካሉ አጋሮች ጋር በጋራ ተጠቃሚነት መንፈስ በመሥራት የተሻለ ዓለም እንዲፈጠር ለማድረግ ወደድንም ጠላንም ዓለማዊ ሁኔታውን በየጊዜው መፈተሽ ለነገ የማይባል ግዴታችን ይሆናል፡፡

ከሃገር ውስጥ ፀረ-ድህነትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታችን ቀጥሎ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባ ከጎረቤቶቻችን ጋር ያለን ግንኙነት ነው፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ ከጎረቤቶቻችን ብዙዎቹ በችግር የሚናጡና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚያጋጥሙ ችግሮች ቀጥተኛ ተፅዕኖ የሚያደርስባቸው በመሆናቸው ያሉበትን ሁኔታ በየወቅቱ ማየቱ ግድ ይለናል፡፡ ሶማሊያ፣ ኤርትራና ጁቡቲ እንዲሁም ሱዳን፣ የዓረቡ ዓለምና መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ የሚከሰቱ አነስተኛ የፖለቲካ ዕድገቶች ጭምር በአብዛኛው በአሉታዊነቱ ያመዘነ ጥላ የሚያጠሉባቸው ሃገራት ናቸው፡፡ ደቡብ ሱዳንና ኬንያም እንደዚሁ የምዕራቡ ዓለም በሚሰጣቸው ትኩረት ልክ ካሉበት

☞

ቀውስ ወደ ተባባሰ ቀውስ ሊገቡ የሚችሉበት ዕድል እንዳለ ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ጂቡቲ ውስጥ ሁሉም ስም አለኝ የሚል የዓለም ኃይል በሙሉ መሬት ተከራይቶ የአካባቢውን የባህር መተላለፊያን የሚቆጣጠር ቃፊር እንዳስቀመጠ ይታወቃል፡፡ ቻይና፣ ፈረንሳይ፣ ጃፓን፣ አውሮፓ ህብረት እና ዩናይትድ ስቴትስ በጅቡቲ ወታደር ማረፊያ ካላቸው ሃገራት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ በህግ በሚመራው (Rules Based) በሆነው ዓለም ውስጥ የነዚህ በአብዛኛው ጊዜ እርስ በእርስ የሚጣረስ አቋም ያላቸው ሃገራት በጥቂት ስኩዌር ኪሎ ሜትር ርቀት ውስጥ ባለ ቦታ ባንድ ላይ መገኘታቸው የጅቡቲን ሉዓላዊነት እስካከበሩ ድረስ እዚህ ግባ የሚባል ችግር አለው ተብሎ አይወሰድም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ከእኛ ጥቅም አንፃር መታየበት ያለበት ጉዳይ ከወደብ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ ሊኖር የሚችል ፈተና ካለ ብቻ ነው፡፡ የጂቡቲ መንግስት ከወደብ ማስፋፋት ጋር በተያያዘ እስካሁን ብዙ ርቀት እንደሄደ ይታወቃል፡፡ የዚህ መስፋፋት ዓላማም ጅቡቲ በዓለማችን ትልቅ የባህር መተላለፊያ በር ከመሆኗ ጋር ተያይዞ የቀረጥ ነፃ ዞን ለማቋቋምና የመሸጋገሪያ ወደብ መሆንም ግምት ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ ይሁንና ለሚቀጥሉት ዓመታት የጂቡቲ ወደብ መስፋፋት ዋነኛ ትኩረት የኢትዮጵያ እያደገ ያለ የወጪና ገቢ ንግድ ማስተናገድ እንደሆነ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ ስለዚህ የጂቡቲ ሰላምና መረጋጋት ተጠብቆ በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነታችን የበለጠ በሚጎለብትበት ሁኔታ ላይ ያለማመንታት ልንሰራ ይገባል፡፡ ከቻይና በስተቀር ሌላው ትልቅ ነኝ ባይ ሃገር በሙሉ ወደየምሽጉ መመለስ በጀመረበት ሁኔታ ከወደብ አጠቃቀም አንፃር ሊደርስ የሚችል የረባ ፈተና አለ ብሎ አይወሰድም፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ይኖራል ተብሎ የሚገመት ችግር ቢኖር የገልፍ ባህረ ሰላጤ ሃገራት በአካባቢው የሚጫወቱት ወይም ሊጫወቱት የሚችሉት አሉታዊም ይሁን አዎንታዊ ሚና ብቻ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ሁሉ ሃገራችን ኢትዮጵያ በመካከለኛው ምስራቅና በሌላው አፍሪካ መካከል እንደ ድልድይ ሆና የምታገለግል ሃገር ናት፡፡ በዚህም ሳቢያ በነዚህ ሃገራት ዘንድ የሚከሰቱ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ክስተቶች እንዲሁም ሃገራቱን በሚያስተዳድሩ ገዥዎች የሚወሰኑ ውሳኔዎች ለአካባቢያችን ሰላም የራሳቸው የሆነ ተፅዕኖ እንዲኖራቸው መገንዘብ ተገቢ ይሆናል፡፡

በየመን ውስጥ ባለው ግምትም ሆነ ከኢራን ሚና ጋር ተያይዞ እነዚህ ሃገራት ዘንድ የሚከተሏቸው አቅጣጫዎች ሚዛናዊነታቸውን የጠበቁ ☞

እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ የሚቻለንን ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ ለዚህም ሲባል ኢትዮጵያን በሚመለከቱ በየሃገራቱ ዘንድ ለዘመናት የተያዙ የተሳሳቱ አመለካከቶችን ለማስተካከልና በጋራ ጥቅም ዙሪያ አብረን ከመሥራት የሚያግደን ነገር እንደሌለ ያለማሳለስ ማስረዳት ይኖርብናል፡ ፡በየመን ውስጥ ሰላም እንዲፈጠር፣ በሶማሊያም ሆነ በሌሎች የአካባቢው ሃገራት ዘንድ ሃገራቱ በእውቀትና የጋራ ጥቅምን ባገናዘበ መልኩ አዎንታዊ ሚና መጫወት የሚያስችላቸውን ዕድል በማመላከት ጭምር በቅርበት መሥራት ይኖርብናል፡፡ እነዚህ ሃገራት መድረሻ ያጣ በርካታ ገንዘብ ያላቸው ከመሆናቸው አንፃር ለልማትና ለኢንቨስትመንት ብቻ ሳይሆን በእውቀት ላይ ካልተመሰረተ ለሁከትና ለአለመረጋጋት ሊውል የሚችልበት ዕድል እንዳለ ተገንዝበን ከእርሱ ጋር በቅርበት በመስራት የአካባቢው ሰላም አካል ለመሆን እንዲችሉ የበኩላችንን ጥረት ማድረግ ይኖርብናል፡፡

በቅርቡ ከአዲሱ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት የመካከለኛው ምስራቅ ጉብኝት ጋር ተያይዞ በነዚህ ሃገራት ዘንድ የተከሰተውን አለመግባባት እንደምሳሌ በማየት በዚህ ረገድ መደረግ ያለበትን ጥንቃቄ መገንዘብ የሚያስፈልግ ይመስለናል፡፡ ፕሬዚዳንት ትራምፕ የሳውዲንና የዩናይትድ አረብ ኤምሬትስን ካዝና ለማስከፈት በነበራቸው ከፍተኛ ጉጉት የተነሳ ሃገራቱ ኳታርን እንደ አንድ ሽብር ፋይናንስ እንደምታደርግ ሃገር እንድትወገዝ የፈለጉ መስለው በመታየታቸው እነዚህ ሃገራትና ግብፅ ኳታር ላይ እጅግ ሰፊ ማዕቀብ እስከመጣል ደርሰዋል፡፡ በዚህ ብቻ ሳይቆጠቡ ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎች የአካባቢውን ሃገራት ኳታርን እንዲያወግዙ የጠየቁበት ሁኔታ እንደነበር ይታወቃል፡፡

በወቅቱ ኤርትራና ጂቡቲ የነ ሳውዲን አቋም የደገፉ ሲሆን የሃገራችን መንግስት ጉዳዩ በሰላም እልባት ሊያገኝ እንደሚገባው መርህ ላይ የተመሰረተ አቋሙን መግለፁ ይታወቃል፡፡ ይሁንና በኋላ ላይ በተግባር እንደታየው የአሜሪካ ትልቁ የጦር ካምፕ ዶሐ ውስጥ እንዳለ በነጋታው ያስታወቁት ፕሬዚዳንት ትራምፕ ከመጀመሪያው አቋማቸው ወጥተው ጉዳዩ በሰላም እልባት እንዲያገኝ ጥሪ ያደረጉበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በሃገራት መካከል ያለ ትብብር በአንድ መግለጫ ምክንያት አደጋ ላይ ሊወድቅ በሚችልበት ሁኔታ ውስጥ ይነስም ይብዛም ሰከን ብሎ በመርህ ላይ መቆም መቻል ከብዙ ጭቅጭቅ ሊያድን እንደሚችል ይህ አንድ ማሳያ ይሆናል ብለን እናምናለን፡፡

☞

የተፈጠረው ሁኔታ ምንም ይሁን ምን ከመሠረታዊ መርሆዎቻችን ላፍታም ቢሆን ሳንነቃነቅ እንደየሁኔታው ማስተናገድ የምንችላቸውን ጉዳዮች በየወቅቱ በጥናት ላይ በመመስረት መወሰን ከአላስፈላጊ ግጭት ሊያድነን እንደሚችል መገንዘብ ይገባናል፡፡ በመርህ መመራት ለሚባል ፅንሰ ሃሳብ ባዕድ የሆነው የሻዕቢያ መንግስት የፕሬዚዳንት ትራምፕን የችኮላ መግለጫ እንደ መጨረሻ ቃል በመውሰድ ለአስራ ምናምን ዓመታት ብቸኛ ቀለብ ሰፋሪው ከነበረችው ኳታር ጋር እንደ ዋዛ ለመቆራረጥ መብቃቱን ስናይ በዚህ ረገድ የምንወስዳቸው ውሳኔዎች ምን ያክል በመሠረታዊ መርሆዎች ላይ መመሥረት እንዳለባቸው ያስገነዝበናል፡፡

"የውጪው ኢንቫይሮንመት ምንም ያህል አላላውስ ቢለን የተቀረቀረና የተዘጋ አይደለም፡፡ በአስቸጋሪ ግሎባል ከባቢያዊ ሁኔታ እጅግ ከፍተኛ በሆነ ፍጥነት ማደግ ይቻላል፡፡ ንድፈ ሃሳብ አያስፈልገውም፣ በተግባር እያየነው ነው፡፡ ስለዚህ ዘለን ዘለን ሲያቅተን ኤጭ ይኸ ነገር ኮምጣጣ ነው እንበል ካላልን በስተቀር ዘለው ዘለው ያሉበት ቦታ ላይ መድረስ የቻሉ ሃገሮች በተግባር አሁን እያየን ስለሆነ የውጪው ከባቢያዊ ሁኔታ ምንም ያክል መጥፎ ቢሆን የተቀረቀረና የተዘጋ አይደለም፡፡ በዚህ ቀዳዳ ውስጥ አልፎ መሄድ የሚችል ሰው፣ሃገርና አልፎ መሄድ የሚያስችል ስትራቴጂ ይጠይቃል፡፡ ነገር ግን አልፎ መሄድ ይቻላል" መለስ ዜናዊ

## ምን ይደረግ ?

ከላይ እንዳየነው ዓለማዊ ሁኔታው ውጥንቅጡ የወጣ ሆኗል፡ ፡በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ እንዲሉ ይህ ውጥንቅጡ በወጣበት ዓለም ህዝበኛ የቀኝ አክራሪ ኃይሎች የቁልፍ አገራትን የስልጣን መዘውር በመቆጣጠር ላይ ይገኛሉ፡፡ እዚህ ላይ ቆም ብሎ ከቶ ምን ማድረግ ይቻል ይሆን ? ብሎ መጠየቅና መልሱን መፈለግ ያሻል፡፡

### ሀ/ አገራዊ ሁኔታው በፍፁም ለቀኝ አክራሪ ኃይሎች የተመቸ እንዳይሆን ማድረግ

ዛሬ በአገራችን የቀኝ አክራሪ አስተሳሰብ ወደ ጠርዝ የተገፋ አስተሳሰብ ሊሆን ችሏል፡፡ ሆኖም ዛሬም ቢሆን በዚሁ አስተሳሰብ ላይ

☞

ወሳኝ የሚባለውን ድል አልተቀዳጀንም፡፡ በመሆኑም የሞት የሽረት ትግል አድርገን በተቻለ ፍጥነት አስተሳሰቡን ግብዓተ መሬት በማስገባት አይቀሬውን የሽንፈት ጽዋ እንዲቋደስ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሁኔታ እንዲፈጠር ደግሞ የፀረ ቀኝ አክራሪነት ትግላችን ሊፋፋምና በወል ጥረት ላይ ሊመሠረት ይገባዋል፡፡ይህን ስናደርግ ዓለማዊ ሁኔታው የቱንም ያህል ይመች ነባራዊ አገራዊ ሁኔታውን ግን የመቀየር ችሎታ አይኖረውም፡፡

ለ/ ህዝባችንን የማንቃት የቤት ስራ

የቀኝ አክራሪነት አስተሳሰብን ማሸነፍ የምንችለው ህዝባችንን ከጐናችን ማሰለፍ ስንችል ብቻ ነው፡፡ ህዝባችን ለፀረ ቀኝ አክራሪነት ትግላችን ሳያወላዳ ድጋፍን መስጠት የሚችለው ደግሞ በጉዳዩ ላይ የተሟላ ግልፅነት ካሳደረ ብቻ ነው፡፡በመሆኑም አሰተሳሰብ የሚያመነጩ ተቋሞቻችን፣ ሚዲያዎቻችን፣ ልሳኖቻችን ወዘተ.. ለዚሁ ተግባር ሊተጉ ይገባል፡፡ እናም የህዝባችንን አስተሳሰብ የመገንባት ታላቅ ተልእኮ በእያንዳንዳችን የድርጅት አባላት ጫንቃ ላይ ወድቋል፡፡

ሐ/ ጉዳዩን በቅርበት መከታተልና እዛ ላይ የተመሰረተ ጥልቅ ጥናት ማድረግ

ዓለማዊ ሁኔታው በሚያስገርም ፍጥነት በመቀያየር ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን በአንክሮ መከታተልና ጥልቅ ጥናት ማድረግ ያሻል፡፡ያለበለዚያ በጉዳዩ ላይ የምንይዘው አቋምና ግንዛቤ ግልብ ይሆንና የምንወስደው እርምጃም ችግሩን በአግባቡ የሚፈታ አይሆንም፡፡ በመሆኑም ክስተቱን በአንክሮ ልንከታተለውና ልንረዳው ይገባል፡፡ከዚያም ጥልቅ ጥናት በማድረግ የሚያሰራ እቅድ መንደፍና በጥብቅ ዲስፕሊን መተግበር ያስፈልጋል፡፡

መ/ ከአፍሪካውያንና ከሌሎች አገራት ተራማጅ ፓርቲዎች ጋር ያለንን ግንኙነት ማጠናከር

የህዝበኛ ቀኝ አክራሪ ኃይሎች እንቅስቀሴ ቁልፍ የካፒታሊስት አገራትን በእጁ ካስገባ በኃላ ትግሉን ወደ ዓለማቀፋዊ ደረጃ አሸጋግሮታል፡፡ በመሆኑም በአንድ በኩል በአገር ውስጥ እየታገልን በሌላ በኩል ደግሞ በዓለም አቀፍ ትግል ውስጥ የበኩላችን አስተዋፅኦ ማድረግ

☞

ይገባናል፡፡ ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል እንዲሉ የምንገኝበት ቀጠናና አህጉራችን በቀኝ አክራሪ ኃይሎች ቁጥጥር ውስጥ እንዳይገቡ ልንታገል ይገባል፡፡በመሆኑም ከመቼውም ግዜ በላይ ከተራማጅ አፍሪካዉያን ፓርቲዎች ጋር የጋራ ግንባር ፈጥረን ይህን አደገኛ አዝማሚያ ልንታገለው ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአፍሪካ ተራማጅ ፓርቲዎች ደረጃ የሚደረገው ትብብር እንዳለ ሆኖ ጉዳዩ ዓለምአቀፋዊ አድማስ አለውና ትብብሩና ትግሉም ተመሳሳይ አድማሳዊ ተደራሽነት ሊኖረው ይገባል፡፡ በመሆኑም በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚገኙ ተራማጅ ፓርቲዎች ጋር የምናደርገው ትብብርም እንዲሁ ሊጠናከር ይገባል፡፡

*ሠ/ የደፈረሰውን ውሀ የማረጋጋት ስትራቴጂ*

ዓለም ውጥንቅጧ በመውጣት ላይ ይገኛል፡፡ ይሄ ሁኔታ በቀላሉ ማስቀመጥ ካስፈለገ እንደ አገራችን አርሶ አደር አባባል ውሃው ደፍርሷል፡፡ እኛ ከውሀው መደፍረስ እንጎዳለን እንጂ አናተርፍም፡፡ በመሆኑም ከምንም በላይ የደፈረሰው ውሀ ይበልጥ ደፍርሶና የጦርነት ዳንኪራው ከተራ ዛቻ አልፎ ዓለም እንዳይተረማመስ የትርምሱ አካል ሳንሆን ውሀው እንዲረጋጋ የምንሰራ ኃይሎች ነን፡፡ በመሆኑም አሸሸ ገዳሜ ከሚሉት ጋር በማበር ዳንከራውን ሳንገፈጥ ለትብብርና መረጋጋት ቅድሚያ ሰጥተን ዓለም እንድትረጋጋ ከሚሰሩት ጋር ከመቼውም ግዜ በላይ እጅና ጓንት ሆኖ መስራት ያስፈልጋ፡፡ የደፈረሰው ውሃ እንዲረጋጋ የሚያስችሉ ዝርዝር ስትራቴጂ ነድፈንም ልንንቀሳቀስ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ውጥንቅጡ እየወጣ ባለ ዓለም ውስጥ ተጽዕኖ የሚፈጥሩብን ሁኔታዎች ያሉትን ያህል ለልማታዊ ዴሞክራሲያዊነት ማበብ መልካም አጋጣሚዎችም በስፋት አሉን፡፡ ጓድ መለስ እንዳለው የተቀረቀረብን አይደለንም፡፡ በበቂ ጥናት ላይ ተመስርተንና በየጊዜውም ጥናታችንን እያደስን በመሄድ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስና መልካም አጋጣሚዎችን አሟጠን ለመጠቀም እንችላለን፡፡ ይህ ጽሑፍም በፓርቲውና ሌሎች ምሁራን ዘንድ ውይይትና ክርክር ለማድረግ የተዘጋጀ እንጂ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት አቋም አይደለም፡፡ የፀሐፊው የግል ግንዛቤ ላይ የተመሰረተ እና ከክርክሮችና ውይይቶች በኋላ ዳብሮ የሚመለከታቸው አካላት ሊጠቀሙበት የሚችሉበትም እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ እናም መልካም የውይይትና የክርክር ጊዜ እንዲሆን እንመኛለን፡፡

☞